«ይህ ከጥያቄ ውጪ ነው። ሁለቱ ጉዞዎች እንደተለያዩ መቆየት ይኖርባቸዋል። ይህ የንጉሡ ትዕዛዝ ነው።»

«የፈረንሣይ ንጉሥ ማለትዎ ይሆናል። መቼም የሲናር ንጉሥ አያደርጉትም»

«ምን ማለትዎ ነው?»

«ምንም! የሲናርን ንጉስ በሚገባ እናውቃቸዋለን፣ ይ'ከው ነው»

በነዚህ ቃላት ውስጥ ምንም የለባቸውም። ይሁን እንጂ ከቃላቱ ጥልቅ ፍቺ ውስጥ፣ አንድ ሰው ኩል በመሰለ ውሃ ሥር ሆን ብሎ ለማስፈራራት ፈልጐ እንደሚዋኝ አባብ የመሰለ አሣ፣ በግልፅ እንደሚመለከት ሁሉ፣ አነጋገሩም በአዕምሮ ውስጥ የተጠነሰሰ ነገር እንዳለ ያሣያል። ሙሴ ዱ ማይሌም ይህን ስሜት ወዲያውኑ ተረዳው። ምንም ዓይነት አደጋ ሊያስከትል የሚችል ነገር አይወስድም። የፈለገው እንኳ ቢሆን መነኮሣቱ ምንም ጓዝ ስለሌላቸው ጉዟቸውን ይጀምራሉ። ሌባም ስለሆኑ ፈጥነው መጓዝ ይችላሉ። ስለዚህ ዱ ሮውሌ ሌላው ቀርቶ ሲናር እንኳ ሣይደርስ በፊት ማንኛውንም ዋጋ ተከፍሎ ምንም ዓይነት የፖለቲካ የበላይነትን እንዳይዙበት መታገድ ይኖርባቸዋል።

«እሺ፣ ታዲያ ምን ይፈልጋሉ?»

ወደፊትና ወደ ኋላ ሲወዛወዙ ከቆዩ በኋላ፣ ካፑቺኑ ተገቢነት በሌለው ዘዴ አንድ ግመል ሁለት በቅሎዎችና ጥቂት መጠን ወርቅ አገኙ። ለቆንሲሉ ዝቅ ብለው ሰላምታ በማቅረብ አመስግነው ሄዱ።

«መቼም በዚህ ድርጊታችን ተሸናፊ አንሆንም። ቢያንስ አሁን ባለዕዳዬ ናቸው» አለ ቆንሲሉ ለሙሴ ማቼ፣ የእጅ መስጠቱን ተገቢነት ለማሣመን እየጣረ። ከዚህ በኋላ ሁለቱ ቢሮውን ለቅቀው ሄዱ። ቆንሲሉ ወደ መኝታ ክፍሉ ለመሄድ ፎቁን ሲወጣና ሙሴ ማቼም በመጥረጊያ ማስቀመጫ ክፍሉ ውስጥ ገብቶ በራሱ ላይ በሩን እስኪዘጋ ድረስ ጠበቀችና ፍራንቾይዝ፣ ከተደበቀችበት ወጥታ ወደ አሊስ ክፍል ተመለሰች።



# 5

ሙራድና ሙሴ ዱ ማይሌ፣ ደማቅ በዓል አድርገው ከተለያዩ ከአንድ ሣምንት በኋላ የኤምባሲው ቅፍለት ለጉዞው ተነሣ። በፈረንሣውያን ማህበረሰብ ውስጥ የተከበሩ ሰዎች፣ የዱ ሮውሌ ሠራዊት ሲንቀሣቀስ ለማየት በዝርዝር ተጠርተዋል። ብዙዎቹ ሸኚዎች ለዚህ ጉዞ የሚሰጡት ምንም ዓይነት ስም አልነበራቸውም። ቆንሲሉ፣ ባለፈው ዘመቻ ጊዜ የባከነውን ገንዘብ በከፊል ለማካካስና ክብሩን ለመጠቀም ችሏል። ፓሻው፣ ለዚህ ተጓዥ ቡድን አስፈላጊ የሚሆኑትን መብቶች ፈቅዶ ለመስጠት ችግር የፈጠረ ቢሆንም፣ ቆንሲሉ ግን ጉዞውን በጥንቃቄና በስልት ለመያዝ ሃሣብ አላደረበትም። ይልቁንም ለዚህ እጅግ ከባድና ሊሆን ለማይችል ዕቅድ፣ ፈረንሣይ የሰጠችውን ከፍተኛ ግምት ለማሣየት ፈለገ። ምንም እንኳ፣ ቱርኮች እዚህ ጌቶች ነን በማለት ለማስመሰል ቢሞክሩም፣ መቼም ሁልጊዜም ለነርሱ ሲሰግድ የሚኖር የለም ይላል።

ፈረሰኛው ዱ ሮውሌና በኩራት የሚወጣጠሩት አጭበርባሪዎቹ የቡድን አባላቱ፣ በግመሎቻቸው ላይ ተቀምጠው ሲታዩ ድንቅ ናቸው። ቤላክ፣ ብቃት ያለው የቅፍለት መሪ ነው። ግመሎቹንም በአንድ ላይ አስደሳች እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ አሰልጥኗቸዋል። እንዲያውም በእግሮቻቸው ላይ የብር ቃጭል አንጠልጥሎላቸዋል።

ይህ አነስተኛ የቅፍለት ጓዝ ቀደም ሲል ፖንሴ፣ አሰዩት ውስጥ የተቀላቀለውን ትልቅ ቅፍለት መገናኘት አልቻለም። በመጨረሻም ተጓዦቹ ቁጥራቸው ብዙ ስለሆነና በበቂም ስለታጠቁ፣ ቤላክ ደህና አድርጐ የሚያውቀውንና በአባይ ሰስተኛው ፏፏቴ ላይ ሊያደርሣቸው የሚችለውን መንገድ ለመከተል ወሰኑ።

ይህ የተንቆጠቆጠ ሰልፍ ወደ ደቡብ አቅጣጫ ሲያቀና፣ ካይሮ ውስጥ የሚገኙ ፈረንሣውያን ባለሥልጣናትና ሃብታሞች ከርቀት ሲያዩት እያነሰባቸው ሲሄድ ልበ ሙሉ ሆኑ። ይህ በዚህ እንዳለ ሌላ ተጓዥ ደግሞ ከቆንስላው ለመልቀቅ ሽር ጉድ እያለ ነው።

ሙሴ ዱ ማይሌ፣ ሴት ልጁ በዚህ ጊዜ ለቅቃ እንድትሄድ ይፈልጋል። ምክንያቱም የመታየቷና የመሄዷ አሉባልታ አይገላም። ስለዚህም፣ አንድ አርማ እንኳ በሌለበት ጥቁር ሰረገላ ውስጥ ሆና፣ ሁለት ዘበኞች በፈረስ ላይ ተቀምጠው አጀበዋት ብቻዋን ጉዞዋን ጀመረች። ማዳም ዱ ማይሌ፣ ለእግዚአብሔር አገልጋይነት የሰጠቻትን መነኩሲት በመሳም ፣ደህና ሁኚ

ካለቻት በኋላ፣ በመግቢያው መተላለፊያ ላይ ሀሲናዋን ስታ ወደቀች፡ ፍራንቾይዝ፣ ወደ ክፍሏ ተሸክማት መውሰድ ስለነበረባት ጓደኛዋ ስትሄድ በወጉ ልታያት እንኳ ዕድል አልነበራትም።

የልብስ አጣቢዋን በቤቱ ውስጥ መቆየት ታግሶ ችሎ የነበረው ቆንሲል፣ አሊስ ቆንስላውን በሉቀቀችበት ዕለት ከፊቱ እንዳትደርስ ለማድረግ ወደ ዕዳት ሥራ አዛወራት። ያንኑ ዕለት ማታ፣ ፍራንቾይዝ ጓዟን ጠቅልላ ተሸክማ ወደ ቤቷ በእግርዋ ተመለሰች።

በመስኮቷ አሻግራ ስትመለከት ሜትር ዠረሚ በመድረኩ ላይ ስለነበረ ሄዳ አገኘችው። የአሊስን መልቀቅም ነገረች። በሚቀጥሉት ቀናት ስለሚያከናውኗቸው ጉዳዮች ተመካከሩ። ከዚህ በኋላ በመካከላቸው ፀጥታና ፍርሃት ነገሠ።

ከምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ነበር። ከመድረኩ በላይ የሚታየው የሰማይ ሜዳ፣ ደማቅ ሰማያዊ እየሆነ ነው። የብርቱካን ዛፎች አሁንም ገና አረንጓዴነታቸው ሲታወቅ ጥቂት ከዋክብትም ያንፀባርቃሉ። ይህ ሰዓት፣ አብረቅራቂው ምሽትና የቀኑ የብርሃን ቀለማት ሲለዋወጡ፣ ሰላምታ የሚሰጣጡበት ጊዜ ይመስላል። በቤቱ ውስጥ ያሉት ዕፅዋቶች ደን፣ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ጥቅጥቅ እያለ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሜትር ዠረሚ እንክብካቤ አላደረገላቸውም። ከኋላቸው ባሉ ብዙ ዕፅዋት ግፊት ሳቢያ ትላልቅ ቅጠሎች በመስኮቱ መስተዋት ላይ ተደፍጥጠዋል።

«እፅዋቶችህ ካንተ እየራቁ ነው» አለች ፍራንቾይዝ

«ከትናንት ጀምሮ ምን ለውጥ አለ . . . »

ለምንጊዜውም ላይመለሱ፣ከሁለት ቀናት በኋላ ከካይሮ ለቅቀው የመሄዳቸው ሃሣብ ሁለቱንም በተመሣሣይ የትዝታ ማዕበል ውስጥ እንዲዋልሉ አደረጋቸው። እውነት ነው ሊሄዱ ነው። የሚሄዱትም አብረው ነው። አብረው በአንድ ጉዳና ይጓዛሉ። ሊያጋጥማቸው የሚችለውንም አደጋ አብረው ይጋፈጣሉ። ባለፉት ሁለት ዓመቶች አንዳችም ነገር ማይፈፅሙ ቢቆዩም፣ አሁንም ድረስ ፍፁም እርስ በርሣቸው አልተቀራረቡም። ይህ ሃሣብ ዠረሚን ተስፋ የለሽ ያደረገውና ጉዳዩም እንዳሳሰበው ፍራንቾይዝ ተሰማት።

«እባክህ ገሽሽ አታድርገኝ። ሁለታችን አብረን መሆናችን የማይቀር ነው። አሁን ባለንበት ሁኔታ ግን መደሰት ይገባናል። እኔ ሌላ የምጠይቅሽ ነገር የለኝም።»

እርስ በእርሣቸው ፊት ለፊት ተያዩ፣ ተቀራረቡ።



«ጆን ባፕቲስት የውሃ ሽታ ሆኖ ቀረ። አሊስም ትታን ሄደች። አ! ዠረሚ፣ ሁለታችንንም ያጣናቸው ነገሮች ናቸው ያቀራረቡን» አለች።

በክፊል ጢም የሸፈነውን ጭንቅላቱን ቀና አደረገና እነዚያን ሩህሩህ አይኖቹን አሣረፈባት፡ እርሷም ፊትዋን በሰፊው ደረቱ ላይ ስታደርግ በክንዶቹ ውስጥ አቀፋት። ጊዜው ሙሉ በሙሉ ሲመሽ፣ በመስኮቱ ውስጥ ከፍ እያሉ የሚወጡ እየመሰላቸው ወደ ፍራንቾይዝ ቤት ሄዱ። በሁለቱ ማዕዘኖች ላይ በሸክላ ድጋፍ የተሠራ ሰፊ አልጋ አላት። ይህ አልጋ በደስታ ማዕበል ውስጥ፣ በደስታ፣ በፍቅርና በነፃነት እንደሚጋጭ ታላቅ የመርከብ ተንሣፋፊ አካል ለሊቱን ሙሉ በዙሪያቸው ሲንሳጠጥ አደረ።

በማግስቱ ጠዋት፣ ሜትር ዠረሚ ወደ ቤቱ ተመልሶ፣ ሻንጣዎቹን ማዘጋጀት ዕቅዱ ነበርና ሥራውን ጀመረ። ይሁን እንጂ አንዴ ወደ ፎቅ ቀጥሎም ወደ ምድር ቤት በመመላለስ ለዚህን ያህል ረዥም ጊዜ በጓደኝነት ያቆዩትን ዕፅዋት እየተቀመጠና እንደገናም እየተነሳ፣ ባለማቋረጥ በዙሪያቸው እየተጓዘ ይመለከታቸው ጀመር። ዠረሚ የፀሎት አማራጭ አልነበረውም። ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ለእግዚአብሔር ምን እንደሚነግረውም አላወቀም።

ፍራንቾይዝ አስተዋይ ስለሆነች መጥታ ልታስቸግረው አልፈለገችም። ነገ ማለዳ ግን አብረው ጉዞቸውን እንደሚጀምሩና ልቧን ሊያስደስተው ከጎኗ እንደሚኖራት እርግጠኛ ነች።

ከሰዓት በኋላ በአሥራ አንድ ሰዓት ላይ በምድር ቤቱ ጥላ የተነሣ መጨላለም ጀመረ። ያንቀሳቅሰ፣ በመብራት እንደሚነቃ ሁሉ፣ በህልም ውስጥ ያለ ሰውም ብዙውን ጊዜ ከግላዊ ዓለሙ በጨለማ ጥቃት ብቻ ይንቀሳቀሣል። ሜትር ዠረሚ ፋኖሱን ሲያበራ ለቅቆ ለለመሄዱ ምንም ዝግጅት አለማድረጉን በድንጋጤ ተገነዘበ። ከዚያም ከአቢሲኒያ ከተመለሰ በኋላ በቁምሣጥኑ ውስጥ ክርችች ብለው ደርቀው የተቀመጡትን ሁለት የኮርቻ ሻንጣዎች አገኘና ለሚጠብቀው ጉዞ የሚያስፈልጉትን ሁሉ መሰብሰብ ጀመረ።

በአንድ ሰዓት ላይ በሩ ተንኳኳ። ፍራንቾይዝ ትሆናለች ብሎ ስላሰበ ዠረሚ በሰጨት አለ። ማንኳኳቱ ተደገመ። ይህን ያህል ከሚጣደፈው በር አንኳኪ ግን ምንም ድምፅ አልተሰማም። እርምጃውን ዝግ አድርጐ ወደ በሩ እየተደናበረ ተራምዶ፣ የዛገውን አጮልቆ መመልከቻ ቀዳዳ ከፈተው።

«ምንድነው?» አለ ጉርነን ባለ ድምፅ፣ በቀዳዳው እያጮለቀ

በመተላለፊያው በኩል ባለው የብርሃን ፍካት ጀርባ የአንድ ወንድ ሰው ቅርፅ ታየው።

«ምን ትፈልጋለህ?» አለ ሜትር ዠረሚ፣ ምናልባት ሃኪም ፍለጋ የመጣ ሰው ይሆናል በሚል ሃሣብ

«ክፊት» አለ ሰውዬው።

«አ! ቀስ በል ወዳጄ፣ መጀመሪያ ነገር እዚህ ማንም የለም።»

እንግዳው ሰው አፉ የማጮለቂያውን ቀዳዳ እስኪነካው ድረስ ተጠጋ።

«እንዲህ ደደብ አትሁን፣ በሩን ክፈተው»

ሜትር ዠረሚ አመዱ ቡን ሲል ተሰማው

«አንተ ነህ እንዴ?»

«ፍጠን፣ ሁሉም ሊያየኝ በሚችልበት በዚህ ቦታ ላይ በግላጭ አታቆየኝ»

በሰከንድ ጊዜ ውስጥ ፕሮቴስታንቱ መቀርቀሪያውን አወለቀውና በሩ ተከፈተ። ጆን ባፕቲስት ወደ ውስጥ ዘለቀ። ሁለቱም ተቃቅፈው ድምፅ ሳያወጡ እንባቸውን አፈሰሱ

በመጨረሻ ተነስቶ በመቆም ወደ ኋላ ራመድ ብሎ ፋኖሱን ከፍ አደረገና «እስቲ ልይህ» አለው ሜትር ዠረሚ።

ጓደኛው የሚለይ አይደለም። በርግጥ አንፀባራቂዎቹ ጥቋቁር ዓይኖቹ በቦታቸው ናቸው። በርግጥ እርሱ ነው ብሎ ለመናገር የሚያስችለው፣ በትክክል የሚታወቀው የፊቱ ቅርፅ እንዳለ ነው። «አዎ፣ ምናልባትም እሱ ነው» ግን እኮ ሁለመናው ተለዋውጧል። ፀጉሩ በአጭሩ ተከርክሞ፣ አልፎ አልፎ ግራጫ ሆኗል። ግራና ቀኝ ሾል ብሎ የሚታየው ሪዙ፣ የአፍንጫውን ቅርፅ ለውጦታል። በሉዊስ 13ኛ ዘይቤ አገጭ ላይ ያለው ቀጭን ሂም፣ ለታችኛ ው ከንፈሩ የኩራትና የቁጣ መልክ ፈጥሮለታል። ከዚህም በተጨማሪ ራሱን ሊከበር በሚችል የጨዋ ሰው ግርማ ሞገስ ጠብቋል። በሉል የተጠለፈ እጅጌው፣ ከውብ ጨርቅ የተሠራ ግራጫ ቡኒ ልብስና የሐር ሰደሪያ ለብሷል። ነጫጭ ላባዎች ያሉበት ባለሦስት ማዕዘን ባርኔጣ በእጁ አንጠልጥሏል።

«ለመሆኑ ልትለየኝ ትችል ነበር?» ሲል ጆን ባፕቲስት እየሣቀ ጠየቀው

«ይህ አማማቅህ ስህተት የለበትም» አለው ፕሮቴስታንቱ፣ጓደኛውን እንደገና ጭምቅ አድርጎ እያቀፈው።



«እንግዲህ ጊዜ አናጥፋ። ፈረሴ በመተላለፊያው ፊት ለፊት ባለ አንድ ቀለበት ላይ ታስሯል። ወጣ ብለህ በጓሮ በኩል ወደ ቤኖቹ ጋጣ ውሰደው» አለው ጆን ባፕቲስት

ከነርሱ ቤት በስተጀርባ፣ በቤኖቹ የንግድ ተቋም የሚመራ የማሰልጠኛ ሜዳ አለ። አንድ ዘመን ላይ ይህ ቦታ በጣም የበለፀገ እንደነበረው ሳይሆን፣ ዛሬ ብዙ ሰፋፊ ባዶ ሥፍራዎች ስላሉት ጐረቤቶች ሁሉ በነፃነት ሊጠቀሙበት የሚችሉት ሆኗል። ሜትር ዠረሚ ፈረሱን ወደ ጋጣው ለማድረስ ወጣ። ሲመለስ የጆን ባፕቲስትን ከባድ ኮርቻ በአንድ ክንዱ ላይ ተሸክሞ፣ አራት ማዕዘን የሆነውን ሻንጣውን በሌላው ትከሻው ላይ አድርጎ መጣ።

ጆን ባፕቲስት በላይኛው ፎቅ ከእዕዋቱ ጋር ነበር። እዚያም፣ ልክ ክፍል ሙሉ እንዳሉ ወላጅ አልባ ህፃናት፣ እያንዳንዱን ተክል በቅጠሎቻቸው ላይ እጆቹን እያሳረፈ ሰላምታ ይሰጣቸዋል።

«መረን ሆነው እያደጉ ነው» አለው ለሜትር ዠረሚ። በድምፁ ውስጥ ምንም ዓይነት ዘለፋ አልነበረበትም። ይልቁንም ተማሪዎቹ አንታዘዝ ያሉት የትምህርት ቤት መምህር የፍቅር ምፀት ይመስላል።

«እህ! የተረገመ!» አለ ሜትር ዠረሚ ወዲያና ወዲህ ከተራመዳት እንቅስቃሴው ረጋ ካለ በኋላ። «ፓሪስ ውስጥ ለፍርድ ቀርበሃል ብለው ነበር ሲነግሩን የነበረው። እንዲያውም በተግባርም አስረውሃል ብለን ስናስብ ነበርን»

«ታስሬ ነበር። ይሁንና ያ ሁሉ አይመለከተኝም። ምክንያቱም፣ ያ ያጋጠመው ሌላ ሰውን ነው። አሁን ከፊትህ ያለው ሰው ከልዑል ዴ ኮንቲ ቤተሰብ የሆነው ፈረሰኛው ሁፌስ ዴ ቫ ው ዴ ሶሬስ እንጂ ሌላ ሰው አይደለም»

ዝቅ ብሎ የአክብሮት ሰላምታ አቅርቦ ፈገግ አለ።

«አሊስ እንዴት ነች?» ሲል ለወጥ ባለ የድምፅ ቅላፄ ጠየቀው። ሜትር ዠረሚም ሁኔታውን ሁሉ በአንድ ጊዜ አስታወሰ።

«እስከ አሁን ፓሪስ ነህ በሚል ታስብ ነበረና ትናንት ጠዋት ከዚህ ለቀቀች።»

«ለቀቀች? እንዴት? ማነው ይህን . . . » አለ ጆን ባፕቲስት

«በሁለት ጉራጌ ታጣቂዎች ታጅባ ነው የወጣችው። የጉዞዋ አቅጣጫ ወደ አሌክሣንደሪያ ሲሆን እዚያም ወደ ፈረንሣይ በሚያደርሣት መርከብ ላይ ትሣፈራለች። እዚያ ከደረሰች በኋላ ደግሞ ወደ ገዳም ትወሰዳለች»

ጆን ባፕቲስት በመገረምና በቁጣ ጮኸ።

ሜትር ዠረሚ በበኩሉ ጓደኛው ምንም ዓይነት ወሬ አስቀድሞ ባለመሰማቱ፣ በመወቀስ ቆጣ ብሎ መሰለለት። ሁለቱም እርስ በእርሣቸው መጠያየቅ ጀመሩ። በዚህ መሃል እንዳቸውም ጊዜ ወስደው መልስ ለመስጠት ፍላጎት አልነበራቸውም።

ድምፁን የሰማችው ፍራንቾይዝ በመስኮቷ በኩል ዘላ ብቅ አለች። ሁለቱ ሰዎች በደረጃው ላይ ዱካዋን ስለሰሙ መናገራቸውን አቋረጡ። ጆን ባፕቲስትም ለመሸሽ በመዘጋጀት ወደ ፎቁ መውጫ ደረጃ ዳኸ።

«ቆይ፣ ፍራንቾይዝ ነች» አለ ሜትር ዠረሚ በሃፍረት ዐይኖቹን እያሻሸ።

«ወደ ሶውቢይራን ሄጄ ነበር። ማሪኔ ከአስራ አምስት አመታት በፊት አርፋለች» ሲል ጆን ባፕቲስት ራሱን አረጋግቶ ፍራንቾይዝን ከማቀፉ በፊት ሹክ አለ።

በመመለሱ የተሰማትን እግራሞትና ደስታ በነፃነት ገለፀች። ይሁንና ተፈጥሯዊ ባህርይዋ ወዲያውኑ አጭሮ፣ ጆን ባፕቲስት ምግብ በልቶ እንደሆነ ጠየቀችው። በርግጥ ጠኔ ጥሎታል። በጠረጴዛው አጠገብ ለሁለቱ የሚሆን ቦታ አዘጋጁ። ሜትር ዠረሚ ከጉሬው ውስጥ ሲያመሳቅል ቆይቶ፣ አንድ ጠርሙስ ይዞ እስኪመለስ ፍራንቾይዝ ወደ ክፍሏ ወጥታ የተቀቀለ ጉመን፣ የስጋ ወጥና ትልቅ የዳቦ ቁራጭ አመጣች። ጆን ባፕቲስት ምግቡን እየተስገበገበ ሲበላ ሜትር ዠረሚ አስቀድሞ ተናገረ።

ፍራንቾይዝ፣ የወጣቷን እመቤትዋን ምስጢር አሣልፋ ስላልነገረችው፣ስለ አሲስ መሄድ በይፋ የሚያውቀውን ታሪክ ነገረው። ከዚህም በመቀጠልም እርስዋን ለመከተል ስለታቀደው ሃሣብና በዚህም መሠረት በሚቀጥለው ዕለት ጉህ ሲቀድ ሊንቀሳቀሱ እንደነበረ አስረዳው። ጆን ባፕቲስት ለሃሣቡም፣ ለዕቅዱም አጨብጭቦ፣ ይሣካ ዘንድ ዕዋቸውን አነሱ። ይህ ሁኔታ ይበልጥ ሃይል ሰጣቸው። ከዚህ በኋላ የውጣ ውረድ ገድሉን መግለፅ፣ የጆን ባፕቲስት ተራ ነበረ። በተቆራረጠ ሁኔታ ስለጉዞው፣ ከንጉሡ ጋር ስላጋጠመው ስብሰባ፣ ከዚያም ስለተከተሉት ችግሮች፣ ስለማምለጡና ፕሮቴስታንቶቹን ስለማግኘቱ ተራ በተራ ዘረዘረ። በዚህም ለሁለተኛ ጊዜ ዋንጫቸውን ከፍ አደረጉ።



«የሆን ሆኖ ሙራድስ?» ሲል ጆን ባፕቲስት ጠየቀው

«ለጉዞው የሚያስፈልገውን ወጭ የሚከፍሉት ጥቂት በጐ አድራጊዎችን ስላገኘና፣ ሊሆን የሚገባውም ድንቅ ውሳኔ ነበርና በቅርቡ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ።

«ስድስት ሰዎች ናቸው አይደል?»

«እምን፣ ግን እንዴት አወቅህ?»

«በፈረንሣይ ቤተመንግስት የተላኩ ጀስዊቶች ናቸው» አለ ጆን ባፕቲስት ዳቦውን እየገመጠ። «እኔ ከንጉሡ ጋር የነበረኝ ግንኙነት ከተበላሸ በኋላ፣ ንጉሡ ለነፍስ አባታቸው ይህንን ቃል ገቡላቸው። ይህን አዲሱን ተልዕኮ ለነፍስ አባታቸው እንደ ስጦታ፣ ሳለፈውም እንደውለታ አድርገው ነው ትዕዛዝ የሰጡት»

«እንዲህ ከሆን የንጉሡ ነገስቱን መልዕክት ልታቀርብ አልቻልክም ማለት ነው?» አለ ሜትር ዠረሚ።

«ይህን በተመለከተ ጊዜ አልነበረኝም። ከዚህም በላይ መልዕክቱን ለመሰማትም ፈቃደኛ የሚሆን፣ ነበረ ብዬ አላምንም»

«አ! አየህ ጆን ባፕቲስት፣ እነዚህ ጀስዊቶች እንደሚያሸንፉ ርግጠኛ ነበርኩ፣ አንተ ግን ከነርሱ ጋር ህብረት የምትፈጥር መስሎህ አስበህ ነበር» አለው ፕሮቴስታንቱ ፊቱን ከስክሶ።

«ወደ ቬርሣይለስ መሄድ ከተገባኝ ሌላ ምርጫ አልነበረኝም»

«ለመሆኑ ወደዚያ ለመሄድ ያን ያህል የቆረጥከው ለምንድን ነበር?» ሲል፣ዐይኖቹ ከአምላኩ ጋር ሲከራከር እንደሚሆኑ አስፈሪ ሆነው ጠየቀው። «የራስህን ጉዳይ በግንባር ቀርበህ ልታስረዳና የአሊስን እጅ ለማግኘት ሙከራ ከማድረግ ሌላ ምክንያት አልነበረህም»

«አንተ ጉዳዩን በጣም አጠንክረህ እየገለፅከው ነው። ከዚያ ባሻገር ንጉሡን ለማግባባትና ላገለግላቸውም እችላለሁ የሚል እምነት ነበረኝ» ሲል ጆን ባፕቲስት በደስታ ተናገረ።

«ቀስ፣ ቀዝቀዝ በሉ» አለች ፍራንቾይዝ! የሁለቱ ሰዎች ድምፅ አሣስቧት። «የሆነ ሰው ሊሰማችሁ ይችላል። አሁን ይህን ለመነጋገር ጊዜውም አይደለም»

«ያም ሆነ ይህ» ሲል ሜትር ዠረሚ ለስለስ ባለ ሁኔታ ቀጠለ። «ውጤቱ በግልፅ የሚታይ ነው። ያንተን ተልዕኮ ተከትሎ በአቢሲኒያ ላይ ድንገተኛ ጥቃት የሚጥሉ ሁለት ቅፍለቶች እየገሰገሱ ናቸው። የሚከፍላቸውም የፈረንሣይ ንጉሥ ነው። ምንም ዓይነት ጀስዊቶች እንደማይኖሩ ምለን ተገዝተን ሣለን፣ አሁን ደግሞ የሙራድን ጭራ ተከትለው

የሚሄዱ ስድስት መጥተዋል። ንጉሡ ነገስቱ የፈለጉት አንተን እንደ አምባሣደራቸው ነበር። ነገር ግን ባንተ ፈንታ ዱ ሮውሴን መርጠውታል። በሚደርሱን መረጃዎች አማካኝ መኮንን በአገር ውስጥ ባለው መጥፎ ሁኔታ ከትልቅ ቤተሰብ የተወለደ ውዳቂ ሰው ነው።»

ፍራንቾይዝ በመፍራት ጉሮሮዋን አጠራች

«ይቅርታ አድርጉልኝ። ከሁሉም በላይ እኔ የምሻው በመሃከላችሁ ሰላምን እንድትፈጥሩ ነው። ስለአቢሲኒያ ስለምታወሩ፣ ቆንስላው ግቢ በነበርኩበት ጊዜ የሰማሁትን ጥቂት ነገር ልንገራችሁ»

ከዚህ በኋላ በሙሴ ዱ ማይሌና በወንድም ፖስኪል መካከል የነበረውን ቃለ መጠይቅ ዘረዘረችላቸው።

«ይህማ ሃሰት ያደርጋቸዋል ማለት ነው» አለ ሜትር ዝረሚ። «አሁን ያልተካተቱት ካፑቺኖች ብቻ ናቸው። እነርሱ ደግሞ ቅብዓ ሜሮኑ አላቸው። ይህም ቢሆን የኮፕቲኩን ፖትርያርክ የጋለ ስሜት ያነሣሣ አልነበረም። ይገርማል! የሠራነው ሁሉ ያሣፍረኛል»

«እኔንም ያሣፍረኛል ዝረሚ» አለ ጆን ባፕቲስት፣ ዓይኖቹን ሰብሮ። «የማትተቸኝ ከሆነ ልንገርህ። እኔ የሠራሁትን ሁሉ ያከናወንኩት በንፁህ ልብ ነው። ይህም ሆኖ አልተሣካልኝም። ስመለስም በጉዞዬ ላይ እንዳችም ሌላ ነገር አላሰብኩም»

ሜትር ዝረሚ የብርጭቆውን ውስጥ አጮልቆ ተመለከተና የሆነ ነገር አጉተመተመ

«እየሀ» ሲል ጆን ባፕቲስት ቀጠለ። «ወደዚህ በመንዝ ላይ እያለሁ እኔም የራሴን እቅድ አውጥቼ ነበር። በዚህ ዕቅድ ውስጥ የአሊስን መሄድ አስመልክቶ አንድም ነገር አላሰብኩም። ምክንያቱም መሄድዋን አላውቅም። ስመኘው የነበረው ማንም እንደሚያደርገው ላያት መጓጓት ብቻ ነው። ከዚህም በላይ ሌሎች ልከታተላቸው የሚገቡኝ ሥራዎች ነበሩኝ።»

ጆን ባፕቲስት፣በረዘሙና በትንሹ ጢሙ ሆኖ ሲታይ፣ ባለፈው ክፍለ ዘመን እንደሚታወቀው ገና ብዙ ትግልና ጦርነት እንዳለበትና፣ ሣንግራይ እንዳሉት ክብሩን የማያስነካና ለዚህም ሲል ማንነቱን በሕይወቱ ለመጠበቅ እንደሚዘጋጅ ሰው አስፈሪ ነው።

«እናንተ ልታከናውኑት ባቀዳችሁት ዓላማችሁ ትቀጥላላችሁ። ስለኔ ከእንግዲህ መጨነቅ የለባችሁም። ነገር ግን በጠረፍ አካባቢ ሄዳችሁ መርከብ ላይ ከምትሳፈሩ ወደ ምስራቅ ማለትም ወደ ስዊዝና ወደ ሲና ተራራ ትሄዳላችሁ። ዝረሚ? ለመሆኑ ወደ ግብፅ ለመጀመሪያ ጊዜ ስንመጣ አንድ ወር ያህል የከረምንበትን ገዳም ታስታውሰዋለህ?» አለው

«የወንድ መነኩሣቱን አለቃ በትክክል ማታቸው ምክንያት ያከምካቸው ቦታ ነው?»



«በትክክል። እዚያ ሄዳችሁ ትደበቃላችሁ። እንዳይከታተሏችሁ ጥንቃቄ ካደረጋችሁ ማንም ሊያገኛችሁ አይችልም። እኔ የማከናውነውን ሥራ እንደጨረስኩ እዚያ መጥቼ እገናኛችኋለሁ።»

ሜትር ዝረሚ በድንነት ፀፀት ተሰማው

«ጆን ባፕቲስት፣ እስቲ ተከተለን። ስላለፈው ብቻ ሣወራህ ቆየሁ። ነገሮች ሁሉ እንደነበሩ ናቸው። ይህ ደግሞ ምንም አይደለም። አቢሲኒያውያኑ ለዘመናት እንዳደረጉት ሁሉ ራሣቸውን ይጠብቃሉ»

«የለም፣ አይደለም ዝረሚ። ያለፈው የሚቋጨውና የሚቀረው ከኛ ሞት በኋላ ነው። እኔ አሁንም ገና እዚህ የማከናውነው ጉዳይ አለኝ። ቃላቸውን የሚጠብቁ አይደሉም ሲሉን የሚችልም ሰው አይኖርም»

ካይሮ፣ በሰላዮችና በጆሮ ጠቢዎች የተሞላች ስለሆነች፣ምናልባት ለይተው ቢያውቁት ስሙን እንደሚያጠፉበት በመናገር ፍራንቾይዝ አስጠነቀቀችው። ሜትር ዝረሚ፣የደረሰባቸውን ተፅዕኖ ማየት ስለቻለ፣ ቀደም ሲል ያደረበትን ፀፀት የሚያስወግድበትን ዘዴ ማሰብ አልቻለም። ጆን ባፕቲስት፣ ተቃውሞአቸውን ድርቅ ብሎ አልቀበልም በማለት ዝም አሰኛቸው። ከአንድ ሰዓት ለበለጠ ጊዜ ያህል እርሱ ከሄደ በኋላ በማህበረሰቡ ውስጥ ስለነበረው ሕይወት፣ ስለመድሃኒት ቅመማው የንግድ ሥራቸው፣ ስለ ዱ ሮውሴ ቅፍለት ሲጠይቃቸው ቆየ። ሜትር ዝረሚም ጥንቃቄ ሲያደርግላቸውና ሲንከባከባቸው የነበሩትን ሕሙማን የስም ዝርዝር ሰጠው።

በመጨረሻም ዕረፍት ለማድረግ ሃሳቱም ተስያዩ። ከማለዳው አስራ ሁለት ላይ ገና የመጀመሪያው የንጋት ብርሃን ሲወጣ ሜትር ዝረሚና ፍራንቾይዝ ሻንጣዎቻቸውን ሰብስበው ከትናንት በስቲያ ምሽት ጆን ባፕቲስት ፈረሱን ካሰረበት ጋጣ፣ የራሣቸውን ፈረሶች አውጥተው አዘጋጇቸው። ፍራንቾይዝ እንደ ወንድ ለብሣለች። የቦት ጫማ ተጫምታ ሰፊ ክፈፍ ያለው ባርኔጣም አድርጋለች። ሜትር ዝረሚም ትንሽ ረዘም ከማለቱ በስተቀር ተመሣሣይ ቁመና አለው።

ደህና ሁኑ፣ ብሎ በመልካም ምኞት ሲሰናበታቸው፣ ጆን ባፕቲስት ጥልቅ የስሜት ማዕበል ተሰማው። ከእንግዲህ በኋላ ለመገናኘት ርግጠኛ ሳይሆኑ፣ ለመጨረሻ ጊዜ ተለያዩ። ግማሽ ሰዓት ያህል ቆይቶ፣ በአትክልቶቹ መሃል ለመጨረሻ ጊዜ ከተመላለሰ በኋላ ጥቂት ዘሮች ወስዶ በኪሱ ውስጥ ከተተ። ሜትር ዝረሚ የተወለትን ትንሽ የመድሃኒት ሣጥን ትክሻው ላይ አድርጎ ወጣ። ከአንድ ቀን በፊት እንደመጣ ወዳረፈበት፣ ወደ ከተማው የድሮ ሰፈር፣ ባዝራውን ወዳሰረበት ቦታ በቀላሉ እጥፍ ብሎ ተራመደ።

# 6

በመጀመሪያው ዕቅዳቸው መሠረት አሊስና ግብረአበሮችዋ ከአሌክሣንደሪያ ጥቂት ራቅ ባለ ቦታ ጠባቂዎችዋን አስወግደው በሴሬናይካን ጠረፍ ጠዳሰ ወደብ በመሸሽ በመርከብ ሆነው ፈረንሣይ ይደርሣሉ:: ፍራንቾይዝና ሜትር ዠረሚ እርስዋ ጉዞ ከጀመረች ከሶስተኛው ቀን በኋላ ጠባቂዎችዋ ላይ የደፈጣ ጥቃት ካደረሱ በኋላ ያገኙአትና አብረው ይሆናሉ::

አሁን ሁሉም ነገር ተለውጧል:: እነርሱ አቅጣጫቸውን በምሥራቅ በኩል ወደ ስዊዝ አድርገዋል:: እርስዋን ለመድረስ መዘግየታቸው አይቀርምና ይህ ደግሞ ከባድ ችግር ይፈጥራል:: ምክንያቱም እነርሱ አቅጣጫቸውን እንደገና በደለሉ ምድር በኩል እስከ ማቋረጫው በመሄድ፣ወደ አልማንሱራ አቋርጠው ከዚያ ወደ እስማኢሊያ መሄድ ይኖርባቸዋል:: ከፍራንቾይዝ ጐን ሆኖ በመጋለብ ላይ እያለ አዲሱ ዕቅድ ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ አሰበ፣ ነገር ግን ፀሐይዋ ከአድማስ በላይ ወጥታ የአባይን ሜዳማ አገር እንደብርድ ልብስ ያፈነውን ጭጋግ ስትዳስሰው፣ብቸኝነትን ለምዶት የነበረው የኘሮቴስታንቱ መንፈስ መጠናከርና ለግልቢያውም ስሜቱን ነፃ ማድረግ ጀመረ:: አልፎ አልፎ ፍራንቾይዝ እየተመለከተችው ፈገግ ትላለች:: እንቅስቃሴውና በወንዙ ዙሪያ ያለው የነፋሱ ሽውታ ጉንጮችዋን ማቅላት ጀምረዋል:: ፀጉርዋ በባርኔጣዋ ሥር ሲሸፈን፣ በአንገቷ ዙሪያ ያለው ፀጉር ምን ያህል ለስላሳ እንደሆነ ሲገነዘበው በግልጽ የሚታይ መሆኑን ሜትር ዠረሚ አወቀ:: እነዚህን ሁለት ግለሰቦች ማየት አስደሣች ነገር ነው:: ሁለቱንም ዕጣ ፈንታ ፈትኗቸዋል፣የሕይወት መከራና ጊዜም ክፉኛ አደድሯቸዋል:: አሁን ደግሞ በትክክል ስሜት እያበቡ፣ ፍፁም ልስልስ ያሉና ከወደመ ከተማ ውስጥ ምንም ሳይሆኑ በመትረፍ የወርቅ ሣህናቸውን ከተደበቀበት እንደሚያወጡ ለዛ ያላቸው ሰዎች ይመስላሉ::

ወደ ጠረፍ እየወረዱ ሲሄዱ፣በዛታቸው የሚጨምር የባህር ወፎች በውሃው ላይ ግራጫና ነጭ እየሆኑ ይንሸራተታሉ:: መንደሩ ውስጥ ከገቡ በኋላ ጥምጣም ያላቸው ብዙ ሽማግሌ ወንዶች አጋጠሟቸው:: እጅግ ሰፊ የሆነው የባላገር መሬት በሸክላ የመስኖ ቦዮች መረብ ተሸፍኖ፣ ተራ ግራጫ ሸሚዝ የለበሱና እነርሱን በፈርኦኖች ዐይን የሚመስኩ ሠራተኞች ተወርሯል:: በጨዋማው ነፋስ የተበታተነውና በዘንባባ ዛፎች አጠገብ ያለውን ሣር



የደለቡ በሬዎች ይግጣሉ:: እነርሱ ራሣቸው መልሰው ያገኙት የወጣትነት፣ስሜታቸው በዙሪያቸው ያለውን የተለመደና ቀላል የሆነውን የዓለምን ወጣትነት እየተመገበ ይመስላል::

የአሊስ ክባድ ጓዝ ከሁለት ቀናት ጉዞ በኋላ አዳር ያደረገበትን፣ ደማንሱር ከተማ በአንድ ቀን ደረሱ:: የቆንሲሉ ሴት ልጅ፣ ከአንዲት ባሏ ከሞተባት ሴት ጋር ትቆያለች:: የዚህች ሴት ሟች ባል፣ ቤትሎራት ይባል የነበረ ፈረንሳዊ ነጋዴ ነበር:: ይህ ሰው እስከሞተበት ዕለት ድረስ በዚያች ትንሽ ከተማ የቆንሲሉ ቃል አቀባይ ሆኖ ሲያገለግል ነበር:: ፍራንቾይዝና ሜትር ዠረሚ ጥራት በሌላትና ኮንቶች በሚያስተዳድሯት ደረቅ ጣቢያ አደሩ:: ጋብቻቸውን ማረጋገጥ ስላልቻሉ ሁለቱም ሁለት የድርቆሽ ፍራሽ ተሰጧቸው፣ ከዘንባባ ስሌን በተሠራ መጋረጃ በተከፈለ ቦታ ሆኑ:: ይህ ዝግጅት ቁመናቸው እንዳይጋለጥ ረዳቸው:: የተትረፈረፈ የዶሮ አሮስቶና ቢጫ ሩዝ ከበሉ በኋላ፣ ሽማግሌው ኮንት፣ በጥርስ የለሹ ድዳቸው በመተባበር ዓይነት ፈገግታ ደህና እደሩ ብለዋቸው ሄዱ:: ከእራት በኋላ ወገብ ለወገብ ተቃቅፈው ከተማዋን በሙሉ ዞሯት:: ከርቀት የአሊስን ሰረገላና የጠባቂዎችዋን ፈረሶች በከተማዋ ውስጥ ካሉት ጥቂት የድንጋይ ቤቶች አጥር ግቢ ውስጥ ተመለከቱ:: ይህን እርግጠኛ ከሆኑ በኋላ፣ ወደማረፊያቸው ተመለሱ:: ሜትር ዠረሚም አስተዳዳሪው ከንጋት በፊት እንዲቀሰቅሷቸው አደራ አሏቸው:: የመጀመሪያው የቀን ብርሀን ከመፈንጠቁ በፊት ማረፊያቸውን ትተው ወደተመረጠው ቦታ አቀኑ::

የአሊስ ጓዝ በዝግታ ተንቀሣቀሰ:: የቆንሲሉ ፈረስ አጣቢ ሚካኤል፣ ከሰረገላው ልጓም አጠገብ ነው:: ሙሉ ታሪክ አልተነገረውም እንጂ የሆነ ነገር መጠንሰሱ ገብቶታል:: በመሆኑም እንቅፋት መሆን አልፈለገም:: አሊስን እንደራሱ ልጅ ስለሚያፈቅራት ወደ ገዳም ሲወስዳት ልቡ ተሰብሯል:: በሌላ ወገን ሁለቱ ዘበኞች ተግባራቸውን ከልብ ተቀብለው ሌሊቱን ሙሉ በአሊስ በር ፊት እንዳወሩ ነበር ያደሩት:: ሁለቱም ወሮበላዎች ሙሉ በሙሉ የሚያመሰግኑት ሙሴ ማቼን ነበር:: አንዱ ፈረንሣዊ ነው:: ይህ ሰው ከሶስት ዓመት በፊት ከጦር መርከብ ላይ ነፃ ተለቅቆ ያለምንም የሰነድ ማስረጃ አቡኪር ውስጥ ይኖራል:: በቱርኮች በተያዘበት ጊዜም እንዲያድነው የቆንስላውን ፀሐፊ ተማጠነው:: ከዚያም ወዲህ በማያጠያይቅ ሁኔታ ታማኝነቱን አረጋገጠ:: ሁለተኛው ሰው፣ ከካይሬን የመጣ፣ ከሕግ ውጭ በኢጣሊያዊና በኮፕት መካከል በተደረገ የፍቅር ግንኙነት የተወለደ ዲቃላ ነው:: ይህ ሰው በአባይ የጭነት ወደቦች ላይ ዘበኛ ሆኖ ሰርቷል:: ሙሴ ማቼ፣ የዜግነት ወረቀት እሰጥሃለሁ በማለት ከረዥም

ጊዜ በፊት ቃል ገብቶለት ነበር። ለዚህ እርግጠኛነት ለሌለው ተስፋ፣ በምላሹ ለማንኛውም ድንገተኛ ሥራ ሊጠራው እንደሚችል ነግሮታል።

ሠረገላው ጉዞ ሊጀምር ሲል አዲስ ችግር ተፈጠረ። አሊስን ያስተናገደችውና ባሏ የሞተባት ቤአትሪስ፣ ጉዞውን እቀላቀላለሁ ስትል ወሰነች። አሌክሳንደሪያ ውስጥ የምትሠራው ስራ ስላላት በቆንሲሉ ሠረገላ መጓዝ ፈለገች። ወዲያውኑ የጠባቂዎቹ ነገር ከፊቷ ድቅን አለባት። ይህም ቢሆን በጥቂት ሣንቲሞች እሽታ ሊያስገኝ ይችላልና ችግር አይደለም ስትል አሰበች፣ ለርስዋ የሚሆን ቦታም ተዘጋጀላትና ጉዟቸውን ቀጠሉ። ጓደኞችዋ፣በትርኢቱ ላይ በማንኛውም ጊዜ በድንገት ፀቡን እንደሚጀምሩ ስላወቀች ፖቤውና ሽጉጡ ያለበትን ሻንጣዋን እግሯ ስር አደረገችው። ይሁንና ለአደጋው ለመዘጋጀት ጊዜ ከመግዛት ይልቅ በቅናት ላይ ለነበረው ጭውውት ምላሽ በመስጠት መቀበጣጠር ጀመረች።

«ውይ፣ የኔ ኮረዳ» አለች ወይዘሮ ቤአትሪስ፣ ማር ማር በሚል ቅላጼ። «በመስኮቱ አሻግረሽ እንደዚህ ማየትሽን ተይው! ራስሽን ትጐጃለሽ። ይህን የምትመለከችውን የመሬት ገፅታ መልክ ትተሽው የምትሄጅው ነው። ይልቅስ ከእንግዲህ በኋላ እስከዘለዓለሙ ስለምታመልኪው ስለ ሰማያዊው ውበት ብታስቢ ይሻልሻል»

«ማዳም፣ አውቀውልኝ ከሆነ እኔም ስለመፃኢው ተስፋ ነው የማስበው»

«ገባኝ። አየሽ፣ እኔም ሙሉ በሙሉ ቀናተኛ መሆኔን ስትገነዘቢ ትደነቂ ይሆናል። ሕይወቴ በርግጥ የተለየ ዓይነት ነበር። ዕድሜዬን በሙሉ ለባሌና ለልጆቼ በታማኝነት ነበርኩ። ይሁንና አንዳንድ ጊዜ ለመሆኑ እኔ ለእግዚአብሔር አገልጋይነት አልተፈጠርኩም ይሆን? እያልኩ ራሴን እጠይቀዋለሁ።»

«የማይደንቅ ነው» አለች አሊስ አሁንም በመስኮቱ በኩል እየተመለከተች።

«አይደለም እንዴ? ሕይወቴን ሙሉ ላገኘው የምጓጓለትን ሰላም፣ ሃይማኖታዊው ሕይወት ያስገኝልኛል ብዬ አምናለሁ።»

ሃር የመሰለውን ልብሷን ለብሣ፣ በባለፈው ክፍለ ዘመን ዘይቤ ፀጉርዋን ጠቅልላ ያለችው የተጨማደደችው አሮጊት እመቤት፣ የእግዚአብሔር አገልጋይ ብትሆን ኖሮ ምን ያህል ትወደድ እንደነበረ ለመግለፅ የድንግልና ስሜት ታሰባት።



«ታውቂያለሽ፣ ራሴን ለእግዚአብሔር አገልጋይነት አሳልፌ በሰጠሁበት ጊዜ ባለቤቴ ቀንቶ እንደነበረ?»

«ይሀ እውነት ሊሆን ይችላል እንዴ?» ስትል አሊስ በትህትና ጠየቀች

ለግማሽ ሰዓት ያህል አሰልቺ ከነበረው ውይይት በኋላ፣ ሠረገላው ከፉኛ በሚታጠፍ መንገድ ላይ ዝግ ሲል ሁለት ፈንጂዎች በርጥበት አዘሉ አየር ውስጥ ተንዷዱ። አሊስ፣ ወደ መስኮቱ ፊጥና ብትንቀሣቀስም ምንም ማየት አልቻለም። በኋለኛው መስኮት ላይ ፊትዋን አስጠግታ ተመለከተች። ከአጃቢ ጠባቂዎቹ አንዱ ተመትቶ ኖር መሬት ላይ ወደቀ። ሚካኤል ሠረገላውን አቆመው። ሁለተኛው ታጣቂ ፈረሱ ላይ እንጣጥ ብሎ ለመውጣት ስለቻለ ወደ ሠረገላ ነጂው ደረሰ። ፈረሶቹን በሃይል እየገረፈ እንዲያስጋልባቸው አዘዘው። በዚያኑ ጊዜ ከአትክልቱ ሥፍራ በስተጀርባ፣ ከደረቁ የድንጋይ አጥር በኋላ በፈረስ ላይ ሆኖ ሲያሣድደው የነበረው ሜትር ዠረሚ፣ ዘበኛው ላይ ተወርውሮ ደርሶበት የታጠቀውን ጐራዴ መዘዘበት። ዘበኛውም፣ ጐራዴውን ከሰገባው ፈጥኖ በመምዘዝ መፋለም ጀመሩ።

የመጀመሪያ ስሜቷ ድንጋጤ የነበረ ቢሆንም፤ እግዚአብሔር በአዲስ ፈተና ውስጥ እየከተተኝ ነው ስትል ማዳም ቤአትሪስ ገመተች። ምርር ብላም እንደ እንስሳ በማላዘን አለቀሰች። በመስኮቷ በኩል ጦርነቱን በከፍተኛ ጉጉት ትከታተል የነበረችው አሊስ፣ ዞር ብላ፣ አሮጊቷ ዝም እንድትል ነገረቻት። ሴትዮዋ ግን የባሰውኑ በከፍተኛ ድምፅ አምባረቀች። ለዘለዓለም በማይረሣት ሁኔታ፣ ወጣቷ ሴት ወደ አሮጊቷ በቀጥታ ዞራ፣ ምንም ሣትናገር ሁለት ጊዜ ፊቷን በጥፊ አጮለችው።

«ዝም ትይ እንደሆነ ዝም በይ፣ አንቺ ጨርጫሳ አሮጊት!»

እጆችዋን በነደዱት ጉንጮችዋ ላይ አድርጋ፣ በሠረገላው ዙሪያ እየተከናወነ ያለውን ድርጊት ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ እያለ በፍርሃት መመልከት ጀመረች። ከጥቂት ጊዜያት በፊት በከባድ ፀሎት ውስጥ የነበረችውና የክርስቶስ እጮኛ የሆነችው መነኩሲት፣ የለበሰችውን ምቾት የለሽ ልብስ አውልቃ የፈረሰኛ ልብስ ለብሳ ተመለከተቻት። ልጃገረዲቱ በመቀጠልም ወለሉ ላይ ያለውን የቆዳ ቦርሣ ከፈተችው። የተጫማችውን አውልቃ በመወርወር እንደቸከላት ቡኒ የሆኑ ባለዘለበት ቦት ጫማዎችዋን አጠለቀች። ከውጭ የጐራዴዎች መጋጨት አሁንም ይሰማል። ሜትር ዠረሚ የሚያይል ቢመስልም ሌላኛው ሰው ራሱን በሃይል ይከላከላል። በቅፅበት የሁኔታዎች አቅጣጫ ተለወጡባቸው። ፈረሰኛ የቱርክ ወታደር በዚህ ጠመዝማዛ

መንገድ ላይ እየጋለበ ሲደርስ፣ እንዲቆም የተደረገውን ሠረገላ ተመለከተ። ጥቃት አድራሹ ማን እንደሆነ ለመለየት ብዙም ጊዜ አልወሰደበትም። ይህ ወታደር፣የደንብ ልብስ ለብሶ የቀረውን፣ የማቹን የቤት ሠራተኛ ለመርዳት ቆልማማውን ጉራዴውን ይዞ ተጣድፎ ገባ። ሜትር ዠረሚ ወደ ኋላው ፈንጠር አለ። ፍራንቾይዝ ከአጭሩ አጥር በስተጀርባ መሆንዋን በግርግሩና በትርምሱ መሃልም ሽጉጧን እንዳትጠቀም በርቀት ላይ እንደሆነች፣ አሊስ ተመለከተች። አሁንም በሰረገላው ውስጥ ሆና በመነፋረቅ ላይ ወዳለችው አሮጊት ዘንድ ተመልሳ በመግባት ከትናንት ምሽት በፊት አቀባብላው የነበረውን ሽጉጥ አሊስ ያዘች። አነጣጥራም የባሩድ ማቀጣጠያውን አስተካከለችው። ተዋጊዎቹ ከርሷ ራቅ የሚሉት ጥቂት ርምጃዎችን ብቻ ነው። ብቸኛው የቱርክ ወታደር በአይታዋ ውስጥ እስኪገባላት ጠብቃ ተኮሰች። የቱርካዊው የጉራዴ እጄታ ሽቅብ ጉኑ። ጥይቱም በቀጥታ ደረቱን በጥርቶ በሌላው በኩል ወጣ። ወዲያውኑ እጥፍጥፍ አለ። ተባባሪ ጓደኛው መመታቱን በመመልከት፣ ከቆንስላው የመጣው ጠባቂ፣ በዠረሚ ፊት ለአፍታ ያህል ፈዝዞ እንደቆመ፣ የዠረሚ ጉራዴ ፊቱን ለሁለት ሰነጠቀው። ሁለተኛው እንቅስቃሴው ልቡን በጠረቀው። ጠባቂውም ከፈረሱ ላይ ወደ ኋላ ዘፍ ብሎ ወደቀ።

አሊስ በደስታ ጮኸች። ይሁንና ልታጠፋው የምትችለው ጊዜ አልነበራትም። ፍራንቾይዝ የወደቁትን አስከሬኖች ከመንገዱ ወደ ዳር በመጐተት ከግድግዳው ኋላ ደበቀቻቸው። ሚካኤልም ሠረገላውን ወደ ኋላ ዞር አድርጐ በዘንባባ ዛፎች አጠገብ ደበቀው። ሜትር ዠረሚ፣ ሽማግሌውን የጋሪ ነጂ ወንጀሉ ሲፈፀም በቦታው እንዳልነበረ ለማረጋገጥ እንዲቻል ጠበቅ አድርጐ አሰረው። አሊስ ራሷ የአሮጊቷን ቤአትሪትን አፍ ለጐመች።

«ያየሽውን ሁሉ በሚገባ አስታውሺ» አለቻት እያዘነች። «እኔ ራሴ በሁለት ቱርካውያን ሽፍታዎች ታፍኜ ነበረ። ከዚህ የተለየ ብትናገሪ ጓደኞቼ ተመልሰው መጥተው ነፍስሽን ወደ ሰማይ ቤት እንድትቀርብ ያደርጓታል»

ከዚህ በኋላ ሣቀች

«እና በገዳሙ ውስጥ አሁንም የኔን ቦታ የምትፈልጊው ከሆን ነፃ ነው»

ከዚህ በኋላ በአንደኛው ዘበኛ ፈረስ ላይ ዘልላ ወጣች። ፍራንቾይዝ ማሠሪያውን አላልታው ነበርና ሦስቱ ጓደኛሞች ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመጋለብ ነጐዱ።



ከኋላቸው በቂ ርቀት መኖሩን ሲያውቅ ሜትር ዠረሚ ከመንገዱ ወጣ አድርጓቸው በአንድ ጉብታ ላይ በሚገኝ ፍርስራሽ በኩል ወሰዳቸው።

ከፈረሶቻቸው ላይ በመውረድ እንስሳቱን እንዲያርፉ አደረጓቸው። ካይሮ ውስጥ ምን እንደተፈፀመ፣ ፕሮቴስታንቱ ለአሊስ ተረከላት።

«ጆን ባፕቲስት ተመልሷል» ስትል በመደነቅ ተናገረች።

ከብዙ ጭቅጭቅ በኋላ ወደ ከተማ ሲመለሱ ነገሯት። የምታፈቅረው ሰው ከነርሱ የግማሽ ቀን የግልቢያ ርቀት ላይ በተቃራኒው አቅጣጫ መሆኑን ቢነግሯትም ይህ በራሱ ስቃይ ነው። ዕጣ ፈንታ፣ ፍቅረኛሞች ፍቅራቸው በደስታ ኮከብ ስር የመሆኑን ምልክት ሲያመለክታቸው፣ እነርሱ ራሣቸው ይበልጥ በድፍረት ሲቋቋሙት ይሞክራሉ። ጆን ባፕቲስት፣ ከሼርሣይለስ ማምለጥ ችሎ ከሆነና ከንጉሡም ካፈተለከ አይፈራም። ምክንያቱም እርሷ ተመልሳ ካይሮ ውስጥ ትታያለች። ሜትር ዠረሚና ፍራንቾይዝ ትዕግስት እንድታደርግ በመጐትጐት ራሱ ጆን ባፕቲስት የሰጣቸውን መመሪያ ደግመው ነገሯት። በመጨረሻም አመነቻቸውና ወደ ሲና ለመድረስ ዕቅድ ነደፉ።

«ለጊዜው አሁን በዚህ ብቸኛና ምንም በሌለበት ቦታ እንተኛና መንገዳችንን እንደገና ማታውኑ እንቀጥላለን» አለ ሜትር ዠረሚ

እንቅልፍ ሊወስዳቸው ባይችልም፣ አውላላው መሬት ላይ ለሽለብታ ያህል ዝርግትግት ብለው ዕረፍት አደረጉ።

ከማታው አስራ ሁለት ሰዓት ሲሆን፣ ፈረሶቻቸውን ጫጭነው እንደገና ጉዟቸውን ቀጠሉ። ምሽቱ ንፁህ ሰማይ ስለነበረው፣ የጨረቃዋ የወተት አረፋ የመሰሉ አንድ ሺህ አንድ ነፀብራቆች በወንዙና በየቦዩ ውሃ ላይ ስለተፀነጉ በደለሉ መሬት ላይ በቀላሉ መጋለብ ቻሉ።

ሊነጋጋ ሲል የኢስማኢሊያን ከተማ ለማየት የሚችሉበት ቦታ ደረሱ። በአስራ አንድ ሰዓት አካባቢ ሲዘልቁ፣ ከተማዋ ገና በፀጥታ እንቅልፍ ላይ ነበረች። የሱቆች የእንጨት መከለያዎች እና መስኮቶቻቸውም እንዲሁ እንደተዘጉ ነበሩ። በሮቻቸው በተለይ በጥብቅ የተዘጉ ነበሩ። በመንገዶች ላይ ነፍስ አይታይም። የጠለፋው ዜና አስቀድሞ ካይሮ ሳይነገር እዚህ ሊደርስ ስለማይችል ሜትር ዠረሚ አልሰጋም። ይሁን እንጂ እርሱም ቢሆን እንደ ሁለቱ ሴቶች በዚህች ያልበፉች ወይም ነዋሪዋ ፈጽሞ ትኩረት ያልሄደችና የሞተች የምትመስል ከተማ ፀጥታ ስጋት አሣድሮበታል።

ግራና ቀኙን በሁለት የኦቶማን መስጊዶች የሀውልት መማቢያ በረንዳዎች ከሚዋሰነው ሠፊ ጕዳና ሲደርሱ በአንድ ቤት ሦስተኛው ወለል ላይ የእንጨት መከለያ በድንገት ሲከፈት ሰሙ። ወዲያውኑም አንዲት ወጣት ሴት መስኮቱ አጠገብ ብቅ ሰትል ተመለከቱ። ዐይኖችዋን በእጆችዋ እንደማከላከል አድርጋ እንደ አይነ ስውር ዐይኖችዋን ጨፈነቻቸው። በዚያው ቅፅበት ከመንገዱ ባሻገር የሚገኝ ቤት መስኮትም ተንጓጥጦ ተከፈተና አንድ ሽማግሌ አጕንበሶ በመንገዱ ላይ መንገዝ ጀመረ። ያደረገው ኮፊያ በጨርማታው ማንፀሩ ላይ ተንጋዷል። ሌሎች መጋረጃዎችም መከፈት ጀመሩ። የአንድ ሱቅ መዝጊያም አፋሽክ።

«ለምንድነው ለመነሣት እንዲህ የምትዘገየው?» አለ ሜትር ዠረሚ ከበላያቸው ባለው መስኮት ውስጥ ለነበረው ሽማግሌው ሰው፣ በአረቢኛ

ሰውዬው የሚያናግረው ማን እንደሆነ ለማየት ዙሪያውን ቃኘ። እርሱም እንደሴትዮዋ ዐይኖቹ ጨፍኖ የማየት ችግር ያለበት ነበር።

«እዚህ መንገዱ መሃል ነው ያለሁት፣ ሃሎ! » አለ ሜትር ዠረሚ

«አሃ፣ እንግዳ መሆን አለብህ!» አለው ሽማግሌው

«ዛሬ ማለዳ መድረሴ ነው»

«እናም በተሰበ መኮዳታችንን አታውቅም ማለት ነው»

ፕሮቴስታንቱ ነገሩ ትዝ አለው። ካይሮ ውስጥ ሣለ፣ በስዊዝ የባህር ወሽመጥ በኩል ራቅ ብሎና በአንዳንድ ከተሞች ውስጥ ወረርሽኝ ተከስቶ እንደነበረ ሲወራ ሰምቷል። በወቅቱ በዚያ አቅጣጫ የመሄድ ዕቅድ ስላልነበረው የሰማው ነገር ከአዕምሮው ጠፍቷል።

«ዛሬ ተገልለን የመሰንበታችን የመጨረሻው ቀን ነው። ለመሆኑ በመንገዱ ላይ ብዙ አስከሬኖች ተመለከትክ? አለው ሽማግሌው ግብፃዊ

«እስከ አሁን አላየሁም። ሁሉም ሰው በጣም ጤነኛ ይመስላል» አለ ሜትር ዠረሚ

ከዚህ በኋላ መስኮቶች ሁሉ ተከፈቱ። ሰዎች ከወዲህ ማዶ ወደዚያ ማዶ ቃላትን በደስታ መለዋወጥ ቀጠሉ። መንገዱ በደስታ ሁካታና ዋካታ ተሞላ። በሮች ሁሉ ተበረገዱ። ወንዶች፣ ሴቶችና ሕፃናት በጭለማው ግራ ቢጋቡም እየተጠባበቁ በመሰብሰብ መንገዱ ላይ መደነስ፣ መዋከብና አይነ ስውር የሆኑ ይመስል እርስ በርሣቸው እየተንቀራፈፉ መጋጨትና ከልባቸው በመሣቅ መደሰት ጀመሩ።

በሁካታውና በጫጫታው መሃል ሰስቱ መንገደኞች ሳይስተዋሉ አለፉ። ለፈረሶቻቸው ድርቆሽና ለራሣቸውም የደራረቁ ፍራፍሬዎችን አገኙ። ባለመደብሮቹም ለረዥም ጊዜ ሥራ ፈትተው ቆይተው ስነበረ በጥሩ ዋጋ ሸጡላቸው።



ቅድመ ጥንቃቄ ካለማድረግ የተነሣ የምግብ ሽቀጣሸቀጦችን ለሚሸጥላቸው ሰው ሜትር ዠረሚ በተደጋጋሚ ወደ ስዊዝ እንደሚጓዙ ነገረው። ከከተማዋም ወጥተው ወደ ባህረ ሰላጤው አቅጣጫ ጉዟቸውን ጀመሩ። ከመንገዱ ጥቂት ርቀት ወጣ በማለታቸውና ቀኑም ገና ስለሆነ ከአንድ ትንሽ የአሸዋ ቁልል ተራራ ግርጌ እጅብ ብሎ በበቀለ የዘንባባ ጥሻ ውስጥ አረፍ ብለው ድብን ያለ እንቅልፍ ወሰዳቸው። በምሽቱ ቅዝቃዜ ደግሞ እንደገና ጉዟቸውን ቀጠሉ። መንገዱን በቀጥታ ተከትለው ከመጓዝ ይልቅ ወደ ኋላ ተመልሰው በምስራቅ አቅጣጫ ወደ ሲና ተራራ የሚያመራውን አቧራማውን የእግር መንገድ በመያዝ ወደ ምድረ በዳው አቀኑ። ብዙም ሣይቆዩ አረንጓዴ እፅዋት ሁሉ ከኋላቸው ቀሩ። በዙሪያቸውም በምድረ በዳው አሸዋማ አለጋቸው ላይ እንደ ሃውልት ሽቅብ ከተመዘዙት ድንጋዮች ሰማያዊ ጥላ በስተቀር አንዳችም ነገር የለም። እንዲህ ባለ የምድር ገፅታ ጉዞ ላይ፣ ግመሎች የበለጠ ተመራጭ ይሆኑ ነበር። ይሁን እንጂ ፈረሶቻቸው እነዚህ የአካባቢውን ምድር ያቆሸሹ፣ሹልና ስለታም ድንጋዮችን በድፍረት ተቋቋሟቸው። እኩለ ለሊት ላይ የመጀመሪያውን የምድረ በዳ ገነት አካባቢ ሲያቋርጡ ላለማረፍ ወሰኑ።

በሰማዩ ውስጥ በተረፖት ከዋክብት እየተበራቱ ጉዟቸውን አጋጋሉት። ሜትር ዠረሚ ብዙ ጊዜ ወደ ፍራንቾይዝ ይመለከታል። ይሁን እንጂ የአሊሰን ቅር መሰኘትና ሃዘን በመፍራት ስሜቷንም ላለማቆሰል በማሰብ ወደ ጓደኛው አብዝቶ ፈገግ ከማለት ተቆጠበ።

# 7

የካይሮ ፓሻ ከሚኖርበት ምሽግ በስተጀርባ፣ ከቤተመንግስቱ ረዥም ግንብ በታች፣አንድ ጭር ያለ መንገድ አለ። ወደዚህ መንገድ ምንም አይነት ነገር ማለትም በርም ይሁን መስኮት እንዲከፈት አይፈቀድም። በዚህም የተነሣ የቤተመንግስቱ ጀርባ በአንድ በኩል እና እንዲሁም ግድግዳ ብቻ የሆኑት የከተማው ቤቶች በሌላው ወገን ሆነው ሲያዩት፣ መንገዱ በሁለት በማይቋረጡ ግድግዳዎች መሃል እንደ አባብ እየተጥመለመለ ያለ የመስኖ ቦይ ወይም ተራ ቦይ ይመስላል። ጠባቂዎች ቀንና ሌሊት ይቃኙታል። ይህን የምስጢር መንገድ አንድም ሰው አይደፍረውም። ይህም ሆኖ ፍፁም ከሌላው በጣም በተነጠለው የጠባቡ መንገድ መሃል አካባቢ፣ አንድ በብረት ቁልፎች የተቀለፈ፣ ነገር ግን በፊት ለፊቱ በኩል የመክፈቻው ቀዳዳ የሌለበት መግቢያ አለ። የዚህን ታላቅና ሰፊ ግንብ በሸነቆረው በዚህ መግቢያ በኩል፣ ማንም ሰው ወደ ቤተመንግስቱ አደባባይ መዝለቅ ይችላል። በዘመናት ውስጥ የተለዋወጡት ፓሻዎች በዚህ መግቢያ ላይ የያንዳንዳቸውን ባህርይ ሊገልፅ ለሚችል ለተለያየ አገልግሎት ተጠቅመውታል። ፖንሴ፣ ወደ አቢሲኒያ ለመጓዝ ከከተማው እንደለቀቀ፣ ከፈረስ ላይ ወድቆ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደሞተው እንደ ሁማይን ያሉት፣ ይህን መሹለኪያ የከፈቱት ማንነታቸው ሣይታወቅ ወደ ከተማው ዘልቀው ለመግባትና በጉዟቸውም ላይ ሰዎች ምን እንደሚሉ ለመስማት፣ በሃሩን አልረሺድ ስልት ሴረኞችንና ተንኮለኞችን ለማሣደድ ይጠቀምበት ነበር። ሌሎቹ ደግሞ ባልተቋረጠ ቅኝት ውስጥ ተቆልፎ እንዲቆይ አድርገውታል። እንዲህ የሚያደርጉት ለነፍሣቸው በጣም የሚፈሩት ናቸው። እንግዲህ የሰዎችን ውስጣዊ ስሜትና ፍላጐት፣ ሁልጊዜም የሚያረካቸውን ነገር የሚያውቀው አላህ ሲሆን፣ እነዚህ ለሕይወታቸው የሚሰጉት ፓሻዎች፣ ብዙ ጊዜ የሚሞቱት በቅጥር ነፍሰ ገዳዮች እጅ ነው። አንዳንዶቹ ደግሞ ይህን የጓሮ በር በአፊሴል የማይቀበሏቸውን ሰዎች የሚያስገቡበት አደረጉት። የመሃመት ቤይም የዚህን በር አጠቃቀም ይህን ይመስላል። ሁሪያውን በፀሎት፣ በተስፋ፣ በግብፅ ውስጥ በሚገኙ ወግ አጥባቂ ሙፍቲዎችና ኢማሞች የማፅናኛ ቃላት ቢታጀብም እርሱም ቢሆን አልፎ አልፎ ሃማበ ግትርነቱን ለሰለስ ያደርግና፣ ጠንቃቃ የውጭ ጉብኚዎችን በዚህ በር በኩል እንዲገቡ ይፈቅድላቸው ነበር። እነዚህ ጠያቂዎች እንዲገቡ የሚደረጉት በመሽሎኪያው በኩል ነው።



መሀመት ቤይ፣ በእስልምና ሕግ አራት ሚስቶች አሉት። ከነርሱም አሥራ ሁለት ልጆችን አግኝቷል። እነዚህ የተቆጠሩት ልጆች በሕይወት ያሉት ብቻ ናቸው። እንዳስመታደል ሆኖ ታዲያ መሃመት ቤይ ሊገታ የማይችል የውጭ አገር ሴቶችን የማደን ስሜት አለው። ይህን አይነት ፍላጐት ያደረበት፣ አውሮፖ ውስጥ በዘመቻ ላይ ሣለ ነበር። እነዚያ የተባረኩና ከረዥምም ዘመናት በፊት የነበሩ ጊዚያት ቀላል ነበሩ። በነዚያ ጊዜያት አረማውያን ቆነጃጅትን በምርኮ ይቀበላቸዋል። ይህን ድርጊት አይሆንም ብሎ የሚቃወምና የሚያጠቃም አልነበረም። ሁሉም ዓይነት ቁመናና ዕድሜ ያላቸውን ፈረንሣውያን ሴቶች ንብረቱ አድርጓቸው ነበር። እውነቱ ይነገር ከተባለ፣ ለርሱ ሁሉም ምንም ልዩነት የላቸውም። መሃመት ቤይ ደስ ይለው የነበረው፣ የሌላ እምነት ተከታዮች የሆኑ ካቶሊኮች፣ አይሁዶች፣ ኦርቶዶክሶች ወይም እምነት የለሾችም ቢሆኑ አግሮቻቸውን አንፈራጥጠው ሲቀመጡ የሚሰማው ስሜት ነው። ይህን ሲያከናውን የራሱን እምነት በመተው አይደለም። በእምነቱ በኩል አይታማም። የራሱን እውነተኛ አማኒያን ፍሬዎች፣ ቀደም ሲል ሌሎች አርሰውና አለሳልሰው ያዘጋጁትን ትልም በመንጠቅ በዚያ ላይ መትከል ለነብዩ ትሁት አገልጋይ የሆነ ያህል ይሰማዋል። ሙፍቲዎችም፣ ፓሻው የሃይማኖት መልዕክተኛ ያህል የሚያከናውነውን የጋለ ፍቅር ስለተቀበሉት ሌላውን ተግባሩን የተመለከቱት በሌላ መልክ ነው። ይሁን እንጂ በዚህ የቱርካውያን ግዛተ ዘውድ አካበቢ ያለውን የሞራል ትክክለኛነት፣ ተገቢነትና በተለያዩ እምነቶች መካከል ያለው ሚዛናዊ የመንፈስ እርካታ ስላለ፣ በተቻለ መጠን የፓሻውን የተለያየ ስሜትና ዝንባሌ ለማስደሰት ይሞከራል። ትንሿ የስርቆሽ በር የምታገለግለውም ለዚሁ ነው።

በውትድርና ዘመኑ ከቦታ ቦታ ያደረጋቸው እንቅስቃሴዎች፣በአካሉ ላይ ከባድ ጉዳት ጥለውበት አልፈዋል። በዚህም የተነሣ ካለፉት ወራት ጀምሮ በሚሰማው ስቃይ ምክንያት፣ሌላው ቀርቶ መጥፎ ወንጀል የፈፀመ ሰው እንኳ ቢቀርብለት ለመቅጣት ብርታቱና ፍላጐቱ አልነበረውም። እንደዚሁም ሁሉ የፈለገውን ያህል ቆንጆ፣ ወጣትና በሃይማኖቷም የተጠላች ሆና ብትቀርብለት ብርታቱና ፍላጐቱ አልነበረውም። ባለፉት ሦስት ወራት በዚህ የጓሮ በር ተጠርተው የሚመጡት ሐኪሞች ብቻ ነበሩ። ከነርሱም መካከል ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ዠረሚ ነበር።

ዠረሚም ከሣምንቱ በተወሰኑ ሰስት ቀናት ውስጥ እኩለ ሌሊት ላይ ይመጣል። የኪላ ዘበኞችም ይህን ስለሚያውቁ «ሄሌቦሬ» የሚለውን የይለፍ ቃል ሲሰሙ ያስገቡታል። የዚያን ዕለት ምሽትም እንደተለመደው በትልቅ ኮት ተጀቡኖ፣ ሰፊ ባርኔጣ አድርጐ መጣ። የይለፍ

ቃሉን ተናግሮ በስርቆሽ በር ገባ። በባዶ እግሩ ሆኖ፣ ነጭ የለበሰ ሰው ሃኪሙን በእምነ በረድ ደረጃዎች በኩል ወደ እንዲት አነስተኛ የቤተመንግስት ቅጥር ግቢ መርቶ ወሰደው። በቱርካውያን ዘይቤ በተሰናዳ ሸምል የቅስት ማለፊያ በር አልፎ፣ ግድግዳው በሰማያዊ ሴራሚክ በተኔጠ ባለ ስምንት ማዕዘን ክፍል ውስጥ አስቀመጠው።

በረኸርም ሰንሰለት በጣሪያው የጥድ ከንች ላይ ከታሰረ መብራት፣ አራት ሻማዎቹ ብቻ የሚበሩበትና የተለያዩ ቀለማት ያሉት የመስተዋት አምፑል ተንጠልጥሏል። ፓሻው፣ በጥግ በኩል በአንድ የአራት መብያ ጠረጴዛ አጠገብ ተቀምጧል። እግሮቹን ወደ አንድ የነሃስ ምድጃ ዘርግቷቸዋል። ምድጃው ባለሦስት እግር ሲሆን የጢስ ማውጫው በቀጭን ቱቦ ወደ ውጭ እንዲወጣ ተደርጓል። እግረኛው ሰውዬ ተመልሶ ሄደ።

«ወደዚህ ቀረብ በል። ዶክተር» አለ መሃመት ቤይ በአረቢኛ

ጉብኚው፣ ከእንጨትና ከዝሆን ጥርስ በተሠራ በርጮማ ላይ ተቀምጦ የለበሰውን ኮት ሲያወልቅ ቱርካዊው በፍርሃት ወደ ኋላ ካለ በኋላ፣ እጁታው እንቁ ሆኖ የታጠቀውን ቢላዋ አፈፍ አደረገ።

«ለመሆኑ አንተ ማነህ?» ሲል ጠየቀው።

ዘበኞቹን ሊጠራቸው ምንም አልቀረውም ነበር። ጆን ባፕቲስት ፈጥኖ ገታው።

«ጌታዬ፣ ስጋት አይግባዎ። የተላክሁት በሜትር ዠረሚ በራሱ ነው። እኔ ሸሪኩ ነኝ። ስለኔ እስከዛሬ ድረስ ምንም አልነገረዎትም?»

«የኢትዮጵያውን ንጉሥ ያከምከው ሰውዬ ነህ?»

«በትክክል እኔ ነኝ ጌታዬ»

ጆን ባፕቲስት ዝቅ ብሎ እጅ ነሣ

«አስቀድሞም እንድታየኝ አጥብቄ የፈለግሁህ አንተን ነበር። ሆኖም ሸሪክህ ወደ አውሮፖ መሄድህን ነገረኝ» አለ መሃመት ቤይ

«ይኸው አሁን ገና መድረሴ ነው»

«እንግዲያው ዠረሚ ለምን አብሮህ አልመጣም። ከዚህ አይነቱ አስፈሪ ስጋት ያድነኝ ነበር»



«እርሱ ራሱ አሁን ጤነኛ አይደለም። ይቅርታ እንዲያደርጉለትም እንድነግርዎ ጠይቆኛል»

ፓሻው በምድጃው አጠገብ ተመልሶ ተቀመጠ።

«እጅግ በጣም ጥንቃቄ ሲያደርግልኝ ነበር። ሁልጊዜም ቢሆን እርሱ እንደማይስተካከልህ በመግለፅ፣ አንተ እዚህ ብትኖር ኖሮ ምንኛ ጥሩ እንደነበረ ሲመኝ ነበር»

«ይህን ዓይነት የሚናገር የልብ ጓደኛ ነው። እውነቱ ግን፣ሁለታችንም እንደጋገፋለን። እኔ መድሃኒቶችን ሣገዝዝ፣ እርሱ ቀምሞ ያዘጋጃቸዋል። የመድሃኒት ቅመማው ለኔ ባዕድ ነው»

«እንዲህ ከሆነ እንግዲያው መርምረኝና የሚያስፈልገኝን የህክምና ጉዳይ ወስንልኝ» አለው ፓሻው በድካም።

ጆን ባፕቲስት፣ ሕመሙ ምን ያህል ጊዜ እንደቆየበት፣ መነሻ ሰበቦቹ ምን እንደሆኑና በትክክል ምኑ ላይ እንደሚያመው ሸማግሌውን በስፋት ጠየቀው። ከዚህ በኋላ ስለራሱ የሕይወት ታሪክ፣ ስለሚበላውና ስለሚጠጣው፣ እንዴት እንደሚተኛ፣ ስለሴቶች ያለውን ስሜት እንዲነግረውም ጠየቀው። በዚህ ዘዴ ጆን ባፕቲስት ከፊት ለፊቱ ያለውን ሰው ውስጣዊ ማንነትና ስሜት ይረዳል። የሰውዬውን ተፈጥሮአዊ ሥረ መሠረት በማመዛዘን ከሌሎች ነገሮች ጋር ማለትም ከሌሎች ሕይወት ያላቸው ነገሮችና ከነዚሁ ነገሮች ቅጠሎችና ፍሬዎች ጋር ያለውን ምስጢራዊ ግንኙነት በመመልከት ጤንነት እንዲመለስለት ሊያደርግ ይችላል።

«የመዳን ዕድል እንዲኖረኝ ልታደርግ ትችላለህ?» ሲል ፓሻው ጠየቀው።

«ይህ የሚወሰነው እንደ ጥያቄው ዓይነት ነው። መዳን ማለት እንደገና የሃያ አመት ጉረምሣ መሆን ማለት ከሆነ የሚቻል አይደለም። ጌታዬ፣ የዚህን ዓይነት ነገር የለም። ነገር ግን ሰላማዊ ጥንካሬና አሁን ባሉበት ዕድሜዎ ላይ የሚያስፈልግዎትና ተዝናዎ የሚሆነውን ደስታ ማለትዎ ከሆነ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ሊያገኟቸው እንደሚችሉ ላረጋግጥልዎ እችላለሁ።»

ቱርካዊው ተደሰተ።

«መድሃኒቶቹን ለማዘጋጀት ወደ ሥራ ቦታዬ መመለስ ይኖርብኛል። እናም ነገ እኔው ራሴ ይዤልዎ እመጣለሁ» አለ ጆን ባፕቲስት።

«እንግዲያው እንዳትዘገይ» አለው ፓሻው፣ ትዕግስት እንዳጣ በሚያመለክት ሁኔታ። «በነገራችን ላይ ዠረሚ ማይነርህ እንደማይቀር ባውቅም፣ እኔም በደንቡ መሠረት ልነግርህ ይገባኛል። ይህን ሁሉ ነገር በተመለከተ አንድም ቃል ትንፍሽ አትልም። በተለይም ለፈረንሳዮች»

«ጌታዬ፣ እኔም እርስዎ ተመሣሣዩን ውለታ እንዲያደርጉልኝ መጠየቅ እወዳለሁ። በፈረንሣውያን ማህበረሰብ ውስጥ የኔን መመለስ የሚያውቅ አንድም ሰው የለም። በተለይም ቆንሲሉ አያውቁም። እኔም ብሆን መመለሴ እንዲታወቅ አልሻም። በርግጥ ሽሪኬን የምጉበኝ ው ማታ ማታ ሲሆን፣ቀን ቀን፣በጥንቱ የአረቦች መኖሪያ ውስጥ በሚገኝ ፔንሲዮን ለጊዜው እየኖርኩ ነው»

«እውነትህን ነው? በጣም ይገርማል» አለ ፓሻው «ንጉሥህን ልታያቸው እንደሄድክና በተልዕኮህም እምነት የተጣለብህ ነበር የመሰለኝ»

«አይ ጌታዬ፣ ታሪኩ ከፉና የሚያም ነው።» ሲል የራሱን መጥፎ ዕድል ሌሎች እንዲሸከሙለት በማይፈልግ ሰው የአነጋገር ቅላፄ «እናም ረዥምም፣ እጅግ ብዙ አስገራሚ ውጣ ውረዶች የነበሩበትና በአጭሩ ሊያደክምዎ የሚችል ታሪክ ነው»

«እስቲ ታሪክህን ንገረኝ» አለው ፓሻው። በአፊ ታሪክ እንደሚታወቀው እንደ ሱልጣን ሻህርያር፣ ልብ አንጠልጥል እንደሆነ ወግ የሚያስደስተው ሌላ ምንም ነገር እንደሌለ ሁሉ

«ደግ እንግዲያው» አለ ጆን ባፕቲስት «ወደ አቢሲኒያ ሄድኩ»

የጉዞውን ትረካ በረዥሙ ገለፀለት። ከንጉሡ ነገስቱ ጋር መገናኘቱን፣ ከከንፈሮቹ እንደ ውብ ምንጭ ውሃ እየፈሰሱ በሚወጡ ቃላት ሲናገር፣ ፓሻው ዐይኖቹን በከፊል ጨፈን በማድረግ ትረካውን በመስማቱ መደሰቱን የሚያመላክት ምልክት አሣየ። ደስታውን ይበልጥ ለማጣፈጥ ስለፈለገ ጥሩ መዓዛ ያለው ተክል ሻይና ኬክ እንዲቀርብ አዘዘ።

ጆን ባፕቲስት በትረካው ውስጥ ንጉሡ አንድም የውጭ አገር ቄስ እንደማይፈልግ፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንም በቋሚነት ከግብፅ ፖትርያርኳን እንድታገኝ ፓሻው መብት መስጠታቸውንና እንደሚያከብሯቸው ዘረዘረለት።

«በተራሮቻቸው ላይ በሰላም መኖር ይፈልጋሉ» በማለት ፖንሴ አጠቃለለ።



«በአላህ፣ ትክክል ነው? ሳስበው ምክንያታዊነታቸው ዝቅ ያለ ይመስለኝ ነበር። አሁን አንተ የምትነግረኝ በጣም ጥሩ ዜና ነው። ነገር ግን፣ ይህ ሁሉ፣ አንተ አሁን ለምን መደበቅ እንዳለብህ የሚያስረዳ አይደለም።» ሲል መሃመት ቤይ ገለፀ።

«ወደዚሁ እያመራሁ ነው ጌታዬ። ከዚያ በኋላ ደግሞ ወደ ቬርሣይለስ ተጓዝኩ . . . »

ጆን ባፕቲስት ከዚህ በኋላ ቬርሣይለስ ስላሉት ስለፀሐዩ ንጉስ ቤተመንግስት ረዥም ገለፃውን ቀጠለ። ፓሻውም በደስታ ያዳምጠው ጀመር። ፓሻው፣ አውሮፖ ውስጥ በውትድርና ላይ በነበረበት ዘመን ወደ አንዱ የአውሮፖ ዋና ከተማ የመግባት ተስፋ ብዙ ጊዜ ነበረው። የሚያሣዝነው ግን ብዙውን ጊዜውን በሜዳ መካከል በሚከተም ቦታ ላይ ነበር ያሣለፈው። በሌላ በኩል አንድ ከተማን የመያዝ ዕድል የነበረው ጊዜም ቢሆን ከተማውን የሚያገኘው ከወደመ በኋላ ነበር። ጆን ባፕቲስት፣ ቬርሣይለስ ስለሚገኙ ሴቶች፣ ስለፀጉር አሠራር ዘይቤአቸው፣ ስለሽቷቸው በሰጠው ገለፃ ላይ ሆን ብሎ በተንኮል ቀስ እያለ ተናገረ። ምስኪኑ ሽማግሌ ወታደር በደስታ አቅሉን ሣተ።

ከዚህ በኋላ ጆን ባፕቲስት ከንጉሱ ዘንድ ያጋጠመውን የሽንገላ ግንኙነት ገለፀ። በዚህ ትረካው ውስጥ አጣርቶ የሚያዳምጥ ጆሮ እንደሌለ፣ የፈረንሣዩ ንጉሥ ደስ ብሏቸው የሚቀበሉት በምስራቅ ሜድቴራኒያን ስላለው ጉዳይ ብቻ ነው ሲል አስረዳ።

በመጨረሻም የፈረንሣዩ ንጉስ፣ ታላቅ ንጉሥ መሆናቸውን ተስማሙ። ይሁን እንጂ፣ ሉዊስ፣ ሙስሊም ባለመሆናቸው መሃመት ቤይ አዘነ። ሆኖም ካለው የጋለ ስሜት በመነሣት፣ ንጉሡ ቢሰልሙ ጥሩ ሙስሊም ሊሆኑ እንደሚችሉ ተናገረ።

«ይህ ሁሉ ነገርህ፣ለምን መደበቅ እንዳለብህ የሚነግረኝ ነገር የለም» ሲል ፓሻው ጐተጐተው።

ምሽቱ እየተገባደደ ነው። አሽከሮች ሁለት ጊዜ በምድጃው ላይ አዳዲስ ጊንዲላ ጨምረዋል። ፓሻው፣ የውሃ ፒፖው እንዲቀጣጠልለትና ከጆን ባፕቲስት ጋር እንዲጋራው ትዕዛዝ ሰጥቷል። በዚህ ሞቅ ባለ ጭውውታቸው በመሃከላቸው ያለውን የደረጃ ልዩነትም አላገናዘቡትም።

«ወይኔ» አለ ጆን ባፕቲስት «ታላቁ ንጉሣችን፣ ያው ንጉሥ ናቸው። ከእግዚአብሔር ጋር ሲነፃፀሩ በጣም ደካማ ንጉሥ ናቸው። በሰማይ ያለው ጌታችን ግን ሁሉንም ነገር ያያል . . . »

ባልተቋረጠ የጣኦት እምነት ቁጥጥር ስር የኖረው ቱርካዊ በተሸናፊነት ወደ ሰማይ አንጋጥጦ ተመለከተ፡፡

«አንድም ጣኦት ብሎ ነገር የለም፡፡ ያለው ፈጣሪ እግዚአብሔር ብቻ ነው» ሲል በመማሪያ እንደተፈጠረ የሙዚቃ ድምፅ ተናገረ፡፡

«. . . ምድራዊ ገዥዎች በሚያውቁት ነገር ውሱን ናቸው»

«ይህ እውነት ነው»

«አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በዙሪያቸው ምን እየተከናወነ እንደሆነ አይጠነቀቁም»

ጨዋታው ከመቀጠሉ በፊት፣ ፓሻው ያቀበለውን የእንጨት ፒፓ ተቀብሎ ሁለት ጊዜ ሳብ ሳብ አደረገ፡፡

«እኔ በቤተመንግስታቸው ውስጥ ሲካሄድ የደረስኩበትን ሴራ፣ እርግጠኛ ነኝ፣ ንጉስ ሉዊስ 14ኛ አይፈቅዱም ነበር»

«ሴራ!» ሲል ጊዜው በጣም ቢመሽም ፓሻው በዶክተሩ ታሪክ ይበልጥ እየተመሰጠ መጣ፡፡

«ሊገልፀው የሚችለው ብቸኛው ቃል ይኸው ነው፡፡ ለምን እንደምደበቅ ለማወቅ ይፈልጋሉ አይደለ? አዩ፣ ምክንያቱ እኔ ራሴን ለነዚህ ሴረኞች እቅድ ተባባሪ ማድረግ ስላልፈለግሁ ነው»

«ይህ ሁሉ ስለምን ጉዳይ ነበር?» ሲል ፓሻው በመቁነጥነጥ ጠየቀው፡፡

«ስለርስዎ ነበር ጌታዬ»

«ስለኔ!»

«አዎን፣ ስለርስዎ፣ ስለግብፅና ስለአቢሲኒያ፡፡ ይህ ሁሉ የሚጠነሰሰውና የሚፈለፈለው እርስዎ እዚህ በመልካም ሁኔታ ተቀብለዋቸው የዲፕሎማሲ ከለላ በሚሰጧቸው ሰዎች ነው»

«የነብዩ ያለህ፣ እስቲ ንገረኝ በሞቴ!» ሲል ፓሻው ብድግ ብሎ ቆመ፡፡ ለማወቅ ያለው ጉጉትም የሥጋት ስሜት አሣደረበት፡፡



«ረጋ ይበሉ ጌታዬ፡፡ እያንዳንዱን ዝርዝር ጉዳይ እነግርዎታለሁ፡፡ ነገር ግን ምንም ዓይነት መጥፎ ምኞት እንደሌለኝ እንዲገነዘቡልኝ እወድዳለሁ፡፡ እኔን በተመለከተ ግን የዚህ ሴራ ሰለባ ሆኜ ቀይቻለሁ»

«በል፣ በል»

«እንግዲያው እሺ፡፡ ይኸውልዎ፣ የእኔ ወደ አቢሲኒያ ተልዕኮ፣ ለንጉሡ የሕክምና ዕርዳታ ከመስጠት ሌላ ምንም ዓይነት ተጨማሪ ወይም የተለየ አላማ አልነበረውም፡፡ ከዚያም፣ ቢያንስ የምስጋና ውለታ አለብኝ ብለው ያሰቡት ንጉሥ፣ ምስጋናቸውን ለፈረንሣዩ ንጉስ እንዳቀርብላቸው ላኩኝ»

«ይህንን ታሪክ አስቀድመህም ነግረኸኛል»

«አዎን አውቃለሁ፡፡ እናም ፈረንሣይ ውስጥ፣ አቢሲኒያውያን ለፈረንሣይ ንጉሥ ያቀረቡት አክብሮት በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ የተለየ ሃሣብ አሣደረ»

«እነማን ናቸው?»

«የንጉሡ ነገስቱ አጃቢዎች ልንላቸው እንችላለን»

«ቀሣውስቱ ናቸው?»

«በርግጥ እነርሱ ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ የሚደንቅ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ወደ አቢሲኒያ ዘልቀው ለመግባት የመፈለጋቸውን ተስፋ ፈፅሞ አልተዉትም፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ይበልጥ የሚገፋፉትና ሙሉ በሙሉ የሚመለከታቸውም እነርሱ ብቻ አይደሉም»

«ከነርሱ ሰዎች፣ የባሰ መጥፎ ነገር መኖሩን ለማሰብ አልችልምና ክፉኛ እያሳሰበኸኝ ነው

«ጌታዬ፣ እርስዎ ነገሮችን ሁሉ በቀናነት ስለሚመለከቱ ነው፡፡ ሌሎች ግን አዕምሯቸውን ሁሉ ለክፋትና ለተንኮል ዕቅድ ሲያዘጋጁ የሚኖሩ መሆናቸውን ይመኑኝ፡፡ ከዚህ ከቱርካውያን መደሰቻ ጥቂት ሳብ ሳብ በማድረግ እራሴን እንድጋብዝ ይፈቅዱልኛል ጌታዬ»

«የቱርካውያኑን መደሰቻ ለጊዜው ርሣውና የምትነግረኝን ቀጥልልኝ»

«ሃሣባቸው እንዲህ ነው። አቢሲኒያ ሃብታም ነች። ወርቅ፣ አልማዝና እንደልብ የሚገኙ የእንጨት ዓይነቶች ሞልተውባታል። ምንም እንኳ አቢሲኒያ የክርስቲያን አገር ብትሆንም፣ በአንዳንድ የሃይማኖቱ ሕግጋት ላይ የተለየ መስመር አላት። በዚህም የተነሣ ለሮማ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን አክብሮቷን አትገልፅም። እንደዚሁም ደግሞ አቢሲኒያ፣ ከቱርኮች አልፋ ማለትም ከርስዎም አልፋ በሩቅ ቦታ ላይ ነው የምትገኘው»

«እና?»

«እናማ ስለዚህ በቁጥጥር ስር መደረግ ይኖርበታል»

«ይኸው ብቻ ነው»

«ይበቃል ካሉ ይኸው ነው። ይህ ደግሞ የተወሰነ ጉዳይ ነው። ነገር ግን እንዴት ዕቅዱ ይሣካል? አቢሲኒያን እምነቷን በማስለወጥ ነው? ይህ ደግሞ ብቻውን በቂ አይደለም። ምናልባትም የተገላቢጦሽ ቢፈፀም የተሻለ ይሆናል። ይኸውም አስቀድሞ በሃይል ማሸነፍና መቆጣጠር። ከዚያ በኋላ ሃይማኖቷን ማስለወጥ። የተመረጠው ዕቅድ ይኸው ነበር»

«ፈረንሣውያን አቢሲኒያን ለመግዛት ይፈልጋሉ ብለህ ነው ሃሣብህን የምትነግረኝ?»

«ሃሣቤን አይደለም የምነግርዎ ጌታዬ፣ እውነቱን ነው የምገልፅልዎ። እኔ በየዋህነት አስቤው ስለኢትዮጵያ ሰላማዊ ንጉሥ የሰጠሁትን ገለፃ፣ ሴረኞቹ በሚገባ የታጠቀ፣ ወርቅና የገፀ በረከት ዕቃዎች ይዞ የተንቀሣቀሰ ሠራዊት፣ ይህችን ኋላ ቀር የሆነች ሀገር ለመቆጣጠርና ለመያዝ በቂ ነው የሚል ሃሣብና እቅድ እንዲያራምዱ ነው የመራቸው። ከአንድ ምዕተ አመት በፊት፣ ጀስዊቶች፣ ንጉሡን ብቻ ለመለወጥ በመቻላቸው፣ አገሪቱን በሞላ ለመቆጣጠር ምንም አልቀራቸውም ነበር። ይሁንና እነርሱ ድላቸውን በጦርነት ለማረጋገጥ መሣሪያ አልነበራቸውም። አሁን ግን አስቀድሞ መሣሪያው ይሰለፋል።»

በመደገፊያው ዙሪያ ባሉ ትራሶች ተከበቦ የተቀመጠው ፓሻ፣ ጆን ባፕቲስትን በጭንቀት ተመለከተው።

«አሁን የምትነግረኝ፣ ይኸ አሁን በመንበዝ ላይ ያለው አምባሲ . . . »

«. . . የተወሰኑ ሰዎች አቢሲኒያን እንቆጣጠራለን ብለው ተስፋ ያደረጉበት መገልገያቸው ነው»

«እነዚህ እኮ ሃያ እንኳ አይሞሉም! ይህ ሊሆን የማይችል ቀልድ ነው!»



«ጌታዬ፣ እኔ ወደዚያች አገር ተጉዣለሁ። አገሪቱ፣ በተቀናቃኝ ሃይሎች ፍላጐት የተዳከመች ነች። ገንዘብና ጠመንጃ ያላቸው ሃያ ሰዎች ሠራዊት ሊመሰርቱ ይችላሉ። አለመረጋጋት ሊፈጥሩ ይችላሉ። በዙፋኑም ላይ አሻንጉሊት ንጉስ ሊያነግሱበት ይችላሉ። ወይም ልክስፓኒያውያን፣ አሜሪካ ውስጥ ባሉ ኢንካዎች ላይ ባለፈው ክፍለ ዘመን እንዳደረጉት ከራሳቸውም ሰዎች አንዱን ሊያነግሱት ይችላሉ።

«እህህህ!» አለ ፓሻው የመሞላቀቅ ፈገግታ ፈገግ እያለ «ይህ ነዋ ሲከበር የነበረው ሴራችሁ?»

«እኔን ራሴን ፍርሃትና ስጋት ውስጥ የከተተኝም ይኸው ነበር። ምክንያቱም እኔ የዚህ ሴራ ተካፋይ ለመሆን አሻፈረኝ ብያቸዋለሁ። ፈረንሣይንም ለመልቀቅ ተገደድሁ። በዚሁ ሳቢያ በተመሣሣይ ምክንያት ስለፈራሁ እዚህ መኖሬን ሸሽጌ እገኛለሁ»

«ወዳጄ ሆይ፣ እውነቱን ልንገርህና አላምንህም። ይህን ሁሉ ያልከኝ እዚያ በነበርክበት ጊዜ ምናልባት አሳሳቢና አስቸጋሪ አለመግባባቶች አጋጥሞህ ይሆናል። ከዚህም ሌላ፣ አንተ በነበርክበት ቦታ ላይ፣ አንዱ ይህን የማይጨበጥ ዕቅድ አንተ እየሰማኸው ተንፍሶ ይሆናል። ይህ ማለት ታዲያ፣እኔ ራሴው ሰላማዊ የይለፍ የሰጠሁት ቅፍለት፣ መሪውን የአቢሲኒያ ንጉሠ ነገስት ለማድረግ ያቀደ ነው ማለትህ ከእውነታው ፍፁም የተለየና የማይታመን ነው»

«ጌታዬ፣ የእርስዎ ማህተም ለነዚህ ሰዎች ፍፁም አስፈላጊያቸው ነበር። የእንቅስቃሴያቸውን መልክ በሚያሣምንና ግልፅ በሆነ መንገድ ካላረጋገጡ እንዴት ሊያገኙ ይችላሉ። እቅዳቸውንም በአንድ ጊዜ ይፋ ማውጣት ጅልነት ነው የሚሆንባቸው። ለምሣሌ የማይንስ ሰዎችን ብቻ ያቀፈ ጓድ ስለሚባለውስ ምንም ነገር አልሰሙም?»

«አዎን ሰምቻለሁ እንጂ። የምሁራን ስብስብ የሆነ አንድ ቡድን ወደ ስዊዝ በማቅናት ከዚያ ወደ አረቢያ ይሄዳል የሚባል ሰምቻለሁ።»

«እና ከዚያም ወደ አቢሲኒያ ይሄዳል። ያጀባቸው ሰው የአቢሲኒያው ንጉሠ ነገስት እንደወኪላቸው አድርገው ከኔ ጋር የላኩት ሰው ነው»

«ያ ውሻ ኩርዳዊ»

«አርመናዊ ነው»

«ያው፣ ያው ነው» አለ ፓሻው። «እርሱ አብሯቸው ሄደ? ይህ አልተነገረኝም ነበር»

«ያልተነገረዎ ሆን ተብሎ ነው። እንግዲህ አሁን ይታይዎ ከሆነ፣ ሰዎቹ ሃያ ያህል ሳይሆኑ ወደ ሠላሣው የሚጠጉ ናቸው። ከነርሱ መካከል ጥቂቶቹ ወርቅና መሣሪያ የያዙ ናቸው። ሌሎቹ የንጉሡን መልዕክተኛና የተከማቸውን የምዕራባውያን ዕውቀት ይዘው ይገባሉ»

ፓሻው፣ ሃሣቡን ሊቆርጥ ያልቻለበትና ግራ የተጋባበት ሁኔታ ላይ ስለሆነ በጣም ተጨነቀ። ጆን ባፕቲስት፣ ርህራሄ ተሰምቶት ሊረዳውና ከውሣኔ ላይ እንዲደርስ ለማድረግ አንድ የመጨረሻ መረጃ ሊሰጠው ወሰነ።

«ሌላም አለ»

«ተጨማሪ?»

ጆን ባፕቲስት ፓሻውን በቀጥታ አይኖቹ ውስጥ አየው።

«አዎን ጌታዬ፣ ከዚህ ቅፍለት በፊት አንድ የካፑቺኖች ቡድን ለምን ቀደም ብሎ እንደሄደስ ራስዎን ጠይቀው ያውቃሉ? ይህ የተደረገው ሲናር ውስጥ ሊጠብቋቸው አቅደው ነው። በዚህም ላይ በኮፕቲኩ ፓትርያርክ የተሰጣቸውን የቅብዓ ሜሮን ዕዋ ለምን ይዘው ሄዱ?»

«ቅብዓ ሜሮን፣ ቅብዓ ሜሮን ደግሞ ምንድ ነው?» አለ ፓሻው በሃይለ ቃል።

«በኮፕቲክ ሃይማኖት፣ ሥልጣንና ሃይል ከአንዱ ንጉሥ ወደ ሚቀጥለው ንጉሠ ነገስት እንዲተላለፍ የሚያደርግ ቅዱስ ዘይት ነው»

«ይህን ያደረጉት ፓትርያርኩ ናቸው?»

«አሁን እተየነጋገርን ባለንበት ጊዜ ካፑቺኖች በጉዞ ላይ ናቸው»

«ለኔ ሣይነግሩኝ? በአሊ ጉራዱ!»

ከፖንሴ ጋር ስሊቱን ለረዥም ሰዓታት ስላወሩ፣ ፓሻው ደከመው። ይሁንና ከንጋት በፊት ይህን ሳይታሰብ የተነገረውን ታሪክ አምኖ ተቀበለ። ከመከዳው ተነስቶ በክፍሉ ውስጥ ወዲያና ወዲህ ተራመደ። የዕለቱ የመጀመሪያዎቹ የፀሐይ ብርሃን ጨረሮች በሰማያዊው የመስኮት መስተዋት አልፈው በግድግዳው የግርጌ ጠርዝ ላይ የወለሉን ምንጣፍ በሰማያዊ ብርሃናቸው ሞሉት። ድንገት በጆን ባፕቲስት ፊት እንደመፍዘዝ ብሎ ቆመና አመሰገነው። ቀጥሎም፣ በሚቀጥለው ዕለት ማታ መድሃኒቱን ይዞ እንደሚመጣ ቃል ካስገባው በኋላ የሚያብረቀርቅ ንፁህ ውሃ ወዳለው ገንዳ ሄደ ። ሃኪሙ፣ በጀርባው የስርቆሽ በር እንደወጣ፣ መሃመት ቤይ ዘበኛውን ጠርቶ የኮፕቲክ ፓትርያርኩን ከመኝታቸው ላይ ቀስቅሶ፣ በዚያውም ኢማሞችንም ጭምር ከየቤታቸው ጠርቶ እንዲያመጣቸው አዘዘው።



# 8

በሚቀጥለው ቀን ማታ ጆን ባፕቲስት ተመልሶ በተለመደው የስርቆሽ በር ገባ። አንዲት አነስተኛ ቦርሣ ይዟል። ፓሻው፣ ባለፈው ጊዜ በነበረበት ክፍል ውስጥ ሆኖ ሲቀበለው፣ መድሃኒቱን ስላመጣለት ወዲያውኑ እቅፍ አደረገው። ጆን ባፕቲስት ብዙ ብልቃጦችን አወጣ። ዱቄት የተሞሉ የሱረት ብልቃጦችና የደረቁ ሥራስሮችን የያዘ ከረጢት ነበሩበት። ፓሻው ሁሉንም መድሃኒቶች በአንድ ጊዜ እንዳይጠቀማቸው መከላከል፣ የጆን ባፕቲስት ግዴታው ነበር። ቱርኮች መድሃኒት ይዳፈራሉ ብሎ፣ ሜትር ዠረሚ የነገረው ቢሆንም እንዲህ ይስገበገባሉ ብሎ አልገመተም።

«መድሃኒቶችን የሚያዘጋጅልዎ የተለየ አሽከር እንዳለዎት አምናለሁ። እርሱ ቢጠራና እነዚህን መድሃኒቶች እንዴት እንደሚያዘጋጃቸው በቀጥታ ከኔ ሰምቶ ሃላፊነቱን ቢወስድ የተሻለ ይሆናል» አለ ጆን ባፕቲስት

ፓሻው አጨብጭቦ፣ አንድ የሆነ ስም ጮሆ ተጣራ። የቤት ውስጥ ተላላኪው ወዲያውኑ ደረሰ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሽምግል ያለ አሽከር ገባና ለሁለቱ ሰዎች በአክብሮት ጐንበስ አለ። አዛውንቱ፣ አጭርና ቀጭን ሲሆን ባለቤቶቹ ያባረሩት፣ ረዣዥም ቅልጥሞች ኖረውት ለመሮጥ ፈጣን የሆነ፣ ዓይኖቹ ማተኮር የሚችሉና የአዳኝ ውሻ የመሠሉ ሾጠጥ ያለ ፊት ያለው ነው።

«አብዱል መጅድ። አዳዲሶቹ መድሃኒቶች እኒሁና። እንዴት መጠቀም እንዳለብህ በሚገባ በጥንቃቄ አዳምጥ» አለው ፓሻው።

ጆን ባፕቲስት ሁሉንም ነገር በስፋት ተንትኖ ከነገረው በኋላ፣ ቦርሣውን ሳያስረክበው በፊት የተነገረውን በሚገባ መረዳቱን ለማረጋገጥ፣ አሽከሩ ሁሉንም ነገር መልሶ እንዲደግምለት አደረገው። ፓሻውም የመጀመሪያውን መጠን እዚያው በዚያ ሰዓት ለመውሰድ የሙጢኝ አለ።

«እስከ ብዙ ሣምንቶች እፎይታ አገኛለሁ ብለው አያስቡ» አለ ጆን ባፕቲስት

ይሁን እንጂ፣ ፈሣሽ መድሃኒት የመውሰዱ ጉዳይ በፓሻው ላይ አንዳች ሃይል ማሣደሩ አልቀረም። ኪኒን ከሚሠራበት የሲንቾና ዛፍ ቅርፊት የተዘጋጀለትን መድሃኒት ሲወስደው፣ ፊቱን እንደማጨማደድ አድርጐ ዕርካታ ካገኘ በኋላ፣ ባገኘው ነገር ሙሉ ደስታን እንዳገኘ

ሙሽራ ባል፣ በመከዳው ላይ ዝርግትግት አለ፡፡ ይሁን እንጂ አዕምሮው ሰላም ሲያገኝለትና የዕለቱን ሁኔታዎች ሲያስታውሳቸው ግንባሩን ቋጠረና ፊታ ሲያደርግ ፊር ማሣየት ጀመረ፡፡

«ያን ውሻ ፓትርያርክ አስጠራሁት» ሲል ጀመረ «ስለዘይቱ አንተ ትክክል ነበርክ፡፡ ሰውዬውም ተናዘዘልኝ፡፡ ዘይቱን ምን ማለት እንደሆነ ልነግረው ግድ ነበረ፡፡ ጀሉ፣ ከከፈሉት ወርቅ ባሻገር ማየት አልቻለም፡፡ እንዲያውም ከነገሠ አስራ አምስት ዓመት የሆነውን ንጉሠ ነገስት፣ ዘውድ ለማስጫን፣ ካቶቺኖች ይህን ያህል የሚያገባቸው ምን እንደሆነ ገርሞት ነበር፡፡ የዚህን ጉዳይ ሥረ-ነገር ፈፅሞ አላየውም፡፡ በኋው ጠያቂነት ዘበኛዬ በካልቾ እየመታው አዋርዶ ባያባርረው ኖሮ እስካሁን ሲያወሩ እንሰማቸው ነበር»

ፓሻው የሚያስተጋባ ግሳት ሲያጋሳ ይህን ያደረገለትን እግዚአብሔር አመሰገነና ቀጠለ፡፡

«እንዲሁም ደግሞ የፈንሣዩን ቆንሲልም አየኋቸው፡፡ አምባሣደሩን መጥራት አላስፈለገኝም፡፡ ምክንያቱም ከሁለት ቀናት በፊት ወደ አሌክሣንደሪያ በሚወስደው ጉዳና ላይ ሴት ልጃቸው ስለተጠለፈች ለዚህ ሲሉ አቤት ለማለት መምጣታቸው አይቀርም»

ጆን ባፕቲስት የደነገጠ መሆኑን ለማሣየት ሞከረ፡፡

«ታውቃት ነበር?» ሲል ፓሻው ጠየቀው፡፡

«በዓይን ብቻ ነው፡፡ ለዚያውም ቆንስላው ግቢ ውስጥ ነው፡፡ በጣም ውብ ልጃገረድ ነበረች፡፡»

«እንዲህ ሆነ ብለው ነገሩኝ፡፡ ለአምባሣደሩ ልነግራቸው የምችለው እጅግ አሳፋሪ ነገር እንደገጠመኝ ብቻ ነው፡፡ ምናልባትም ጠላፊዎቹ ዘራፊዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ መንገዱን የሞሉት እነርሱ ናቸው፡፡ ጠላፊዎች ያልወሰዷት፣ግን በሰረገላው ውስጥ የነበረች ሌላ ሴት በኋላ ላይ ስለድንነተኛ አደጋ አድራሾቹ ገለፃ ሰጥታለች፡፡ ሴትዮዋን ያልወሰዷት ልጅነት ስለሌላት ይሆናል፡፡ በሴትዮዋ አገላለፅ ሰዎቹ ማንንም ሊመስሉ የሚችሉ ናቸው፡፡ ሁለት ግዙፍ ወንዶች ናቸው፡፡ ሁለቱም ጥምጣም አስረዋል፡፡ ሪዛቸው ጥቁር ነው፡፡ የሚምሉት በአላህ ነበር፡፡ ልጅገረዲቱን፣ አንደኛው በፈረሱ ላይ አፈናጥጧት፣ በሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ ሄዱ፣ ስትል አስረድታለች፡፡ ምናልባት በድብቅ በጀልባ ወደ ቆጵሮስ ሲያሻግሯትና ከዚያም በባልካን አገሮች ወይም ሌላ ቦታ በሴትኛ አዳሪነት ሕይወቷን ትቀጥላለች» አለ ፓሻው

«ምስኪን ልጅ» አለ ጆን ባፕቲስት ፈጠን ብሎ፡፡



«አዎን፣ ግን ምንም ባያጋጥማትም ኖሮ በቀረው ዘመኗ የደስታ ሕይወት አይኖራትም ነበር»

«ለምን ቢባል?»

«ወደ ሴቶች ገዳም እንደምትገባ አባቷ ነግረውኛል፡፡ ዶክተር፣ ላንተ በሁሉም ረገድ አክብሮት አለኝ፡፡ ነገር ግን ክርስቲያን ስለሆንክ በናንተ እምነት በኩል ሊገቡኝ የማይችሉ ነገሮች አሉ፡፡ ይህን ሁሉ ሴት፣ ለእግዚአብሔር አገልጋይ ይሁን በማለት ብቻ ለምን ዘግታችሁ ታኖሩታላችሁ፡፡ በርግጥ እግዚአብሔር ይፈልጋቸዋል ብላችሁ በእውነት ታምናላችሁ? ሁለቱን ፆታዎች ሲፈጥራቸው እንዲዋሃዱ አይደለም? ስለሁኔታው ቆንሲሉ ሲገልፁልኝ በማንኛውም መልክ ተዘግቶባት የምትቀረው ይህች ልጅ በዙሪያዋ አሁን ላሉት የሰው ልጆች አንዳች መልካም ነገር ልታደርግላቸው ትችል ነበር ብዬ ልነግራቸው ዳድቶኝ ነበር፣ እና፣ተወው ይልቅስ ጨዋታችንን እንቀጥል፡፡ የዚህ ሁሉ ፍፃሜው ታዲያ፣ ሙሴ ዴ ማይሌ በከፍተኛ የመንፈስ መረበሽ ውስጥ መውደቃቸው ነው፡፡ እንዲያውም ሊምባሲያቸውንም ፈፅሞ የረሱት ይመስላል፡፡ ይመስላል ያልኩበት ምክንያት፣ እኔ ስለጉዳዩ አንዳች ነገር እንዲነግሩኝ ስጠይቃቸው፣ እርሳቸው ጉዳዩን ሙጭጭ ይሉብታል፡፡ አንተ ሁሉንም ነገር ግልጥልጥ አድርገህ ካሣየኸኝ ወዲህ፣ ሰውዬው ለዚህ ስራ ያላቸውን ጠንካራ ፍላጎት በተሻለ መረዳት ችያለሁ»

ጆን ባፕቲስት የተረጋጋ ስሜት ይዞ ቆየ፡፡ የቤት ውስጥ ተላላኪው፣የሚበላ ኬክና ሻይ ይዞ ከተፍ አለ፡፡

«ቀትር ላይ ጋደም በማለት ለመተኛት ብሞክርም እምቢ አለኝ፡፡ ይህን አታምንም ይሆናል፡፡» ሲል ፓሻው ቀጠለ፡፡ «እየተካሄደ ያለው ነገር ሁሉ በአዕምሮዬ ውስጥ እየተሽከረከረ ነው፡፡ ዶክተር? አንድ ነገር ልናዝዝልህ፡፡ ከዚያ በኋላ የራሴንም ማንነት በሚገባ አሳውቃለሁ፡፡ ጠላቴን ማየት ስለቻልኩ አንተን አመሰግንሃለሁ፡፡ ይህ ደግሞ በራሱ ታላቅ ነገር ነው፡፡ ይሁንና ጠላቴን እንዴት አድርጌ ነው መምታት ያለብኝ? በአሁኑ ጊዜ በጦርነት ሜዳ ውስጥ አይደለንም፡፡ ታዲያ ምን ሳደርግ እችላለሁ? የአገራችን ከፍተኛው የአመራር አካል፣ ከፈረንሣዮች ጋር እንዴት እንደሚሠራ ታውቃለህ፡፡ ሁልጊዜም ድርድር ነው የሚያደርገው፡፡ የገመድ ጉተታ አይነት፣ አንዱ ሌላውን በመቃረን ብቻ፤ ውጤት አልባ ነው፡፡ ታዲያ ይህ ሁሉ ወዴት እያመራ እንደሆነ አሁን እያየን ነው፡፡»

ሲናገር ወደ ጆን ባፕቲስት እየተመለከተ አልነበረም። ጆን ባፕቲስትም መናገር የሚገባው ጊዜ እስኪደርስ በትዕግስት ጠበቀ።

«ለታላቁ መሪያችን ሁኔታውን ሪፖርት ባደርግ ምን ሊሆን እንደሚችል አውቃለሁ። ማረጋገጫ ማስረጃ ይጠይቁኛል። እኔ ላቀርብ የምችለው ማንኛውም ማስረጃ በቂ አይደለም ተብሎ ይፈረጃል። ስለዚህ ተጨማሪ ይጠይቁኛል። በዚህ ሁሉ ጊዜ ውስጥ ቀኑ ቀንን እየወለደ ጊዜው ይገፋና እነርሱም ያንን የተረገመ ዘይት በዱ ሮውሌ ግንባር ላይ በማፍሰስ ንጉሠ ነገስት ብለው ዘውድ ይጭኑለት ይሆናል»

ጆን ባፕቲስት ባይፈልግም ራሱን በመነቅነቅ ተስማማ

«በሌላ በኩል በራሴ ውሣኔ በፈረንሣውያኑ ላይ እርምጃ ብወስድ፣ ቆንሲሉ አስፈሪ ምሬት ሊያሰሙ ይችላሉ። ቁስጥንጢንያ ደግሞ እኔን መርዳቷን መናገር አይቻልም። ይህን ጉዳይ በተመለከተ ለረዥም ጊዜያት አጥብቄ አስቤበት ነበር። የበቀል ጥቃትን ሳልፈራ፣ልይዛቸው የምችላቸው፣ ካፑቺኖች ብቻ ናቸው። በዚህ ውሣኔዬ ረክቼ ቀጣዩን ለሊት በሰላም ለማደር ወታደሮቼን ወደ ሲናር እልካለሁ። ከዚያም በማግስቱ ወታደሮች አስረው እንዲያመጧቸው በዚያውም ቅብዓ ሜሮኑንና የፖትርያርኩን የምስክር ወረቀት መልሰው ያመጣሉ። ለመባረር በሚገባ የተመቻቹ ስለሆነ፣ ማንም ጠንካራ ተቃውሞ የሚያነሣ የለም። ግን የፈረንሣዮችን ቅፍለት ምን ላደርገው ነው? ዶክተር፣ አንተ የታላቅ ጥበብና ብልሀት ባለቤት ነህ፣ እንዲያው ስለዚህ ጉዳይ ምን ትለኛለህ?»

ጆን ባፕቲስት ይጠብቀው የነበረው ሰዐት ይህን ነበር። ሁለት ጊዜ ከሻዩ በዛ አድርጐ ከተጐነጨ በኋላ መልሱን ለማቀናበር ወይም የሚያቀናብር ለመምሰል ጊዜ ወሰደ። እንደ እውነቱ ከሆነ መልሱን ቀደም ሲል አዘጋጅቶ ነበር። እናም ጥያቄ አስመስሎ በጥንቃቄ ጣል አደረገ።

«ምናልባት የሲናር ንጉስ አንድ ዓይነት ርምጃ ይወስዱ ይሆናል?»

«የለም፣ ኦፊሴላዊ የሆነን የፈረንሣይ ኤምባሲ በማጥቃት አደጋ እንዲገጥመው ፈፅሞ አይፈልግም።»

«ሕዝባቸው በራሱ ፈቃድ ካላደረገው በስተቀር . . . »

«ምን ማለትህ ነው?»

«እኔ ሲናር በነበርኩበት ጊዜ፣ ካፑቺኖች ህዝቡን በኔ ላይ ለማነሣሣት ማስፈራራት አስበው ነበር። ማድረግ የነበረባቸው፣ እኔን አስማተኛ ነው የሚል ጥላሸት መቀባት ብቻ ነበር። የሲናር ሰዎች አስማተኛን በጣም ስለሚፈሩ፣ ሊያምኑ ምንም አልቀራቸውም ነበር። በዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ስጋት ያደረበት ሕዝብ፣ በራሱ ተነሣሽነት በማያውቀው የተጓዥ ቡድን ላይ ቁጣ ሊቀሰቅስና ማንም ሰው፣ ሌላው ቀርቶ ንጉሡ እንኳ ቢሆኑ ሊቆጣጠሩት የማይችሉት ረብሻ ሊያነሳ ይችል ነበር»

በፈረሰኛ ወራጅ ወንዝ ውስጥ ሆኖ፣ነፍሱን ለማዳን ሲል ያገኘውን ሀረግ ሁሉ ለመያዝና ወደዳር ለመውጣት እጆቹን እያወናጨፈ እንደሚጥር ሰው፣ ፓሻው ይህን የሣሣብ ሰንሰለት ተከተለው። ሣሣቡን ሰብሰብ አድርጐ አዕምሮን ከገዛ በኋላ፣ እንዲህ ያለ ግልፅ ፈረንጣዊ በማግኘቱ ራሱን በራሱ የምስራች አለው።

ከዚህ በኋላ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ተከታታይ ጥያቄዎችን ጠየቀው። ጆን ባፕቲስትም በቀላሉና ግልፅ በሆነ መልክ መለሰለት።

«ልክ አስቀድመህ መልሱን ያዘጋጀኸው ነው የሚመስለው» ሲል ፓሻው በጥርጣሬ ሳይሆን በታላቅ የአድናቆት ስሜት ተናገረ

የሚያጤሰው ፒፖ እንዲመጣለት በማዘዝ፣ ያንን እየማገ በደስታ ተነፈሰ። ጆን ባፕቲስት፣ ቀጥሎ የሚሆነውን ጠበቀ። ፓሻው ሲናገር ሲል፣ የፒፖው ጭስ በተሣሣተ መተንፈሻ አካሉ በማለፉ በድንገተኛ መረበሽ ሳሉ ተቀሰቀሰበት።

«ከዚያ ኩርድ ጋር በመንገዘ ላይ ስላሉት ምሁራንስ ምን ትላለህ?»

«እነርሱን ለኔ ይተዉቸው ጌታዬ፣ እኔ እከታተላቸዋለሁ።» አለ ጆን ባፕቲስት

ፓሻው በአግራሞት ተንቀሣቀሰ

«እስከ ጂዳ ድረስ የሚያጅቡኝን ሰዎች፣ግብፅ ውስጥ እስካለሁ ድረስ ምናልባት ለቆንሲሉ ስሜን የሚያሳጣብኝ እንዳይኖር መከላከያ ይሆነኝ ዘንድ የርስዎን ከለላ ይስጡኝ። በአሁኑ ጊዜ በይፋ እኔ ፈረሰኛው ዱ ቫውዴ ሶርጌስ ነኝ። እርስዎ፣ኦፊሴላዊ ዋሴ ቢሆኑኝ፣ ያለ አንዳች ፍርሃት የትም መሄድ እችላለሁ። ስድስቱንም ሰዎች ፍፁም ኢትዮጵያ ሳይደርሱ በፊት እንደማገኛቸው ይመኑኝ»

ከረዥም የማቅማማት ጊዜ በኋላ ቆርኳዊው ተናገረ

«ይህ ከጥያቄ ውጪ ነው»

ጆን ባፕቲስት ዓይኖቹን በሽማግሌው ጠረኛ ላይ ተክሎ ተንቀሳቀሰ

«እየሁ፣ እኔ ያለሃኪም መቆየት አልችልም» አለ ፓሻው።

ግንዲላው ቀስ እያለ በመንጣጣት እየነደደ ምድጃውን በአመድ ዱቄት እየሞላው ነው።

«ጌታዬ፣ እጅግ ቢበዛ አራት ሣምንታት ቢወስድ ነው። ለርስዎ የሚሆን ቢያንስ ለሦስት ወራት ሊያገለግልዎ የሚችል መድሃኒት አዘጋጅቼ እተዉልዎታለሁ። ምንም እንኳ አሁን የታመመ ቢሆንም፣ አስፈላጊ ከሆነ ሜትር ዣረሚ ይከታተልዎታል»

«በምስራቅ በኩል ወረርሽኝ የመነሣቱ ነገር ይወራል። የኢስማኢሊያ ከተማ ተገልላ እንድትቆይ ተደርጋ ነበር። አንተም ብትሆን ታመህ ልትተኛ ትችላለህ»

«ይህ እዚህም ሊደርስ ይችላል። ሁላችንም ብንሆን በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ ነን» አለ ጆን ባፕቲስት ካንጀቱ ሳይሆን ካንገቱ

«እውነቱ ይህ ነው።» ብሎ ፓሻው በረዥሙ ተነፈሰ። ከዚህ በኋላ ፖንሴ ያቀረበውን ሃሣብ በአማራጭ ካሉት ሃሣቦች ጋር ካመዛዘነ በኋላ የትኛውም ባያስጨንቀውም ተስማማ።

አሁን ሁሉም ነገር መፍትሄ አግኝቷል፣ወይም በቅርቡ ውሣኔ ያገኛል። ትምባሆው ከሰጠው የርካታ ስሜት፣ የመከዳው ልስላሴና ምናልባትም ደግሞ ከመድሃኒቱ የተነሣ የሽማግሌውን ቁርካዊ ሰውነት ባለፉት ሁለት ቀናት ከነበረው የከረረ ሁኔታ ጋር ሆኖ የድካም ማዕበል መታው።

ጆን ባፕቲስት ቀደም ብሎ ተሰናበተ። ፓሻው ወደ አልጋው ከመሄዱ አስቀድሞ ሲናርን በተመለከተና ዶክተሩን እስከ ጂዳ ድረስ አጅቦ ስለሚሄደው ሠራዊት ትዕዛዝ ሰጠ።

❧

ፈረሰኛው ዴ ቫውዴ ሶርገስ በሸክላው የአረብ ፈረሱ ላይ ተሽሞንሙኖ ተቀምጦ፣ በካይሮ ከተማ ውስጥ አለፈ። በየፎቅ ቤቶቻቸው መስኮቶች ላይ ሆነው እርሱንና የክብር አጃቢዎቹ የሆኑትን የጠመጠሙና ጉራዴዎቻቸውን የታጠቁ ወታደሮቹን በአድናቆት ቁልቁል የሚመለከቱትን የቤት እመቤቶች፣ ፊቱን ወደነርሱ ቀና በማድረግ ባርኔጣውን ያነሣላቸዋል። ዕለቱ ሞቃት ሲሆን፣ አዕዋፍት በብዛት በሰማዩ ውስጥ ይበርራሉ። በተለያዩ የሲጋጃ ምንጣፎች፣ የመዳብ ቁሣቁሶችና የሸፈት ዕቃዎች ቀለማት በሚያብረቀርቁበት የንግድ ሱቆች



መሃል ሠራዊቱ አለፈ። እነዚህን ከየመደብሩ ወጥተው በጉዳናው ዳር የተደረደሩ ቁሳቁሶችን፣ ረገዥም ሰማያዊ ጥቁር ካባ ለብሰው፣ ጠርቡሽና አይነርግብ ያደረጉ አሳፊ አግዳሚዎች በእጆቻቸው ይነካኳቸዋል።

እነዚህ ተጓዦች እስከ ስዊስ ሲሄዱ አንዳችም ቃል ሳይተነፋፈሱ ነበር። ሌላው ቀርቶ፣ ከፍተኛዎቹ አጃቢ ወታደሮች፣ ይህን እጅግ የተከበረ በማለት የተከተሉትን ሰው በመፍራት፣ ፀጥታውን ሊሰብሩት አልደፈሩም። ጆን ባፕቲስት ወደፊት የሚጠብቀውን ስራ በአዕምሮው እያውጠነጠነ ሊያናግራቸው አልቻለም። አዕምሮው ዕረፍት እንዳገኘ ግን አሊስንና በዚያ ምድረበዳ ውስጥ የምታደርገውን ሽሽት አሰበ። ጆን ባፕቲስት፣ በርስዋ፣ በዣረሚና በፍራንቾይዝ ላይ መተማመን ነበረው። ከሁሉም በላይ ግን በራሱ እጣ ፈንታ ላይ ከፍተኛ መተማመን ነበረው።

በመጨረሻም መራራውን ሐይቅ አልፈው፣ ሴራፒየምን ከርቀት ተመለከቱ። ሁለተኛውን የጉዞ ዕለት ሊያጠናቅቁ ጥቂት ሲቀራቸው፣ ትንሿን የስዊዝ የወደብ ከተማ ከባህሩ ጠርዝ ላይ ተመለከቱ። በዚህ አካባቢ ያለው የስዊዝ ወደብ፣ የኢጣሊያ ሐይቆችን ያህል ጥብብ ያለ ነው። ወደቡ፣ ነጫጭና ግራጫ መልክ ባላቸው ጀልባዎች የተሞላ ሲሆን ከሰሜን ምስራቅ በኩል ለስላሣ ነፋስ ይነፍሳል።

በአጃቢ ወታደሮቹ ጥያቄ መሠረት፣ የወደቡ አዣዥ የሆነው ጢማሙ፣ፍልቅልቅ ሊባኖሳዊ፣ ሊጠቀሙባቸው የሚችሏቸው ባለሁለት ሸራ ጀልባዎችን ሰጣቸው። ቀድሞ የንግድ መርከብ የነበረችው ይህችው ጀልባ፣ ሁለት መድፎች ተጨምረውላት ወታደራዊ አገልግሎት እንድትሰጥ ተደርጋለች። የዚህችው መርከብ ሠራተኞች ቱርካውያን ወታደሮች ሲሆኑ፣ በአፈ-ታሪክ እንደሚነገሩት የባህር ላይ ባለችሎታ ሰዎች፣የተቀጣላቸው ናቸው። የአጋጣሚ ሆኖ ለወታደሮቹ አስፈላጊውን ስንቅና ትጥቅ የሚያቀርበው ክፍል አዛዥና ብዙዎቹ ሰዎች በቀን አምስት ጊዜ እየፀለዩ፣በመሃመድ አምላክ የሚያምኑ ቢሆኑም እስከ አሁን ድረስ የአሪስቶፊኔስን ቋንቋ የሚናገሩ ናቸው።

መርከቧ፣ በባህረሰላጤው ዳር ምንም አይነት ድንገተኛ ነፋስ ወይም ፍፁም ፀጥ ያለም ነፋስ ሳይገጥማት በሰላም ተጉዛ የሲናን ተራራ አለፈች። በአካባ ባህረ ሰላጤ ዳር ሆኖ አካኋ በጭጋግ ውስጥ ተሰይቶ ይታወቃል።

በአካባ ባህረ ሰላጤ ጠርዝ ላይ፣ የባህሩ ውሃ እንቅስቃሴ የሞገድ ለውጥ ይታይበታል። ቀን ላይ ርጥቡ የጀልባዋ ክፈፍና ጠርዝ፣ የመርከበኞቹ ፊትም በፀሐይዋ ብርሃን ውስጥ ያብረቀርቃሉ። ምሽቱ አሁንም ቀዝቃዛና ሃይለኛ የነፋስ ማዕበል አለው። መንገደኞቹ፣ በጉዟቸው ላይ አንድ ጊዜ ብቻ በወደብ ዳር ከማረፋቸው በስተቀር በአምስተኛው ቀናቸው ንጋት ላይ ጂዳ ደረሱ።

የካይሮው ፓሻ፣ አድራሻው ለመካው ሸሪፍ የሆነ የይለፍ ወረቀት ሰጥቶት ስለነበረ፣ ፈረሰኛው የአክብሮት አቀባበል አገኘ። ከዚያም ማርቆስ በሚባል ሶሪያዊ የኦርቶዶክስ ክርስቲያን ንብረት በሆነ ትንሽ ሆቴል ውስጥ እንዲያርፍ ተደረገ። ቦታው ከቀሪው የከተማው አካል ትንሽ ራቅ ብሎ ከአሸዋው መሬት ጠርዝ ላይ በሚገኙ ጥቂት የዘንባባ ዛፎች አጠገብ የተመሠረተ ነው። ይህ ቦታ ክርስቲያኖች እንዲሰነብቱበት የሚፈቀድ አካባቢ ነው።

የዚህ ትንሽ ሆቴል ጓሮ፣ በአጥር ወደ ተከበበ የአትክልት ቦታ መግቢያ አለው። ወደ አትክልቱ የሚወስደው መንገድ በጡብ የተሠራ ሲሆን፣የብርቱካንና የሮዝ አበባ ተክል ያላቸው አፅዋት በሚያምር መስመር ተተክለውበታል። በዚህ ቦታ ላይ፣ ጆን ባፕቲስት፣ ይሆን ይሆናል ብሎ የጥርጣሬ ስሜት ይዞ ነበርና ይህ ሃሣቡ ስህተት አልነበረም። ወደ አትክልት ሥፍራው ውስጥ ብዙም ሳይራመድ በፊት ሙራድ በአንድ መከዳ ላይ ተቀምጦ የውሃ ጋያውን ሲያጨስ ተመለከተው። ከርሱ ባሻገር ስድስቱ ምሁራን ፅጥ ብለው በክብ ቅርፅ ተቀምጠዋል። እያንዳንዳቸውም መፅሃፍ ይዘዋል

ጆን ባፕቲስት፣ በፈረሰኛው ዴ ሻውዴ ሶርገስ ሚና፣ ራሱን በኩራት ጉንበስ በማድረግ አስተዋወቀና ጆርባውን ለሙራድ ሰጥቶ ተቀመጠ። ወዲያውም የሚጣፍጥ የቱርክ ቡና አዘዘ። በርሱ ጥያቄ መሠረት አጃቢ ወታደሮቹ የሉም። እርሱ ከሚፈልገው ቦታ በመድረሱ ሳቢያ ስለማይፈልጋቸው፣ ወታደሮቹ በከተማዋ ውስጥ የየራሣቸውን ክፍሎች ተከራይተዋል። ጂዳ፣ የቅዱሱን ቦታ ተሣላሚዎች መጓጓዣ መንገድ ላይ ስለሆነች እንቅስቃሴ የሞላባት፣ በጥብቅ ሥርዓቷ ውስጥ ሁሉንም ዓይነት ምቾት የያዘች ከተማ ነች። ጆን ባፕቲስት፣ ለአጃቢ ወታደሮቹ አለቃ፣ ሁለት ሴኩይንስና ለሌሎቹ ደግሞ አንዳንድ ሰጣቸው። ይህ ገንዘብ ሁለት ክሩሳዶስ ማለትም ሃምሣ ስድስት ሴሪፊንስ ይሆናል። ወይም በሌላ አገላለፅ አንድ መቶ አሥራ ሁለት ፓርዳይስ ወይም ሁለት ሺህ ሁለት መቶ አርባ ታንጋ ወይም ስድስት ሺህ ሰባት መቶ ሃያ ባሩክስ ይሆናል። ይህ በወቅቱ በቀይ ባህር ዙሪያ በማገልገል ላይ የነበረ ገንዘብ ከብረታ ብረት የተሠራ ሣይሆን፣ በቬኒስያ መስታወት ስብርባሪ የተሠራ ነበር። በአጭሩ፣ ጆን



ባፕቲስት እነዚህን ሰዎች በአንድ ጊዜ ባለፀጋ አድርጓቸዋል። ወደ ከተማውም በኩራትና በጥድፊያ እየተቧደኑ ወጡ። እግዚአብሔር በዚህ ገራገር ሰው ላይ አድሮ፣ ሕይወት የምትከፍላቸውን ውለታ እንዲቀምሱት ፈቃዱ ሆኗል።

በዚያን ዕለት ምሽት፣በትንሿ ሆቴል ቤት ውስጥ የነበሩት እንግዶች በሙሉ ነጭ ቀለም በተቀባ በአንድ ትልቅ የምግብ አዳራሽ ውስጥ ራታቸውን በፀጥታ ተመገቡ። በዚህ አዳራሽ ውስጥ ይታይ የነበረው ብቸኛው ጌጥ፣ ዝገት የበላው የጥንት የፈረሰኛ ጉራዴ፣ በሁለት ሚስማሮች ላይ ተንጠልጥሎ ነው። ዕራት ተመጋቢዎቹ፣ ሻማዎቻቸውን ይዘው ወደየክፍላቸው ሲሄዱ፣ ከበላያቸው ያለው ወለል ሲንሳጠጥ ድምፁ ይሰማል። ሙራድ፣ ሁልጊዜም እንደሚያደርገው ልማዱ፣ ሌሎች ተመጋቢዎች ያስተረፉትን ምግብ እስኪያፀዳ ድረስ ከገበታ ሳይነሳ ስለሚቆይ ብቻውን እስኪሆን ድረስ ጆን ባፕቲስት ጠበቀ። ወዲያውም ከአርመናዊው አንፃር ተቀመጠ።

«ጌታዬ!» አለ ጆን ባፕቲስት፣ በአረቢኛ

ሙራድ የቅርቡን ብቻ እንደሚያይ ዓይኑን አንሸዋርሮ እንደመጓጓት አይነት ጉንበስ አለ።

«ባልሣሣት አምባሣደር ሙራድ ነዎት» አለ ጆን ባፕቲስት

«እህ!ይህን እንዴት ሊያውቁ ቻሉ?»

አርመናዊው ሻማውን አንስቶ ወደሚያዋራው ሰው ፊት ጠጋ አድርጎ ያዘው።

«እንዴ . . . ፍፁም እሱን ይመስላሉ . . . ለመሆኑ አንተ ጆን ባፕቲስት ነህ እንዴ?»

«እሸሸ! እኔ ፈረሰኛው ዴ ሻውዴ ሶርገስ ነኝ»

«አ! ይቅርታ» አለ ሙራድ ተስፋ ቆርጦ «ሳስብም»

«የለም፣ አንተ ደደብ፣ እኔው ነኝ። ነገር ግን በዚህ ሁሉ ሰው ፊት እንደምታምባርቅ፣ በተለይም በአዲሶቹ ጓደኞችህ ፊት»

«ጓደኞቼ አይደሉም። ስላንተ ምንም ወሬ አጣሁ። እነርሱ ደግሞ ስለአቢሲኒያ ማወቅ ይፈልጋሉ . . . »

«ካይሮን ለቀህ በመውጣትህ ትክክል ነገር ሠርተሃል ሙራድ» አለው ጆን ባፕቲስት ፈገግ እያለ

አንዲት የተከደነች የመዳብ ኩዳ አውጥቶ ንፁህ ፈሳሽ በሙራድ ባዶ ስኒ ውስጥ ከጨመረ በኋላ ለራሱም ቀዳ።

«ብራንዲ ነው!» አለ አርመናዊው። «አረቢያ ውስጥ ያውም በነብዩ ምድር ላይ! አትፈራም እንዴ?»

ብርጭቆዎቻቸውን በዝግታ አጋጭተው ወደ ጣሪያው አፈሰሱ።

«አዎን፣ እፈራለሁ፣ ስላንተ ስል እፈራለሁ» አለ ጆን ባፕቲስት

«ምን ማለትህ ነው?»

«ወደ ምፅዋ ልትሻገር ነው አይደል?»

«የሜካ ሸሪፍ የነዚህን ክቡራን ሰነዶች ማህተም እስኪመቱበት ድረስ ሁለት ሦስት ቀን ይፈጃል»

«ናኢቡን ካየሃቸው ረዥም ጊዜ ነው?»

«አዎን፣ ድንቅ ሽማግሌ ናቸው»

«በአሁኑ ጊዜ እዚያ የሉም»

«እውነት ነው። መቼም ጨካኙ ሙሃመድ እንዳይሆን»

«የለም፣ ሙሃመድ ሞቷል። ከእንግዲህ ግንኙነትህ ከወንድሙ ልጅ ከሃሰን ጋር ነው። ሃሰን የባሰ ጨካኝ ሲሆን፣ ለፈረንሣውያን ካህናት ያለው ጥላቻ ወሰን የለውም»

«እና ይህ ታዲያ ለኛ ምናችንም አይደለም። ንጉሡ ራሣቸው፣ ፈቃደኛ ሆኖ የሚመጣ ከተገኘ ምሁር ይዤላቸው እንድመለስ ነግረውኛል»

«ምሁራን? ልክ ነው። ነገር ግን ጀስዊቶችስ?»

«ምን? ምን እያልክ ነው?» አለ ሙራድ

ጆን ባፕቲስት፣ የአርመናዊውን ኮሌታ ጨምድዶ ፊቱን ወደ ፊቱ አስጠጋ።

«የምልህማ፣ስድስት ንፁህ የጀስዊት ደም ያላቸውን ሰዎች ወደ ምፅዋ እየመራህ ነው። ይህን ለማስተዋል እንዳትችል አንተ ተንኮል የሌለብህ ሰው ነህ። በዚህ የተነሣ ናኢቡም



አይጠነክሩም። ንጉሠ ነገስቱም ቢሆኑ ስድስት ሰዎችን ይዘህላቸው ስትመለስ፣ ሃይማኖታቸውን እንዳያስለወጧቸው እንጂ ሌላ የሚጠረጥሩት ነገር አይኖራቸውም። ታስታውስ እንደሆነ አንድም ጀስዊት ወደ አገራቸው እንዳናመጣባቸው አስምለውን ነበር። አንተ ግን ግማሽ ደርዘን የሚሆኑትን በሻንጣህ ተሸክመህ እየተመለስክ ነው»

ሙራድን ሲለቅቀው የተመታና የደነዘዘ ያህል ተመልሶ ወንበሩ ላይ ወደቀ።

«እኔ ጠፋሁ» አለ አርመናዊው

እንደ ህፃን ልጅ በዝምታ ማንባት ጀመረ።

«በቃህ» አለው ጆን ባፕቲስት፣ ብርጭቆ ሙሉ ሌላ ብራንዲ እየቀዳለት።

ሙራድ በአንድ ትንፋሽ ጨለጣትና ብርጭቆውን አስቀምጦ ከበፊቱም የባሰ ያዘነ መሰለ።

«ወይኔ! ራሴን በራሴ መከራው፣ ካይሮ ውስጥ የፀጥ ቤት ሰራተኛነት ሥራ ብጀምር ይሻለኝ ነበር። የሚገባኝም ነገር ይኸው ነበር። ይህ የሃይማኖትና የፖለቲካ ነገራችሁ ግራ ያጋባኛል»

«ስማ ሙራድ። የምነግርህን ከፈፀምክ የምትፈራው አንዳችም ነገር የለም። ንጉሠ ነገስቱም ባንተ ላይ ያላቸውን እምነት ስለሚያረጋግጡ ሌላው ቀርቶ ከፈለግህ አንተው ራስህ የወጥ ቤታቸው ልትሆን ትችላለህ»

ሙራድ፣ምንም ሣይናገር አየር ወደ ሣንባው ከሣበ በኋላ፣ ቀስ ብሎ ብርጭቆውን ጠረጴዛው ስር አስቀመጠው። ጆን ባፕቲስት ወደ ማዕድ ቤቱ ከተመለከተ በኋላ ሌላ ማደፋፈሪያ ቀዳለት።

«ነገ ጧት ከንጋት በፊት ወደ ወደቡ ውረድ።» አለው ሃኪሙ። «የምትፈልገውን አይነት ጀልባ ከነካፒቴኑና ከሠራተኞቹ ጋር ልትከራይ እንድትችል አንድ ወቄት ወርቅ እሰጥሃለሁ። ቀይ ባህርን አቋርጠህ ወደ ናኢቡ ሒድ። እዚያም ደርሰህ፣ ስድስት ጀሰዊቶች ወደ አገራቸው ሊገቡ እንዳቀዱና አንተ ግን ዕድለኛ ሆነህ ልታመልጣቸው እንደቻልክ ንገራቸው። ከዚያም ወደ ጐንደር ተጓዝ። ለንጉሠ ነገስቱ ሰላምታዬን አድርስልኝ። የፈረንሣዮች ንጉስ፣ ኤምባሲያቸውን እንደተቀበሉና ምርቃታቸውን መላካቸውንም ንገራቸው።

ያንተም ተልዕኮ እዚያ ላይ ያበቃል። ከዚያ በኋላ ወደ አጐትህና ወደ ወንድሞችህ ልጆች ዘንድ መሄድ ትችላለህ። በቀሪው ዘመንህም ደስተኛ ሆነህ እንደምትኖር ተስፋ አደርጋለሁ»

«ጀስዊቶችስ?» ሲል በስማቸው ቃላትና በሶስቱ ብርጭቆ ብራንዲ የተደሰተው ሙራድ ጠየቀ።

«የነርሱን ሃላፊነት እኔ እወስደዋለሁ»

«እና . . . አንተስ?»

«እኔ ደስተኛ ሰው ነኝ፣ ወዳጄ። ከዚህም በኋላ እጅግ በጣም በቅርቡ ደስተኛ እንደምሆን ተስፋ አለኝ»

«እምነትህስ?»

«አብሬአት ለመሆን እየተንቀሳቀስኩ ነው። ማን ያውቃል? አንድ ቀን ጉንደር ውስጥ ታየን ይሆናል»

ለሁለተኛ ጊዜ መልካም ምኞታቸውን ተለዋወጡ። ጆን ባፕቲስት፣ ከአነስተኛዋ ነጥብ ጀምሮ ቀደም ሲል የነገረውን መመሪያ በዝርዝር ደገመለት። እኩለ ለሊት አካባቢ ሞቅ ባለ መተቃቀፍ ሰላምታቸውን ተለዋውጠው ተለያዩ።



# 9

በሚቀጥለው ቀን፣ ጆን ባፕቲስት፣ በትንሿ ሆቴል ውስጥ ባሉት በስድስቱ እንግዶች ላይ የቅርብ ክትትል ሲያደርግ ዋለ። ሙራድ ከመኝታው ዘግይቶ የሚነሣ በመሆኑ፣ ሰዎቹ ይህንን ስምደዋልና ጨርሶ አለመኖሩን ያስታውሱት እኩለ ቀን አካባቢ ነው። ከመካከላቸው አንዱ የሙራድን ክፍል በር ለማንኳኳት ሄዶ፣ በከፍተኛ ጭንቀት በረዳውን እየወረደ ተመልሶ መጣ። ባለፈው ምሽት በጆን ባንቲስት የተሰጠውን መመሪያ በመከተል ሙራድ የቃል ማስታወሻ ለባለሆቴሉ ነግሮታል። በዚህ ማስታወሻውም ከተማ ውስጥ ሥራ እንዳለው፣ ማንኛውም የውጭ አገር ዜጋ የተለየ መብት ካልተሰጠው በስተቀር ወደ ከተማ መግባት እንደማይፈቀድለት በመግለፁ፣ ስድስቱ ጀስዊቶች በትዕግስት በመጠበቅ ተጉላሉ። በአትክልቱ ስፍራ ውስጥና ወደ ወደቡ በሚወስደው አቧራማ መንገድ በተፈቀደላቸው አምስት መቶ ያርድ ርቀት ውስጥ ሲናፈሱ ዋሉ።

ቀኑ መሸ። ጀስዊቶቹ እንደገና ተመካከሩና እራታቸውን በፀጥታ ተመገቡ። የዚያን ዕለት ምሽት ከፖንሴ በስተቀር ሌሎች ደንበኞች በሆቴሉ ውስጥ አልነበሩም። ምግቡን በተቻለ መጠን በፀጥታ ከተመገቡ በኋላ፣ ሊጨርስ ሲል፣ ጆን ባፕቲስት ወንበሩን ገትቶ ወደ ምሁራኑ ጠረጴዛ በመሄድ የሚንት ሻይና ኬክ ሊጋብዛቸው ይችል እንደሆነ ፈቃዳቸውን ጠየቀ። ከአነስተኛው ውይይታቸው የተረዳው የአገሩ ልጆች መሆናቸውን እንደሆነ ሳይደብቅ ነገራቸው።

«ትችላለህ» አለው፣ ከስድስቱ ጨፍጋጋዎች አንዱ።

«እሺ እንግዲያው።» አለ ጆን ባንቲስት፣ እንፋሎታማውን ብርጭቆውን ብድግ በማድረግ፣ «በዚህ አካባቢ ለጤናችን ብለን ጽዋችንን የምናነሳበት ሌላ ዘዴ ስለሌለ ሻዩን አነሳሳችኋለሁ። እንደምታዩት ቀለሙ በጣም ወደ ክኛክ የሚጠጋ ስለሆነ እንደ መጠጥ አስቡት። ለጤናችሁ፣ ክቡራን ጌቶች»

እነርሱም ብርጭቆቻቸውን አነሱ። ጆን ባፕቲስት ለሰባታቸውም ተገቢ የሆነውን ቢገልጽም ከነርሱ አንዱም ደስተኛ አልነበረም

«እባካችሁ ይቅርታ አድርጉልኝ ራሴን ሳላስተዋውቃችሁም፣ ፈረሰኛው ሁጎ ዴ ቫውዴ ሶርገስ እባላለሁ። ላገለግላችሁም ዝግጁ ነኝ»

ይህን ካለ በኋላ፣ አስመሣዩ ፈረሰኛ ከወገቡ ላይ ጥቂት ኢንቾች ብድግ በማለት በተለይ ተለይቶ ባልተገለፀ መልክ በመጠኑ ጐንበስ አለ።

«እኛ ምሁራን ስንሆን፣ ለስፖኒሽ የሮያል አካዳሚ ኦፍ ሣይንስ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የተላክን ነን» ሲል ከእንግዶቹ ሽምግል የሚለው ጨፍጋጋ ተናገረ።

«እና ጉዟችሁ ወደየት የሚወስዳችሁ ነው?» ሲል ጆን ባፕቲስት በየዋህነት ጠየቀ።

ስድስቱ ሰዎች እርስ በርሳቸው በጭንቀት ተያዩ

«ወደ አቢሲኒያ» ሲል ቃል አቀባያቸው በመጨረሻም ተናገረ።

ፈረሰኛው የአድናቆት ፖኸት አሰማ።

«የማይታወቅ አገር ነው፣ ክቡራን፣ ለድፍረታችሁን እጅ እነሳለሁ።»

ለፍላፊው፣ የማይታመነውን አነጋገሪያቸውንና መንገድ መሪያቸውን ያጡ ስለሆኑ በዚያች ቅጽበት ከስድስት የተከፉ መንገደኞች ያነሰ ጀግንነት የሚታይበት አልነበረም።

«ምስጢር ካልሆነ አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ፣ ጌቶቹ?» ሲል ጆን ባፕቲስት ዝቅ ባለ ድምፅ ጠየቀ።

«መጠየቅ ካለብህ»

«እሺ እንግዲያው፣ ግን ጥያቄዬን ሳለመመለስ ከፈለጋችሁ አትገደዱምና ልትተዉ ትችላላችሁ። ለመሆኑ አግብታችኋል?»

የስድስቱንም እንግዶች ስሜት ምቾት የሚነሳ ድንጋጤ ወረረው። ለአፍታ ያህል ፀጥ ካሉ በኋላ ያው ሰው በመጨረሻ ላይ ተናገረ።

«የለም፣ አላገባንም፣ ባልደራስ»

«ይህ ድንቅ ነገር ነው። በጣም ድንቅ ነው» አለ ጆን ባፕቲስት

«ለምን ቢሉ ብሎ ቢጠየቅስ?» ሲል ከተንገሮቹ አንዱ ቆጣ ብሎ ጠየቀ። ከጠረጴዛው በስተግራ በኩል የተቀመጠው ይህ ሰው ጣልቃ ገቡን ሰው ከሌሎች ይልቅ በርጋታ ይመረምረው ነበር።

«ምክንያቱም፣ ወደዚያ የምትሄዱት የአገሪቱን ሃይማኖት ለማስለወጥ እንደማይሆን ትንባት ታህል ጥርጣሬ በአዕምሮዬ አይኖርም»



ስድስቱም በአንድ ጊዜ የመደነቅ ቃል ተናግረው ሲያበቁ፣ በጭንቀት ወደ ማዕድ ቤቱ በር ተመለከቱ። እንደ ዕድል ሆኖ የጆን ባፕቲስትን የድፍረት ንግግር ያዳመጠ አንድም ሰው አልነበረም።

ከተንገሮቹ መካከል ይበልጥ ለፍላፊ የሆነው ሰው «ማንነትህን ግለፅልን» ሲል ዝቅ ባለ ድምፅ ጠየቀው

«እንዳችም ቀላል የሚሆን ነገር የለም። አንዲት ትንሽ ታሪክ እነግራችኋለሁ። ያን ጊዜ ይገባችኋል። ታሪኩን የሰማሁት በሲናር ኗሪ የነበረና በጥቂት ራቅ ብሎ ወደ ኋላ ካለችው ወደ አቢሲኒያ አቅጣጫ ተጉዞ ከነበረ የካፑቺን ሚሲዮናዊ ነው። ነገር ግን ከሁሉ በፊት፣ ማነህ የኔ፣ አስተናጋጅ! ሻማዎች አምጣልን። ደግሞም አትሰስት፣ የምንከፍልህ ለዚሁ ሁሉ በቂ ነው»

ማርቆስ እያነከሰ ደረሰ። እንግዶቹ ጥያቄአቸውን ግልፅ እስካደረጉና ጮክ ብለው እስከተናገሩ ድረስ ለማስተናገዱ ሙሉ በሙሉ ዝግጁ ነው። ምክንያቱም ጆሮው እያስቸገረው ነው። ሶስት አዳዲስ ሻማዎችን እስኪያቀርብላቸው ጠበቁትና ተመልሶ ሲሄድ ፈረሰኛው ታሪኩን ቀጠለ።

«ታሪኩን ልቀጥልላችሁና፣ ይህ ሚሲዮናዊ ከዕለታት አንድ ቀን ጥቂት ጐጆዎች ያሉበትና ዙሪያውን በረዣዥም ሣሮች በተከበበ አንድ የሣር ምድር መንደር ደረሰ። እዚያም የመንደሩ ሽበቶ ጐምቱዎች በድንክ በርፖጫዎቻቸው ላይ በአንድ ትልቅ የዋርካ ዛፍ ሥር ተቀምጠው ያገኛቸዋል። ራሱንም በአረቢኛ ቋንቋ ያስተዋውቃል። የአገሬው ሰዎች በመጠኑ ቋንቋው ይገባቸዋል። የመንደሩ ሹም እንግዳውን ወደደው። የመንደሩም ሕዝብ ተቀበለው። ሁለት ቀናት ያህል ከቆየ በኋላ ስለራሱ ሃይማኖት መናገር ይጀምራል። ይህም ስገምተው ስለኛ ሃይማኖት ይመስለኛል»

ተንገሮቹ በታሪኩ በመስማማት ሳይሆን ጭንቅላታቸውን አነቃነቁ

«ሹሙ፣ ብዙ ተአምራቶችን በሠራው በኢየሱስ ታሪክ ከፍተኛ ስሜት አደረበት። የካፑቺኖችን ወዳጅነት እንደተደሰተበትና ስለሃይማኖቱም የበለጠ ለመማር እንደሚፈልግ ይነግረዋል። በዚህ መልክ ሁሉም ነገር በሰላም የሚዘልቅ መሰለ። ከዚያም ምሽት ሆነ። ምስኪኑ መነኩሴም ሊተኛ ሲዘጋጅ፣ የሹሙ ሴት ልጁ፣ በማደሪያ ጐጆው ውስጥ ሆና ስትጠብቀው አገኛት። ምንም ሳይናገርና ሳይነካት በአልጋው ግርጌ ሄዶ ተኛ። በማግስቱ በሌሊቱ ሁኔታ ያልተደሰተችው ልጃገረድ ለአባቷ ትነግረዋለች። «ምን?» ይላል ሹሙ።

«ልጁን ላለመቀበል ምን አይነት ሃሞት ቢኖርህ ነው ሳትቀበላት የቀረኸው? ካህኑ እፍረት እየተሰማው ሃይማኖቱ ሁሉንም ዓይነት ዝሙት እንደሚከለክል ለማስረዳት ይሞክራል።»

ስድስቱ ጀስዊቶች ጭንቀታቸው እየጨመረ አዳመጡ። ጆን ባፕቲስት፣ ጊዜ ወስዶ ትረካውን ከመቀጠሉ በፊት ተጨማሪ ሻይ አዘዘ።

«ሹሙ ክፉኛ ተቆጣ! አስፈሪውን ንዴቱንም በጉብኚው ላይ ተወጣበት። «ይህን ዓይነት ትዕዛዝ የሚሰጥ አምላክ ምን አይነት አምላክ ነው? የሰዎች ደስታና ምቾት በልቡ ቢኖር ኖሮ፣ እርሱን እጅግ አድርገው እንደሚወድዱት የሚገልፁትን ሰዎች፣ በሕይወታቸው ውስጥ በፍፁም ሴት እንዳይነኩ እንዴት ያስገድዳቸዋል? በአጭሩ ያንተ አምላክ ወንጀለኛ ነው። ተፈጥሮን እንዲህ የሚሰድብ ከሆነ፣ ሊፈጥረውም ባልተገባ ነበር። የዚያን ዕለት ምሽት፣ ሹሙ፣ ሴት ልጁን ከካፑቺኑ ጋር እንደገና እንድታድር በሩን ዘጋባቸው። በዚህ ጊዜ የመንደሩ ሰዎች በሙሉ በጉጆው ዙሪያ ተኮለኮሉ። መነኩሴውም ከዚያች ውብ ድንግል ልጃገረድ ጋር መርፌና ክር ሆኖ ሕጋዊ ጋብቻ መፈፀሙ ካልተረጋገጠ በስተቀር በሕይወት እንደማይወጣ አስጠነቀቀት»

«ይህ እጅግ ዘግናኝ ታሪክ ነው ባልደራስ፣ እባክህ ይብቃህ፣ አትንገረን» አለው የተጓዦቹ መሪ ስሜት ባጣ ሁኔታ።

ይሁንና ጀስዊቱ ተቃውሞውን አጠንክሮ አልገፋበትም። እንደ እውነቱ ከሆነ ሁሉም ቢሆኑ ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ለማወቅ የነደደ ጉጉት ነበራቸው።

«ታሪኩን ከሞላ ጐደል ጨርሻለሁ።» አለ ጆን ባፕቲስት። «ወዳጄ ቅዱስ አይደለም ወይም ደግሞ በተግባሩም ቅዱስ ሊሆን የሚችል አልነበረም። ታዲያ በማንኛውም መመዘኛ መሥራት የነበረበትን ሠራ። ሹሙ፣ አንዳችም ሃፍረት ሳይሰማው ማረጋገጫውን ለማወቅ በሚቀጥለው ማለዳ ሲመረምር፣ ወዳጄ! ዛሬ ኮራሁብህ። አሁን ስላንተው እየሱስ ለመስማት ዝግጁ ነኝ። ከዚህ በኋላ መላውን አገር ሃይማኖቱን ማስለወጥ ትችላለህ። በዚህም አቅምህ እስቀፈቀደልህ ድረስ ብዙ ትንንሽ ሕፃናትን የሚያስገኝልህ ዘር ልትዘራ ትችላለህ። ማንም ቢሆን ሃይማኖቱን ለማስፋፋት ጥሩው ዘዴ ይኸው ነው' ሲል ሹሙ ንግግሩን ቋጨ። በአጭሩ ብዙ ሕፃናትን ማፍራት እንጂ የሌሎችን መስረቅ አይደለም፣ መስረቁ ጥሩ አይደለም»

ጆን ባፕቲስት ታሪኩን ሲጨርስ፣ በክፍሉ ውስጥ ከባድ ፀጥታ ሰፈነ። ደንታ ቢስ በመሆን ሻዩን እፍ ብሎ ሃይለኛ ድምፅ እስኪያሰማ ድረስ ሳበው።



ከሁሉም ደፋሩና ነገሩን በአትኩረት ሲከታተል የነበረው ጀስዊት በመጨረሻ ላይ፣ «የምትነግረን እኛ ስድስታችን አቢሲኒያውያንን በሙሉ ማስረገዝ ያለብን መሆኑን ነው?»

ይህን ከተናገረ በኋላ በጊዜ ርዝመት የደበዘዘውን ትውስታውን ለማጥራትና ሃሳቡንም ለማቅለል ፈረሰኛውን አተኩሮ ተመለከተው። የዚህ ሰውዬ ፊት ለጆን ባፕቲስትም ቢሆን ፍፁም የማይታወቅ አይደለም። የሰውዬውን ጥያቄ በሚመልስበት ጊዜ፣ ፖንሴ የማጃጃል አቀራረቡን ፍፁም በመለወጡ፣ አድማጮቹን ይበልጥ ፍርሃት ያርዳቸው ጀመር።

«አቢሲኒያ፣ የሲናር ገጠር አይደለችም። አቢሲኒያ ኩሩ ጥንታዊ የክርስቲያን አገር ነች። እኛ ግን ይህንን ጥንታዊነት፣እንጭጭና ብስለት የሌለው ነው በሚል በመገመት በዚህ የምትተዳደር አድርገን እንስድባታለን»

ዙሪያውን የተቀመጠትን ሰዎች በጥንቃቄ ተመለከታቸው።

«አባቶቼ፣ እኔ የምሰጣችሁ ምንም ነገር የለም። በፍፁም አስፈላጊም አይደለም። በአጭሩ ግን እናንተ ማን እንደሆናችሁና ምን ልታደርጉ እንደሆነ ከእውነተኛ ምንጭ ተረድቻለሁ»

የአነጋገሩ ቅላፄ የርግጠኛነት ድምፅት ስላለበት ማስተባበል የሚቻልበት አይመስልም ነበር። ከመጀመሪያው ድንጋጤአቸው በኋላ በሌላ አቅጣጫ ተፋለሙት።

«እሺ እንግዲህ እኛ ማን መሆናችንን አወቅህ?» ሲል የመጀመሪያው ቃል አቀባይ ቀጠለ። «እንግዲያው በኛ ዕቅድ ላይ ሊኖርህ የሚችለውና ልንቀበለው የምንችለው ተቃውሞ ሊኖርህ ከቻለ ንገረን። ለመሆኑ የወንጌልን መስፋፋት ትቃወማለህ?»

ሙራድ፣ ስለጉዞው ድጋፍ አድራጊዎች ከሰጠው መግለጫ በመነሣት፣ የራሱን ግንዛቤ ወስዶ በደረሰበት ውሳኔ መሠረት «እርስዎ መቼም አባ ዴ ሞኔሃውት መሆን አለብዎት?» አለ ጆን ባፕቲስት

«ልክ ነህ»

«እሺ እንግዲያው፣ አባቴ፣ ተቃውሞ ከሆነ በጣም ብዙ ተቃውሞ አለኝ። ያቺ አገር ወንጌልን፣ እኛ ያወቅነውን ያህል ዘመን ስለምታውቅ፣አሁን ወንጌል አያስፈልጋትም። እኔ እስከማውቀው ድረስ እነርሱ የሚከተሉት የሃይማኖት ህግ ከካቶሊክ ቀኖና ጋር ልዩነት አለው። እውነቱን ለመናገር የጉዳዩ ሥር መሠረት ያለው ሌላ ቦታ ነው»

«የት ነው ያለው?» ሲሉ አባ ዴ ሞኔሃወት ለስለስ ብለው ጠየቁት።

ጆን ባፕቲስት ለአፍታ ያህል ካመነታ በኋላ ቀጠለ።

«ጊዜው ረዥም ነው። እኔም ብዙ ተሰውጫለሁ። እምና በዚህ ጊዜ ቢሆን ኖሮ፣ ባለኝ ታሪካዊ መረጃ፣ ሰብዓዊና ሃይማኖታዊ የመከራከሪያ ነጥቦች ደገፍ በዚህች አገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እንዳትገቡ በማቀርባቸው የመከራከሪያ ነጥቦች ላማምናችሁ እችል ነበር። በዚህ ዓላማ መሠረት ጉዳዩን ለማስረዳት ወደ ቬርሣይለስ ድረስ ተጉዤ ነበር። »

«ፖንሴ!» አሉት ማንነቱን በጣም ሲመረምሩት የነበሩት ጄስዊት

እኒህ ካህን፣ ጆን ባፕቲስት ከአባ ኘላንቴይን ጋር ሆኖ ማርሴይለስ ሲገባ፣ በጄስዊቶች መኖሪያ የነበሩት ቄስ እንደሆኑ አስታወሳቸው።

«አዎን፣ አባቴ ባለፈው ዓመት ባዩኝ ጊዜ ሰዎች እንዲያዳምጡኝና እንዲረዱኝ በጣም እጣደፍ ነበር። አሁን ግን ሁሉንም ነገር የተረዳሁት እኔ ነኝ»

የሆነ ወፈፌ ሰውን የሚያረጋጉ ይመስል «እስቲ ምን እንደተረዳህ ትነሽ ንገረን» አሉት አባ ዴ ሞኔሃውት በተረጋጋ ስሜት።

«በጣም ቀላል በሆነ አገላለፅ፣ እናንተ ለአንድ አስገዳጅ ሃይል የተደራጃችሁ መሆናችሁን ነው» ክርስቶስን እንደ ባንዲራችሁ በመያዝ፣ ሌላውም ባንዲራ እንዲሁ እንደናንተ ተመሣሣዩን መሠረታዊ ጉዳይ ሽፋፍኖ ያቀርባል። መሠረታዊው ጉዳይ ሥልጣን ነው»

«እናስ?» አሉ፣ እኒያው ለትችት የተፈጠሩ የሚመስሉ ቄስ

«እናማ፣ የሚገታችሁ ሃይል ነው። በጣም ለረዥም ጊዜ፣ ከነገ ዛሬ ሁኔታውን ትረዱታላችሁ የሚል ገራገር እምነት ነበረኝ»

ለአፍታ ያህል ፀጥታ ሆነ። ይህ በሻማዎች ብርሃን የደመቀው ክፍል በአረቢያን ባህረ-ሰላጤ አሸዋማ ምድር ጠርዝ ላይ ጠፍቶ የቀረ ነው ብሎ ለመዘንጋት ቀላል ነው። የት እንዳለ ጆን ባፕቲስት በድንገት ትዝ አለው። ይህ ቦታ እንዴት በቀላሉ ወህኒ ቤት ሊሆን እንደሚችልም ተገነዘበ።

«ሙራድን ለማግኘት አትባዝኑ። ሙራድ ሄዷል። እንዲያውም በዚህ ቅፅበት ከሚፈልግበት ቦታ ይደርሣል የሚል ተስፋ አለኝ። ስለናንተ አመጣጥ የምፅዋው ናኢብ ማስጠንቀቂያ ደርሷቸዋል። የኒህ ናኢብ ቅድመ አያት፣ የአገሪቱ በር በሚገባ መጠበቁን



ለማረጋገጥ የናንተን ቀደምት መነኮሳት ጭንቅላቶች፣ ለንጉሡ ነገስቱ ልከውላቸው ነበር። እኒህ የልጅ ልጅ የሆኑት ናኢብም፣ የአያቶቻቸውን ባህርያት ሁሉ የወረሱ ናቸው። እኒህ ናኢብ ቱርካዊ አይደሉም። የቱርክን የበላይ መሪ የሚታዘዙት ከርቀት ነው። እኒህ ሰው ምንም አይነት የተንኮል ሴራ፣ ምንም ዓይነት ውሸትና ምንም ዓይነት አቤቱታና ተማፅኖ ከአላማቸው ንቅንቅ አያደርጋቸውም። ይህን ባህር ስታቋርጡ ሊገጥማችሁ የሚችለውን አደጋ እንቀበላለን እንኳ ብትሉ ወደ አቢሲኒያ ግን ለዘለዓለም አትደርሱም።»

ይህን ቀይ ፍም የመሰለ ሙሉ ልብስና የተስተካከለ የአንገት ፎጣ ለብሶ፣ እጆግ ክብድ ምት ያሣረፈባቸውን ግርማ ሞገስ ያለውን ወጣት ሰው፣ በፍርሃት ተመለከቱት።

«ታዲያ ምን ማድረግ አለብን?» ሲሉ አባ ዴ ሞኔሃውት እያዘኑ ጠየቁ።

«በጣም ደካማ አቀባበል ሊያጋጥማችሁ ወደሚችለው ወደ ካይሮ አትሂዱ ወይም አቢሲኒያ ለመድረስ በየብስ ለመጓዝም አትሞክሩ። ምክንያቱም በየአቅጣጫው ላሉ የአካባቢ ገዥዎች በናንተ ላይ እንዲነሱ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል። በአሁኑ ጊዜ ነፃና ክፍት ሆኖ የምታገኙት መንገድ፣ በጀልባ ተሣፍራችሁ ወደ ስዊዝ የምትመለሱበት ብቻ ነው። ከዚያም ወደ ቅዱስ ምድራችሁ ወይም ወደ ፈረንሣይ ወይም በርግጥም ወደ ምትመርጡት ማንኛውም ቦታ መሄድ ነው። በብዙ ቦታዎች ራሣችሁን ቤተኛ ስላደረጋችሁ ልትሄዱበት የምትችሉበት አገር እጥረት አይኖርባችሁም»

ጆን ባፕቲስት ብድግ ብሎ ከቆመ በኋላ በሚያስፈራ ሁኔታ በመራመድ ሁሉንም በይቅርታ ዓይነት እተያዩ ተመለከታቸው።

«እመኑኝ፣ ለያንዳንዳችሁ አክብሮት አለኝ። እናንተን የማጋለጥ ሃሣብ ቢኖረኝ ኖሮ፣ ጉዳዩን በተለየ መልክ እንቀሳቀስበት ነበር። ይልቁንስ እኔ በተቃራኒው ሕይወታችሁን እየታደግሁላችሁ ነው። ይህን የማደርገው የእምነት ቃሌን ለሰጠሁት ንጉስ ታማኝ ስለሆንኩ ነው»

ስድስቱ ጄስዊቶች ዕቅዳቸው መቀልበሱን በዝምታ አሰቡት። ፖንሴም ቢሆን፣ ከነርሱ የባሰ የተጨነቀ መሆኑ ተሰማው። ይህ ሁሉ የሚሆነው፣ እኔ፣ ነፃ ሰውጥ እምጭ ስለሆንኩ፣ የምሠራውና የምንቀሣቀሰው በሙሉ ሃላፊነት ነው። እነርሱ ግን የራሳቸው ምኞትና ፍላጐት ጌቶች ሣይሆኑ፣ የሚባሉትን በእሺታ የሚቀበሉ ናቸው፣ ሲል አሰበ።

በትህትና ጐንበስ ብሎ ሰላምታ ከሰጣቸው በኋላ፣ በሩን ከመድረሱ በፊት መለስ አለና ወጥቶ ሄደ።

«ብርግጥ የመካውን ሸሪፍ የምናስጠነቅቅበት ምንም ሰበብ የለም። እስካሁን ስለ እውነተኛው ማንነታችሁ የሚያውቁት ምንም ነገር የለም። ይሁን እንጂ በአጠቃላይ እውነተኛው ማንነታችሁ መጋለጥ የሚገባው ሁኔታ ከተፈጠረ እጅግ የከፋ ሁኔታ ይሆንባችኋል። እንግዲህ በጣም ስለመሸ ጥቂት ዕረፍት አድርጉ። ደህና እደሩ። አባቶች»

ወደ ፎቁ ወጥቶ የራሱን ክፍል በር ዘጋ

ከንጋቱ አሥራ አንድ ሰዓት ላይ፣ መስተዋት የመሰለውን የባህር ውሃ የሚያወራጨው አንዳችም የነፋስ ሽውታ ሳይኖር፣ ጀን ባፕቲስት ከወደቡ በተከራየት አነስተኛ ጀልባ ሹልክ ብሎ ወጣ። ስምንት የጀልባ ቀዛፊዎች በተባበረ ሙሉ ሃይላቸው በሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ፣ ካሊዮፒያን ተከትለው መቅዘፍ ጀመሩ።

❦

በዚያው ሣምንት ውስጥ ፓሻው የላካቸው ቱርካውያን ፈረሰኞች በአባይ ወንዝ ሦስተኛው ፏፏቴ ላይ ሁለት ካፑቺኖችን አሰሩ። ከታሣሪዎቹ አንደኛው በያዙት ከረጢት ውስጥ ለአቢሲኒያው አቡን የተፃፈ ሰነድና አንድ ብልቃጥ ዘይት ይገኛል። እነዚህ የተያዙ ዕቃዎች ወደ ካይሮ ተወስደው የኮፕቲኩ ፓትርያርክ እንዲያዩዋቸው ሲደረግ፣ ደብዳቤውን ሲያረጋግጡ ብልቃጡንም ሆነ ዘይቱን ከዚህ በፊት አይተው እንደማያውቁ በመሃላ ገለፁ። ወንድም ፖስኪል ግን በግትር አቋማቸው ሳቢያ፣ እውነተኛው ቅብዓ ሜሮን የት እንደተደበቀ ለመግለፅ አሻፈረኝ አሉ። ይህን በግልፅ የታየውን አስነዋሪ የእምነት ጉዳይ፣ ፓሻው ወደ ቁስጥንጢንያ በላከው ደብዳቤ ላይ ጠንከር ያለ አፅንኦት ሰጥቶ ስለገለፀ፣ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የካፑቺን ወንድማማቾች አባላት ከአገር እንዲወጡና ወደ ኢጣሊያ እንዲሄዱ ተደረገ። ወደ አቢሲኒያ የተንቀሳቀሰውም የዚህ የሃይማኖት ሥርዓት ሚሲዮናዊ ጓድም ከዚህ መሰናከል አላመለጠም።

❦

የዱ ሮውሌ አንዱ ጭንቀት በተከታዮቹ መካከል ሥነ ስርዓትን የማስጠበቅ ጉዳይ ነበር። የሰበሰባቸው ጋጠ ወጦችና ምላሳም የሆኑ ከበሌዎች፣ ሀብት ለማግኘትና ለዐረራም በጣም



የሚጓጉ ስለነበሩ፣ ይህን ስሜታቸውን ለማርገብ ያልተቋረጠ ጥረት ማድረግ ነበረበት። እነዚህ ቁርጠኛ ጀግኖች የሆኑ ሰዎች ይህንን የማይበረግ የጀግንነት ወኔአቸውን፣ አንዲት የዋህ ኮረዳ ብን ብላ ስትጠፋ ያሣዩትን ያህል ድፍረት ሌላ ጊዜ አሣይተው አያውቁም። ይሁን እንጂ በሙስሊም ግዛት ውስጥ እስካሉ ድረስ ይህ ባህርያቸው መገታት ነበረበት። አቢሲኒያ ውስጥ ግን ታሪኩ ልዩ ይሆናል። ከዚህም በላይ ኢትዮጵያውያን ሴቶች ከፍተኛ የወሲብ ፍላጐት ስላላቸው የሚጠመዱት እነርሱ እንደሚሆኑ ስለተነገራቸው፣ ይህን ዘገባ እውነት ነው ብለው ለማመን በቅተዋል።

በሚገባ ተደራጅቶ፣ በሚገባ ታጥቆ፣ በሚገባ ስንቅ ይዞ የሚጓዘው ይህ ቅፍለት አንዳችም አይነት ያልተጠበቀ መጓተት ሳይገጥመው ደንጎሎ ደረሰ። የዚያች ከተማ መስፍንም በሚችለው ሁሉ በመልካም መስተንግዶ ተቀበለው። ይህ መስፍን ለክብራቸው ሲል ባዘጋጀው ጉስቋላና ደካማ የእራት ግብዣ ሁኔታ በመገረም ሣቃቸውን እንዳይለቅቁት ዱ ሮውሌና ሩሚላክ ራሳቸውን በጣም መቆጣጠር ነበረባቸው።

«ያልሰለጠነ ሰው መሆን ወይም ካልሰለጠነ ሰው ያልተሻለ መሆን እንዴት ድንቅ ነገር መሰለህ። እነዚህ ሰዎች የነፃነትንና ተፈጥሮአዊ የሆነውን የጭውውት ዕድል ሊደሰቱበት ይገባቸው ነበር። እነዚህ ሰዎች እንዲህ ያለውን ነገር አያደርጉም። በድሮ ዘመን በአገራችን ከነበሩት መሣፍንቶችና መኳንንቶች በባሰ መልክ፣ የህብረተሰብ ሕግ ትክክል ካልሆነ ብለው ሙጭጭ የሚሉ ናቸው» አለ ዱ ሮውሌ።

ዱ ሮውሌና ሩሚላክ፣ በዋናው አስተርጓሚያቸው በፍሬሴቲ ሁኔታ ላይ ቅሬታቸውን ይነጋገራሉ። ይህ አስተርጓሚ የአገሬው ተወላጆችን ድርጊትና ተግባሮች ተገቢ አድርጐ ሲቀበል፣ የነርሱን ባህርይ ግን እንደማይስማማበት የሚያሣይ ሥራ ያከናውናል። ይህ ደግሞ እንደ እውነቱ ከሆነ ከሚገባው በላይ ነው። ዘሩ ሊነገር ከማይችል የጥቁር ሕዝብ መሃል የተገኘ ካልሆነ በስተቀር፣ ከመሣፍንትና ከመኳንንት ዘር ለሚወለዱ ሰዎች ስለ ትክክለኛው ባህርይ ትምህርት ለመስጠት መዳፈር ያበዛል።

በዚህች ከተማ ውስጥ ሊከናወን የሚችል የንግድ ጉዳይ ስለሌለ፣ አንድ ቀን ብቻ አርፈው ወደ ሲናር ተንቀሣቀሱ።

የመጀመሪያዎቹን ሁለት የበረሃ ገነት ሰፈሮች በቀላሉ ደረሱ። በሦስተኛው የበረሃ ገነት መንደር ሲደርሱ የቅፍለቱ መሪ ቤላክ፣በጣም ተጨንቆ፣ ዱ ሮውሌን ለማግኘትና ለማነጋገር መጣ። ሦስት ግመል ነጂዎች ጉዟቸውን ለመቀጠል አሻፈረኝ ብለዋል። ለዚህም

ምክንያታቸውን ለመግለፅ አልፈቀዱም። የየበረሃው ገነት ነዋሪዎች ሊገለፅ የማይችል እምነት ማጣት በነጮች ላይ እያሣዩ ነው። እነዚህ ሕዝቦች፣ ነጭ ነጋዴዎች በውስጣቸው እየተዘዋወሩ ሲነግዱና ከነርሱ ጋር ሲሠሩ ያውቃሉ። ከሠራተኞቹ አንዱ የሆነ፣አንድ ወደል የዳልማቲያ ጕረምሳ፣ እንደአጋጣሚ ሆኖ የአሥራ ሁለት ዓመት ዕድሜ የሚሆናትን ኮረዳ ሰውነት በጣም እንደተላመዳት አይነት እጆቹን በማሣረፍ አሻሽቷታል። ልጅቷ አፍንጫዋ በንፍጥ የተለቀለቀ፣ ባዶ እግሯን ያለች ጮሌ ስትሆን ተወላጁ ህዝብ ክብሯ በመነካቱ ተደፈረን በሚል ስሜት በተጋነነ ቅናት ለመከራከረ ተነሣ። ሁኔታውን ለማለሣለስና ለማብረድ ሲል፣ ዱ ሮውሉ ለዚህች ተደፈረች ላለች የፈጠራ ሰው፣ የቬነሲያውያንን የመስተዋት ሃብል ይሰጣታል። ለአባቷም ያረጁ ጫማዎችን ይሰጣል። ይሁንና እነዚህ ያልሰለጠኑ ሕዝቦች በዚህ የረኩ አይመስልም። የሚታየው አጠቃላይ ጥረት ሁሉ ሙሉ በሙሉ ስምምነት የማይታይበትና የአካባቢውን ጕሣ የጥላቻ ስሜት የሚያመላክት ሆነ። ይህ ሁሉ፣ ጕብኚዎች በሚያደርጕት የተለየና ያልተለመደ ችሮታ ሳቢያ ነው ሲል ሩሚላክ አሰበ።

በሚቀጥለው ሠፈር የተሻለ አቀባበል እናገኛለን በሚል ተስፋ ይህኛውን መንደር ትተው ወጡ። ይሁን እንጂ ወደ ሲናር በተጓዙ ቁጥር ሁኔታዎች ከዕለት ዕለት እየተበላሹ ሄዱ። በየደረሱበት ሁሉ፣ ፅጥታ የሚታይበት የጥላቻ ስሜት ያለው የሕዝብ ስብሰብ አለ። እንደ ዕድል ሆኖ ግን፣ንጉሡ ፣የሕዝቦቹን የቀዘቀዘ የአቀባበል ስሜት ለመቀየር ሲል ያሰበትን ሃላፊነት በልዩ ሁኔታ ተወጣው። መንገደኞቹን በመጀመሪያው ዕለት አብረውት እራት እንዲበሉ ጋበዛቸው። ምንም እንኳ ለቅመማ ቅመማትና ቅባት ለበዛበት ምግብ ጥሩ .ፍላጐት ባይኖራቸውም፣ ዱ ሮውሌ፣ ሩሚላክና ባልስልጣኖች ናቸው የተባሉ ሌሎች ሁለት ሰዎች በግብዣው ላይ ተገኙ። ፍራሴቲ ታምሜአለሁ በሚል የማስመሰያ ሰበብ፣ ካምፕ እጠብቃለሁ ብሎ ቀረ። ፈረንሣውያኑ፣ ሁሉም ሰው የሚያውቀውንና የሚቀበለውን ባህል ቢከተሉም፣በየኪሶቻቸው ውስጥ ትናንሽ ብልቃጦች ይዘዋል። ከነዚሁ ብልቃጦቻቸው መጠጦቻቸውን ይጕነጫሉ። የእራት ግብዣው በሚጠናቀቅበት ጊዜ እነዚህ ተጋባዦች በሚገባ ሞቅ ብሏቸው ነበር። ይህን የመሰለ ሞቅ ያለ ስሜታቸው ምን እንደሆነ ንጉሡ የማያውቅ መስሎም ተሰማቸው። ይህም ንጉሡን የታወረ አድርጎ የመገመት ያህል ነው። በርግጥ ንጉሡም እንደክብሩ ምንም ያላስተዋለ መሰለ። ሌላው ቀርቶ የቀድሞው ወታደር፣ በተከታይ አሸከሩ ረዥም ጀለቢያ ኪስ ውስጥ እጁን ሲሰድድ፣ እንዲህ ባለ ረዥም ካባ ውስጥ ምን ሊፈለግ እንደሚችል እንኳ እንዳላየ ሆነ። በመጨረሻም ወደቅፍለታቸው ሰፈር ተመለሱ።



ማረፊያቸውም ከከተማዋ መግቢያ በአንዱ አጠገብ ተደርጕላቸው ነበር። እነዚህ ሰዎች ደስ እንዳላቸው ሰዎች ሆነው ወደየመኝታቸው ሄዱ። በዚያም ዝናና ሃብት ሲያልሙ አደሩ።

በሚቀጥለው ቀን በነርሱ ላይ የተቀሰቀሰው ጥላቻና ተቃውሞ ከመቼውም በበለጠ እየጕላ መጣ። ከሰዎቹ መሃል ሁለቱ በከተማው ውስጥ እየተዘዋወሩ ሳሉ ድንጋይ ተወርውሮባቸዋል። በየገበያው ስፍራ ለመሸጥ የሞከሯቸው ሸቀጣ ሸቀጦች ከአውሮፖ የሚመጣ ማንኛውም ነገር መጥፎ ዕድል ይዞ የሚመጣ ይመስል ተቀባይ አጡ።

ዱ ሮውሌ በበኩሉ ተቀባይነት የማግኘታቸውን ዕድል በተገቢ አክብሮት ለመቀበል ከሚፈቅዱ ሰዎች ማለትም፣ ከንጉሡና በዙሪያው ከሚገኙ መኳንንቱ ጋር ለማጠናከር ወሰነ። ባለፈው ምሽት ለአገሪቱ የበላይ መሪ ካቀረበው የገፀ በረከት ስጦታ በተጨማሪ፣ ልዕልቲቱንና ከፍተኛ ደረጃ ያላቸውን ወይዛዝርቶችዋን ከአውሮፖ ባመጣቸው ማራኪ ቁሣቁሶች ማስደሰት እንደሚፈልግና ዕድል ቢሰጠው ይህ ለርሱ ከፍተኛ ክብር እንደሚሆን መልዕክት ላከ። በማግስቱም አንድ ደርዘን ያህል የሚቆጠሩ ሴቶች ከቤተመንግስቱ መጡ። ይሁን እንጂ፣ ንግስቲቱ በመጀመሪያው ቀን ሳለመታየት ፈልጋ ነበር። እነዚህ ግዙፍ ኑቢያውያን ሴቶች፣ ቀለመ ደማቅ አይነ ርግቦቻቸውን እንዳደረጉና ፊቶቻቸውን ሳይሸፍኑ በነፃነት ደብረክ ደብረክ ሲሉ በማየቱ ሩሚላክ በሳቅ ፈነዳ።

ከመጀመሪያው ጀምሮ ለእንግዶቹ ፈገግ ብሎ «ምን አይነቶቹ ያለፈበትን ፋሽን የሚለብሱ ማስጠሎዎች ናቸው?» ሲል ዱ ሮውሌ በፈረንሳይኛ ነገረው።«አባካችሁ ወይዛዝርት ወደ ውስጥ ዝለቁና የልዕልታት ምርጫዎች የሆኑትን፣ የተከበሩ የቫሊየሬ ወይዛዝርት የሚወዷቸውን ተመለከቱ»

ራሷ ላይ ሁለት አጫጭር ጉንጉን ያለባት፣ የምታነክስ ወፍራም ሴት ላይ ጣቱን አመለከተ።

«ውድ ፍራንቾይዝ ዳውቢኜ እኒሁና። እባክዎ ማዳም ላ ማርኩይስ ይግቡ»

ሴትየዋ፣ ተስፋ የቆረጠ ፊት የሚታይባት አሮጊት ነበረች። በሰፈሩ ውስጥ ወዳለው ትልቅ ድንኳን እንዲገቡ ካደረጋቸው በኋላ ዱ ሮውሌ፣ ቃል የገባበትን ማስደሰቻ ማሳየት ጀመረ። ከነዚህም መካከል መልክን አጣምሞ የሚያሳየው የቬነስ መስተዋት ይገኝበታል።

መስተዋቶቹ ሁሉ በግድግዳው ዙሪያ ተሰቅለው ሳሉ፣ ወይዛዝሮቹ በድንኳኑ መሃል ነበሩ። መስተዋቶቹ የተሸፈኑባቸው ጨርቆች ሲነሱ፣ ወይዛዝሮቹ ንቅንቅ ሳይሉ፣ በየራሳቸው ስብስብ ቆዩ። ፈረንሳውያኑ ወንዶች፣ ወይዛዝሮቹ ገና የመልካቸውን ነፀብራቅ እንዳላዩ አመኑ። ዱ ሮውሌና ሩሚላክ እነዚህን እመቤቶች ተራ በተራ እየያዙና በፈረንሳይኛ እየቀለዱ፣ ሴቶቹ የፊቶቻቸውን ምስል በቅርበት እንዲያዩ ያመጧቸዋል።

«ይህች ወይዘሮ፣ ራስዋን እንዲህ ሸንቃጣ ሆና ፊፅሞ አይታ አታውቅም፣ እዩልኝ የኔን ቆንጆ! ሲያዩሽ የግመለ ቅርፅ ነው ያለሽ ሁሉመናሽ እግር ብቻ ሲሆን ጭንቅላትሽ የፍየል ነው»

«ነይ ጠጋ በይና ጓደኛሽን ተመልከቻት፣ እንዴት ኮስታራ እንደሆነችም እዩት። ከቁመትዋ መርዘም ይልቅ ወደጐን ትሰፋለች። እዚህ ያሉት ወንዶች ደግሞ እንደርስዋ ያሉትን ይመርጣሉ»

ዋናው አስተርጓሚ ፍሬሴቲ፣ ሴቶቹ የሚያጉረመርሙበትን ምክንያት ስለተረዳ አይስቅም ነበር። ሴቶቹ፣ በነዚህ ምስሎቻቸው የደነገጡና የተገረሙ መሆናቸውን ተረድቷል። ሴቶቹ፣ ራሳቸውን ሲመለከቱ፣ የሚያስጠላ መልክ፣ የሰውነታቸው ቅርፅ ተወለጋግዶ፣ አካላቸው ወደ ርኩስ መንፈስ የተቀየረባቸው መስሎ ታያቸው። የእስልምና ሃይማኖት እየተገነባ ባለበት አገር፣ የአስማትን ሥራ ህጋዊ ማድረግ ምትሃት ነው ተብሎ ብቻ የሚታሰብ ሳይሆን የከረረ ስሜት አለበት። ዱ ሮውሌ፣ ሲያሽሟጥጣቸው፣ ለነርሱ ይታያቸው የነበረው፣ ልክ የገሃነም በሮች በድንገት ተከፍተው፣ የተረገሙባቸውን ዘለዓለማዊ ሥቃይ እንዲመለከቱ የተደረጉ መስሏቸው፣ የወደፊቱ ዕጣ ፈንታቸው ታያቸው።

በመጀመሪያ እሪታዋን የለቀቀችው ወይዘሮ፣ ለሌሎቹ ምልክት በመስጠት ቀሰቀሰቻቸው። ከድንኳኑ ውስጥ በመውጣት ዓይነ ርግቦቻቸው ሩጫቸውን እንዳያሰናክሉባቸው ከፊቶቻቸው ላይ እያነሷቸው፣ አይኖቻቸውን ጐልጉለው በነዚያ ሽለቆ በሚመስሉ የእግር መንገዶች እስከ ቤተመንግስቱ ድረስ እያለከለኩና ጋሻቶቻቸውና እሪታዎቻቸው ከኋላቸው እያስተጋቡባቸው ሮጡ።

ዱ ሮውሌ፣ ሁሉም ነገር ካለፈ በኋላ ነገሩን ተረድቶ፣ ሁሉም መሣሪያ እንዲያዘጋጅና የመከላከያ ቦታውን እንዲይዝ ትዕዛዝ ሰጠ። አሥር ደቂቃ ያህል የፍርሃት ፀጥታ ከሆነ በኋላ ጥቅጥቅ ያለ የሰዎች ክምችት በሶስት አቅጣጫ ሲመጣና ዝግ ያለው የእግር እርምጃቸውም የአቧራ ደመና ሲያስነሣ ተመለከቱ። እያንዳንዱ ፈረንሣሳዊ ጠመንጃውን በመተኮስ



ያነጣጠረበትን ሰው ገደለ። ነገር ግን የወደቀውን ሰው የሚተካ ተጨማሪ ሰው ቦታውን እየሞላው፣ መጭው የውጭ ሃይል ለመፀለይ እንኳ ፋታና ጊዜ አላገኘም። በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ መላው የቅፍለቱ መንደር በአደጋ ጣዮቹ ቁጥጥር ሥር ሆነ። በኑቢያውያኑ እምነት፣ አንድን አስማተኛ በባዶ እጅ መግደል ርግማን ያስከትላል። በዚህ ሳቢያ የጦር እስረኞቹ ስቃይ በቀጥታ በስቅላት ተፈፅሞ ቢሆን ኖሮ ሊቀለል ከሚችለው በላይ ተራዘመ።

የንጉሡ ፈረሰኛ ጦር ሁሉም ነገር ካበቃ በኋላ ጣልቃ በመግባት፣ በቅፍለቱ ላይ ተጭነው የነበሩትን ንብረቶችና ግመሎችን በመያዝ ወደ ንጉሡ አመጣ። ንጉሡም፣ የዚያውኑ ዕለት ሊጋሻው ደብዳቤ ፃፈ። ጥርጥር በሌለው ሁኔታ፣ ካፑቺኖች የነዙት የተንኮል ወሬ፣ ተጓዦቹ ወደ አገሩ ከመግባታቸው በፊት መሠራጨቱን በማማረር ገለፀ። እርሱ ራሱ፣ ፈረንሣውያንን በተቻለው መጠን በትህትና ያስተናገደ ቢሆንም፣ ሕዝቡ ግን በመጨረሻ ላይ እንደያዛቸው ፃፈ። እንግዲህ ሕዝብ ተቆጥቶ ለግድያ ከወጣ፣ ንጉሡ ምን ሊያደርግ ይችላል? የሚል ትህትና ያለበት ጥያቄ ያዘለ ደብዳቤ ፃፈ።

# 10

ሁለቱ የባህር ሰላጤዎች በሚለያዩበት ቦታ ላይ በጀልባዋ ሰፊ ክፍል ውስጥ አዲስ ነፋስ ሽው አለ። ሸራዎቹ ተወጥረው ጀልባዋ ወደ ሲና በጥሩ ፍጥነት ተንሣፈፈች። የተራራው ቀይ አፈር እናት፣ ከግራጫው ሰማያዊ የሚያዝያ ወር ሰማይ አንፃር ከፍ ብሎ አድጓል። ጆን ባፕቲስት በፊቱና በእጆቹ ላይ የባህሩ ሃይለኛ ጣዕም ነበረው። በሰውነቱ ላይ የተረጨው ውሃ የጨው መስመር ምልክቶችን በመተው ፀሐይዋ አደረቀችው።

ሁሉም ነገር ማብቂያና መነሻ እየሆነ ነው። ወደ አቢሲኒያ የተንቀሳቀሱት ሦስቱም ተልዕኮዎች ተገትተዋል። አሲስም፣ አሁን በእይታ ውስጥ ባለው ተራራ ትከሻ ላይ ሆና ትጠብቀዋለች። ከእንግዲህ በኋላም ርግጠኛነት የሌለባቸው ብዙ ነገሮች ስላሉ፣ ጆን ባፕቲስት ወደፊት ስላለው ሁኔታ ይጨነቃል። በርግጥ ከእስከ አሁኑ የበለጠ አስደናቂ ነገር በልቡ ውስጥ አያስብም። የተናወጠው ነፋስና ማዕበል የወረወረው ውሃ፣ በአስገራሚው የባህሩ ወለል ላይ ሲላተሙ የሚያሣዩትን ሰላማዊ ትርኢት መላ አካሉ ሲሰማው፣ የሰውን ዕድል ፈንታና ሁኔታ የሚወክሉ ይመስላሉ። ይህን ትርዒት ጆን ባፕቲስት በተደበላለቀና ተቃውሞ በሌለው ምርኮ፣ ልክ በገደል ጠርዝ ላይ ቆሞ በመጨረሻው ሰዓት ላይ ከሚያፈቅራት ሴት ጋር ዳግም የሚዋሀድበትን ጊዜ እንደሚጠብቅ ሰው በርጋታ ተመለከተው።

በፀሃይና በጨው፣ ቀለሙ ለቅቆ በወየበው የመርከብ ወለል ላይ፣ አረባውያኑ መርከበኞች ባዶ እግራቸውን በቁረያው ቆሙ። ረዣዥሞቹ ሸሚዞቻቸው በነፋሱ ይውለበለባሉ። መርከበኞቹ ሙቀት በማግኘታቸውና ጀልባቸውንም በሰላም ወደ አገራቸው መልሰው ማምጣት በመቻላቸው ደስተኞች ነበሩ። ተራራውን ፊት ለፊታቸው እንደተገተረ እንደ አንድ ትልቅ ተራ ነገር ተመለከቱት።

እንደነርሱ ለመሆን እንሞክር ሲል፣ ጆን ባፕቲስት ለራሱ ተናገረ። ሊሰማን የሚገባው፣ እየሆነ ያለው ብቻ እንጂ፣ አዕምሯችንን በሰላም ላይ ማስታጠቅ የለብንም።

እኩለ ቀን ሊሆን ሲል፣ አል ቱር ወደብ ደርሰው ወረዱ። ጆን ባፕቲስት፣ የአውሮፖዊ ልብሶቹን በከረጢት ውስጥ አድርጐ እንደ አረቦች ለበሰ። የቻርትሬሱ መስፍን የሰጡትን አስር ሴኩንስ ሊሆን የሚችል ትንሽ ወርቅ እስከአሁን ስላለው፣ አንድ ያረጀና በግላሱ ውስጥ ጭዱ



ወጥቶ የሚታይበት ኮርቻ ከአንድ በቅሎ ጋር መግዛት ይችል ነበር። በአንድ እጁ የኢጋሰሱን ጐን መታ መታ የሚያደርግበት አርፖሜ በሌላው እጁ የእንሰሳውን አቅጣጫ የሚቆጣጠርበትን የልጓም ገመድ ይዞ በአብዛኛው በውሃ ወደተከበበው አገር ሄደ።

በዚህኛው የባህር ጠረፍ ቦታ ላይ፣ የሲና ተራራ ከወደሜዳው እጅግ ቀስ እያለ የሚያድግ በመሆኑ መንገደኛ ሰው ወደ ተራራው ሰንሰለት በዝግታ እየወጣ ሊጓዝበት ይችላል። ምድረበዳው፣ ከወደቡ የመጨረሻው የአትክልት ሥፍራ በኋላ ወዲያውኑ ይጀምራል። ምድሩ፣ ሁሉም ነገረ የተለያየበት የአሸዋ ምድረ በዳ ሳይሆን፣ ይልቁንም እርቃኑን ባለ የምድር ገፅ ላይ ድንጋዮች በቋጥኝ ላይ የተገተሩበት ነው። ሲመለከቱት፣ እጅግ ሰፊና ገላጣ በሆነ ቦታ ላይ፣ በማይበከለው ማዕድኑ የሚታይ የሐውልቶች ፍርስራሽ መስሎ፣ ከራሱ ዘለዓለማዊና የተወሰነ መኖር በስተቀር የሌሎችን መኖር የሚያከስስ ይመስላል። ከአረቢያ ፔትራኤ እምብርት በሚጥመለመል የእውሎ ነፋስ ሃይል ተገፍቶ የመጣው የነጭ አፈር ንብርብር፣ አይን የሚያርፍበትን ሁሉ የሸፈነ ስለሆነ፣ የመጨረሻው አገልጋይ ለቅቆ ከሄደ በኋላ የሚታይ የቤተመንግሰት ሁኔታ በሃሣብ ውስጥ ይመጣል። ዘመን ከቶም ሊያከስምነው ስላልቻለ፣ ይልቁንም መስኮታዊ የጊዜ መቀመሪያ፣ ውብ የአሸዋ ዱቄቱን ያፈሰሰበት ይመስላል።

ጆን ባፕቲስት፣ አንድም ሰው ሳያይ ሁለት ሰዓት ሙሉ በበቅሎው ሰገረ። ምሽቱ በጣም እየተቃረበ ነበር። በቅሎዋ በተቻለ መጠን ቀሪውን ርቀት እንድትፈጥንለት የሚችለውን ሁሉ ቢያደረግም ከንቱ ሆነበት። ምስኪኒቱ እንሰሳ የነበራት የአረማመድ ሁኔታ ሁለት ዓይነት ብቻ ነበር። አንደኛው ፍፁም መቆም ሲሆን ሁለተኛው የድንዛዜ ዓይነት ነበር። ከዚህ በኋላ ያለው መንገድ ሽቅብ እየተጠማዘዘ የሚያድግ፣ ጠቁሮ የሚታይ ገደል ነው። ጆን ባፕቲስት ዳገቱን ወጥቶ ሲያጠናቅቅ ሰማዩ የጥቁር ቀለም መልክ ይዟል። ጥቁርቁር ያለ ቅርፅ የያዙት ቋጥኞች፣ በዚህ የሰማይ ቀለም ፊት እንደ ጭራቅ ተገትረዋል። የሲናን ተራራ ጫፍ በጠረቡት በሁለቱ ታላላቅ ሸለቆዎች መገናኛ ላይ፣ በጣም ተመሣሣይ በሆኑ ድንጋዮች መሃል አንድ የተጠረበ ቋጥኝ ተመለከተ። ይህ፣ አራት ማዕዘን ቅርፅ ያለው የገዳሙ ግድግዳዎች ቁልል ቋጥኝ ነው።

የእነዚህን አመድማ ግድግዳዎች ወለል ሰንጥቀው ሽቅብ ያሰነጉ አሥራ ሁለት ክብ ማማዎች አሉ። የጦር ጫፍ የመሰሉት የቤተክርስቲያኑ ሁለት ጣሪያዎች ባይኖሩ ኖሮ በምድረበዳ ውስጥ ያሉ ምሽጐች ይመስላሉ። በጣም ቅርብ ቢሆንም፣ የመከላከያውን በሮች ለመድረስ ግን ከአንድ ሰዓት በላይ ይወስዳል። በዚህ የመከላከያ ቦታ ላይ ዘቦቹ ራሣቸው

መነኮሣቱ ነበሩ። ሰውነታቸው እንደ ነፃ ትግል ታጋይ በሚገባ ፈርጥሞ የተገነባና ቀጥ ያሉ ስለታም ጉራዴዎቻቸውን በካባዎቻቸው ላይ ባሉት ሰፋፊ ቀበቶዎቻቸው ላይ የታጠቁ ሁለት መነኮሳት መንገደኛውን ካስቆሙት በኋላ፣ ስሙን ለገዳሙ አበምኔት ላኩ። መግባት እንደሚችል የሚፈቅደው መልስ ከመጣ በኋላ እንዲገባ ተደረገ።

በአጥሮቹ ውስጥ ያለው የቅድስት ካተሪን ገዳም እንደእውነቱ ከሆነ አንድ ከተማ ነበር። በተክርስቲያኑ የሚገኘው መሃል ላይ ሲሆን ሌሎች ህንፃዎችና አዳራሾች፣ ተመሣሣይ መልክ ያላቸው መኖሪያዎችና ትናንሽ የፀሎት ቤቶች መጠነኛ ክፍተት በመሃላቸው እየተተወ ዙሪያውን ተገንብተዋል። የግድግዳዎች፣ የመንገዶችና ተራ የመተላለፊያ ጉዳናዎች በምስራቅ ሜዲተራኒያን ከተሞች የሚታዩትን ዓይነት ናቸው። እንደ መስቀል ጦር ተዋጊ፣ ስስና ወርቃማ የራስ ፀጉር ቀለም ያላቸው ወጣት መነኩሴ፣ ጆን ባፕቲስትን እየመሩት ወደ አበምኔቱ መኖሪያ ወሰዱት። መነኩሴው፣ የጆን ባፕቲስትን ሻንጣ ሲይዙለት፣ በቅሎውን ግን በመግቢያው በር ላይ ከሚገኙት መነኮሣት ዘንድ እንዲተወው መከሩት።

የቅድስት ካተሪን ገዳም የተመሠረተው በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ በጀስዊታውያን ነበር። ከዚያ እስከ ዛሬ ድረስ መቆየት የቻለው በነዚሁ አጥሮቹ ነው። ከዚህም በላይ ምናልባትም ሲወርድ ሲዋረድ በመጡት የሙሴ ዘሮች ዘንድ እጅግ ከፍተኛ ግምት ባላቸው በነዚህ የተቀደሱ ተራሮች መከላከያነት ይሆናል። በዚህ ቅድስተ ቅዱሣን ሥፍራ የሚኖሩት የኦርቶዶክስ መነኮሣት፣ የሚመሩት በቀጥታ በኢየሩሣሌም ፓትርያርክ ሥልጣን ሥር ነው። ይሁን እንጂ ለአንድ የተለየ የሃይማኖት መስመር መሣሪያ ከመሆን በማለት፣ በገዳሙ የሚኖሩ መነኮሣት የራሣቸው የሆነና ራሣቸውንም የሚያስተዳድር ሥልጣን ያለው ጠባቂ በዚህ አስፈሪና ምስጢራዊ በሆነ ቦታ ላይ መሠረቱ። ወደዚህ ገዳም ሸሽተው የሚመጡና ከለላም የሚሹ ሰዎች፣ ከየትም ይምጡ ከየት ወይም ምንም ዓይነት ወንጀልም ፈፅመው ይምጡ፣ ደህንነታቸው የተረጋገጠ ነበር። ጥቂቶቹ በዚህ ቦታ ላይ ለአጭር ገዜ ሲሰነብቱበት፣ ሌሎች ብዙዎች ደግሞ በቋሚነት ስለሚቀሩ፣ የኗሪው ቁጥር እንዲያድግ አድርገዋል። ከብዙ ጊዜ ሃይማኖታዊ የደረጃ ዕድገት በኋላ ከነዚህ ሰዎች አንዳንዶቹ የገዳሙን ማህበረሰብ ለመምራት ጭምር ተስፋ ይኖራቸው ነበር።

በገዳሙ አበምኔት መኖሪያ ውስጥ የነበረው ሁኔታ፣ ጆን ባፕቲስት ከዚህ በፊት በመጀመሪያ ጉብኝቱ ወቅት ከሚያውቀው እጅግ አዲስና የተለየ ነበር። መነኮሣቱ የሚነጋገሩት



እየተንሾካሹኩ ነበር። የብርጉድና የከርቤ ሽታ፣ የድንጋይ ንጣፍ ባለባቸው መተላለፊያዎች በአየሩ ውስጥ ተበትኗል።

«የገዳማችን አስተዳዳሪ በጣም ታምመዋል» ሲሉ አበምኔቱ ለጆን ባፕትስት ነገሩት። ከሶስት ሣምንት በፊት ቅዳሴ ሥርዓት ላይ እያሉ ወድቀው ህሊናቸውን ስለሣቱ አንስተን ወስድናቸው። ይህ ሁኔታ ከገጠማቸው ወዲህ ቃላት አነባጥመው ለመናገር ያቅታቸዋል። በምሽት የህመሙ ስቃይ ይበረታባቸዋል። ሲያቃስቱና አንዳንዴም ሲጮሁ እንሰማቸዋለን። ባልደረባህ የሚጠጣ መድሃኒት ስለሰጣቸው እፎይታን የሚሰጣቸው ቢሆንም እኛ ግን እስካሁን እንደተጨነቅን ነን»

ጆን ባፕቲስት የገዳሙን አሲቃ ለመመርመር እንዲችል ሃሣብ አቀረበ። ይሁን እንጂ ከዚህ አስቀድሞ ውስጡን ሲበላው የነበረ ጥያቄ ነበረው።

«ጓደኞቼ፣ ሜትር ዠረሚና ሁለቱ ሴቶች የት እንዳሉ ይንገሩኝ»

«ስለነርሱ አትጨነቅ።» አሉት አበምኔቱ። «እዚህ ከመጡ ሁለት ሣምንት አልፏቸዋል። እስካሁንም አንተኑ ነው የሚጠብቁህ። እንደ አጋጣሚ ሆኖ ግን ትናንትና የኛው ወንድሞች በተራራው ጫፍ ላይ ባነጿት አንዲት የፀሎት ቤት አጠገብ ሆነው የማለዳዋ ፀሐይ ስትወጣ ለማየት ሄዱ። እዚህ ምንም የሚሠራ ነገር ባለመኖሩ ሣይሰላቹ እንዳልቀሩ ነው። ወጣ እንዲሉ ሃሣቡን የሰጠኋቸው እኔ ስለነበርኩ አዝናለሁ። ይሁን እንጂ በማንኛውም ሁኔታ ነገ ጧት ተመልሰው እዚሁ ይደርሣሉ።»

ጆን ባፕቲስት ለጊዜው ተስፋ እንደመቁረጥ ካለው በኋላ፣ መልካም የዕረፍት ለሊት ሊያገኝ፣ ልብሶቹንም ለመቀየር እንደሚችል ለራሱ በመንገር፣ በአካልና በአዕምሮ ብርታት አግኝቶ፣ በማግስቱ ጧት ሊያገኛቸው እንዲችል ለመሄድ ወሰነ።

የገዳሙ አበምኔት፣ ጆን ባፕቲስትን ወደ አስተዳዳሪው መኝታ ክፍል አስገቡት። የመኝታ ክፍሉ ሰፊ ሲሆን፣ ረገሻዎቹ መስኮቶቹ ለምለም ሣርና የደወል ቅርፅ ያላቸው አበቦች ፈንድተው ወደሚታዩበት ስገነት ይከፈታሉ። በአንደኛው ግድግዳ ላይ የባቢሎንን ግንብ የሚወክል የሲጋጃ ጥልፍ ተሰቅሏል። የገዳሙ አስተዳዳሪ የንድፍ ሥራ ባለሞያ ሆነው ደማስቆስ ውስጥ ለብዙ ዓመታት ኖረው ነበር። ነገር ግን ከባለቤታቸውና ከሁለት ወንዶች ልጆቻቸው ድንገተኛ ሞት በኋላ እግራቸው እንደመራቸው ወደፊት ተጉዘው የሲና ተራራን

ጐዳና ገቡበት። ሲና ከገቡ ወዲህ፣ ቅድስት ካተሪንን ለቅቀው ወጥተው አያውቁም። ከአስር ዓመት ባነሰ ጊዜም ውስጥ ከፍተኛው መሪዋ ለመሆን በቅተዋል። ጆን ባፕቲስት፣ ሲና ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በሰነበተበት ሰሞን እኒህ ሰው ገዳሙን ለማስፋፋት የሚያስችላቸውን ንድፍ ለማዘጋጀት የፕላን መሥሪያ ኮምፖሳቸውን፣ ማዕዘን ማውጫዎችንና ማስመሪያዎቻቸውን በመገልገል ላይ ነበሩ። በአንድ ጠርዝ አጠገብ የተቆለሉ የወረቀት ጥቅሎች ይታያሉ። እነዚህ ያለጥርጥር ያልተገባደዱ ሥራዎቻቸው ይሆናሉ።

ምስኪኑ ሰው፣ ሊለዩ በማይችሉበት ደረጃ ከስተዋል። ፊታቸው እንቅልፍ በማጣትና በጭንቀት ተሸብሽቧል፣ ቆዳቸው እንደሰም ገርጥቷል። አፋቸውም የስቃዩ መጠን ስላየለባቸው ተጣምሟል።

«ሁሉም ነገር ከመፈፀሙ በፊት በድጋሚ አንተን የማየት ዕድል ስላገኘሁ በጣም ደስ ብሎኛል» አሉት በመከራ።

አንዳች ቃል ለመተንፈስ አቅም የሌላቸውን ሰው የደረቀ እጅ፣ ጆን ባፕቲስት ጠበቅ አድርጐ ያዘ። ሽማግሌው ወዲያውኑ አሸለቡ። ዶክተሩ ከክፍሉ ውስጥ ሹልክ ብሎ ወጥቶ አበምኔቱን አገኛቸው። ስቃዩን እያስታገሱላቸው ሊያቆዩዋቸው ብርቱ ተስፋ የነበራቸው ቢሆንም፣ መሞታቸው የማይቀር መሆኑን አረዳቸው።

«እጅግ የተለየ የሚሆነው ነገር» አሉ አበምኔቱ። «እርሣቸው ይህንንም ወይም ያኛውን ፈፅሞ አይፈሩም። ይበልጥ የምንጐዳው ግን እኛ ነን»

«እንደማስበው በሁለት ቀናት ውስጥ . . . »

አበምኔቱ የመስቀል ቅርፅ አመላክተው አማተቡ። እንባቸውንም ጠራርገው፣ ለጆን ባፕቲስት ወደ ተያዘለት ክፍል ይዘውት ሄዱ።

የፀሐይዋን አወጣጥ ከሚመለከቱበት የማረፊያ ቦታ ወርደው፣ ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ሲሆን በመምጣት ላይ ሣሉ፣ ፍራንቾይዝና ገሮሚ፣ ጆን ባፕቲስት ከገዳሙ ወጥቶ ሽቅብ ሲመጣ አገኙት። ሞቅ ባለ ሁኔታ አቅፈውት ሰላምታ ከሰጡት በኋላ ስለጉዞውና ስለአመጣጡ ጠየቁት። እርሱ ግን ስለአሊስ ተጨንቆ ነበር።



«ለጥቂት ወደ ኋላ ቀረት ብላ ነው። ለአጭር ጊዜ ያህል ብቻዋን መሆን ስለፈለገች ነው። ከዚህ ብዙም በማይርቀው ከቤተመቅደሱ ባሻገር፣ በትልቁ ማህበረሰብ መሬት ላይ ታገኛታለህ» አለችው ፍራንቾይዝ።

እነርሱን ትቶ በመሄዱ ይቅርታ ጠይቆ፣ ጆን ባፕቲስት የእግር መንገዱን ተከትሎ ሽቅብ ቀጠለ። ጊዜው ሞቃት ስለነበረ ጃኬቱን አውልቆ ትከሻው ላይ አደረገው። አነስተኛዋ ቅድስተ ቅዱሳን በመንገድ መጠማዘዣ አጠገብ በድንገት ታየች። ቤተክርስቲያኗ ተራ የድንጋይ ጉጆ ናት። ጣሪያዋም በቅርፅ የለሽ የድንጋይ ቁርጥራጮች የተሠራ ነው። መነኮሣቱ፣ ሌላው ቀርቶ የመስቀል ቅርፅ እንኳ በላይዋ ላይ አላቆሙም። ይህን ያደረጉት የተለያየ እምነት ኖሯቸው ሃሣባቸውን ሰብስብ አድርገው ራሣቸውን መግዛት ለሚፈልጉ ጐብኚዎች ካላቸው አክብሮት የተነሣ ነው። ሕንፃውን፣ ከአንድ ባህረገብ መሬቱ ላይ ካለ ቋጥኝ ጋር የሚያገናኝ አነስተኛ ደልዳላ መሬት ሲኖር፣ ቀጥ ብሎ የሚታየው ቋጥኝ አንድ የተንጠለጠለ አካል ይመስላል። በዚህ ቦታ መሬቱ በሦስቱ ማዕዘኖቹ የሰመጠ ስለሆነ፣ የፀሐይዋን አወጣጥ ለማየት የሚጋርድ እንቅፋት የለም። በነዚህ የድንጋይ ቅርፆች መካከል ጆን ባፕቲስት፣ አሊስን ለይቶ አወቃት። ወይም መኖርዋን ተገነዘበ። እርስዋም ብትሆን እንደተመለከተችው ተመሣሣይ ሃሣብ አድርባት ባለችበት ቆመች። ወደርስዋ ሮጠ። አሥር እምጃዎች ያህል ሲቀረው ሆን ብሎ ርምጃውን አንቀረፈፈው። ምን ያህል ተለውጣለች! ፊትዋ፣ ሰውነትዋና አቋቋምዋ በአጠቃላይ የጐመራ ነው። ውበትዋም ይበልጥ ያሸበረቀና የሚያበራ ሆኗል። የለበሰችው የፈረስ ግልቢያ ልብስ ነው። ጥብቅ በሚያደርጋት ጠባብ ልብስ የታሠረች አይደለችም። ፀጉርዋን ለቃዋለች። በርስዋ ላይ ከሚታየው የግርማ ሞገስ ድባብ ጋር ሲታይና ማንም ሊቆጣጠራት የማይችል መሆኑ ሲታወቅ፣ ይህ ሁሉ ነገር ኢምንት ነው። እርስዋም በበኩልዋ፣ እርሱ ባልነበረባቸው ጊዜያት፣ አብሯት ያኖረችውን የደከመ ቅርፅ፣ ይበልጥ የደቀቀ ሆኖ ሲታያት እንዳልነበረ ሁሉ፣ አሁን ብርቱና ሃያል ቁመናው ጐልቶ ወጣ። ብሩህ ዓይኖቹና ተዋህደው የሚታዩት የብርታትና የቁመና ዛላው የርሱን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ እንደነበረ አድርጐ አሣያት።

ሁሉም ነገር እንግዲህ ይኸው ነው። ሁሉም እንቅፋት ተሸንፏል። ጠጠራማ ከሆኑ አሥር እርምጃዎች ያህል ከሚሆን ስፋት በስተቀር ሁለቱን የሚለያቸው አንዳችም ነገር የለም። የደምና የዘር ልዩነት፣ የአባቷ ተቃውሞ፣ የንጉሡ ግዴለሽነትና የብዙ ሰዎች ምቀኝነት፣ በእግራቸው ሥር ሆኖ ከሚንከባለለውና ቀልጦ ከቀዘቀዘው የእሣተ ገሞራ ፍርክስካሽ የበለጠ ጉዟቸውን ሊያደናቅፈው የሚችል አይደለም።

ለመነካካት በተቃረቡበት ጊዜ እርስ በእርሣቸውን በሃፍረት ተመለከቱ:: እስከዚህ ሰዓት ድረስ ሁለቱም ያከናወኑት ተግባር፣ ራሳቸውን ለዕውነተኛና ፍፁም ትኩረትን ለሚሻው የመጀመሪያው ግንኙነታቸው መንገዱን ማዘጋጀት ነበር:: በጉን የመተያየቱና ዓይን የመስበሩ አስቂኝ ጨዋታ አብቅቷል:: ከዚህ በኋላ ሁለቱም ነፃ ናቸው:: ሁለቱም አንዳቸው ሌላውን ሙሉ በሙሉ በነፃነት ለማየት ነፃ ነው:: ከዚህ በኋላ አይን አፋርነትን አሽቀንጥረው በመጣል ምን መሆን እንደቻሉ ያያሉ::

አሊስ፣ እጇን በዝግታ ወደ ጆን ባፕቲስት ክንፈሮች አስጠጋች:: የጣቶችዋን ጫፎች ሳማቸው:: እነዚህ ጣቶች ነፃ ስለነበሩ ደስታቸውን የድብብቆሽ የሚያደርጉበት ሁኔታ ከእንግዲህ በኋላ የለም:: ወይም ደግሞ በችኮላ ምክንያት ንክኪያቸውን በማጣደፍ የሚሰጡትን ደስታ መቀነስ ከእንግዲህ በኋላ የለም::

ሰማዩ ትላልቅ የጥጥ ባዘቶ በመሰሉ ደመናዎች ተሞልቶ ፀጥታ የሰፈነበት ነው:: ጆን ባፕቲሰት፣ ጃኬቱን በአንድ ቋጥኝ ላይ ጥሎ አሊስን አቀፋት:: ሁለቱም ነፃ ስለነበሩ ስሜታቸውንና መፈላለጋቸውን የሚገቱበት አንዳችም ምክንያት የለም:: ይህን ማድረጋቸው ደግሞ ተገቢም ነው:: ተሣሣሙ:: ከንፍሮቻቸው በፍቅር ተደሣሰሰው፣ በጋራ ቀለጡ:: በሕይወታቸው ውስጥ እንዲህ ባማረና ትክክለኛ በሆነ መልክ ለአፍታም ያህል እንኳ መደሰትን አስበው ለማያውቁ ጥምር፣ ስለዚህ ጉዳይ የሚነገር የለም::

አንዳቸው ሌላው ላይ ልጥፍ ብለው በመተቃቀፍ እየተራመዱና የመሣሣማቸውን ዕድገት መቋረጥ ለመቀጠል ቆም እያሉ፣ ማለዳውን በሙሉ በተራራው ላይ ቆዩ:: ግዙፍ የጥቁር ድንጋይ ቋጥኞች፣ እንደ ታላቅ መፅሐፍ ገፆች እርስ በርሳቸው ተሰድረዋል:: የተለያዩ የምድሩ ገፅታዎችም በተከታታይ ልዩ ልዩ ሰማያዊ ቀለማት ይታያሉ:: ራቅ ብሎ ወደ ቀይ ባህር አካባቢ እነዚህ ቀለማት ወደ ሃምራዊ ጥላነት ያደላሉ:: በምድር ላይ ከሲና ተራራ ከፍታ በበለጠ የተሰቃየ ቦታ የለም:: ይህ የተራራ ከፍታ ከቀለጠው የምድር ማህፀን ውስጥ ተመዝዞ በመውጣት፣ በማዕበል በሚተራመሰውና በዝናብ ደመናዎች ተሸፍኖ በሚወራጨው አውሎ ነፋስ ተጠምዝዞ ሽቅብ የተመዘዘ ይመስላል:: ፀጉራቸውን እንዲደበላለቅና በነፋሱ ሀይል እንዲውለበለብ በሚያደርገው በሞቃቱ ነፋስ ውስጥ ተጓዙ::

«ምን አይነት አስማታም ቦታ ነው:: እንዲያው እግዚአብሔር በማንኛውም ቅጽበት በደመና ውስጥ ሆኖ ሊመጣ የሚችልበት አካባቢ አይመስልም?» አለ ጆን ባፕቲሰት



«እግዚአብሔር እዚህ እፊት ለፊታችን ዱብ ቢል ምን ታደርጋለህ?» ስትል አሊስ እየሣቀች ጠየቀችው::

«ደግ፣ በመጀመሪያ አረፍ እንዲል እጠይቀዋለሁ:: ያውም በዚህ ትልቅ ቋጥኝ ላይ፣ ምክንያቱም ሳስበው እጅግ በጣም የሽመገለና የደከመው ሰው አድርጌ ነው የማስበው»

«እና ከዚያስ?» በማለት በፍቅረኛዋ ግንባር ላይ የተለጠፈውን ፀጉር ወደጐን እያነሳችለት::

«እና ከዚያም እንዲባርከን እጠይቀዋለሁ:: ከዚያም ስለርሱና ስለኛ ሕይወት እንጫዋወታለን»

«እንበልና አሥርቱን ትዕዛዛት ቢሰጥህስ?»

«ሕይወት ባላቸው ፍጥረታት ሁሉ ዘንድ ተጽፈው መገኘታቸውን እነግረውና ደስታ ቢስነትን የሚያስከትሉት ቀሣውስትን፣ ነገስታትና አባቶችን ለማግኘት ካልሆነ በስተቀር በተለይ ለማንም እንዳይሰጥ እለምነዋለሁ::»

«ይህማ እጅግ በጣም ብልግናና ድፍረትም ይሆንብሃል:: ስለዚህም የቁጣውን መብረቅ ሊልክብህ ይችላል»

«ለምን ይልክብኛል::» አለ ጂን ባፕቲስት እንደማዘን ብሎ «በርግጥ እግዚአብሔር እኮ ደስተኞችን ሰዎች የሚያፈቅር ነው»

እነዚህን ፍፁም የደስታ ሰዓታት፣ በየመካከሉ በሚኖሩ በሣቅ በተሞሉ ጭውውቶችና የእርስ በርስ መደባበስ አሣለፉ::

የቁልቁለቱን የእግር መንገድ ተከትለው ወደ ገዳሙ ሲመለሱ፣ ተለያይተው በቆዩባቸው ጊዜያት በነበሩት ሁኔታዎች ላይ በዝርዝር መነጋገር ጀመሩ:: ይህን ርዕስ ለረዥም ጊዜ ያህል ሊጨርሱት እንኳን አልቻሉም:: ምስጢሩን ይዛ መቆየት ስላስጨነቃት፣ ራሷን ለሌላ ሰው ገልፃ መስጠቷን አውጥታ ልትነግረው ወሰነች:: ማን እንደሆነና ለምንስ እንዳደረገች በአጭሩ ነገረችው::

«ታፈቅረዋለሽ?» ሲል ጆን ባፕቲሰት ጠየቃት

«ሀሳቤ ሁሉ አንተ ነበርክ:: አንተን ማፍቀሬን ለአፍታ ያህል እንኳ አቋርጬ አላውቅም»

«እንዲህ ከሆነ ታዲያ ምን ይፈይዳል? እኔ ጌታሽ አይደለሁም:: እንደዚህ እንዳንቺና እንደኔ ባለ አንድነት ላይ ግዴታዎች የሉም»

ለመናገር የፈለገውን ወይም የተመኘውን ሳይል፣ የበቀል ስሜቱን መወጣቱን በማሰብ፣ ጆን ባኘቲስት በውስጡ ፈገግ አለ።

ጎዳሙ ውስጥ ምሳቸውን ከፍራንቾይዝና ከሜትር ዠረሚ ጋር ተመገቡ። ደስታውን በጥሩ መንፈስ የተቀበለው ኘሮቴስታንቱ የቀድሞው ፈገግታውንና ወሬኛነቱ ተመልሶለታል። ከእንግዲህ በኋላ ዋናው ቁም ነገር ወዴት ይሂዱ ነው። ምንም እንኳ በቅድስት ካተሪን ገዳም ጥላ ከለላ ውስጥ ቢሆኑም፣ አሁንም የሚገኙት በታላቁ የቱርክ መሪ አገር ውስጥ ነው። በመሆኑም እነርሱን የመፈለጉ ጉዳይ መቀጠሉ እንደማይቀር እርግጥ ነው።

«ፍራንቾይዝና እኔ ወደፈረንሣይ እንሄዳለን» አለ ሜትር ዠርሚ

«ወደ ፈረንሣይ? ሬሣህ እንዴ? አንተ እኮ ኘሮቴስታንት ነህ»

«እኔ ከረሣሁም እነርሱ ያስታውሱኛል» አለ ሜትር ዠረሚ እየሣቀ «ቁም ነገር እንጨዋወት። ከማህበረሰቡ ተገልሎ በዚህ በምስራቃዊ የዓለም ክፍል መኖር ይሻላል? ወይስ በራስ አገር መኖር ይሻላል? የሕህይወት መራራው ክፍሉ ሁሉ ወደ መንከራተት ሕይወት እንደሚያመራ የምናገናዝብበት ዕድሜ ላይ ደርሰናል። ስለዚህ በምንም ዓይነት መልክ የሚያደርጉልንን አቀባበል እንቀበላለን»

በዚህ ጉዳይ ላይ ፍፁም አምነውና አቋምም ይዘው ስለነበረ፣ ጉዳዩን እንደገና እንዲያስቡበት የማስደረግ ተስፋ የለም። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ካይሮ ውስጥ ስለአሊስ መጠለፍ በመግለጽ ያናፈሰውን ወሬ ለማቀዝቀዝና ለማርገብ ሲሉ ሁለቱ ለአንድ ወር ያህል በገዳሙ ውስጥ በመቆየት ይሰነብታሉ። ከዚያም ወደ ፖለስታይን በመሄድ ወደ ቆጵሮስ፣ ወደ ግሪክ፣ ወደ ቬነስና በመጨረሻም ፈረንሣይ የሚያደርሣቸውን መርከብ ይሣፈራሉ።

ሁለቱን በጥንካሬአቸው፣ በመንፈስ እርጋታቸው፣ በተሞክሯቸው ብርታትና ፍፁም ጥልቅ በሆነ ፍቅር መዋሀዳቸው ሲታይ፣ ለጋራ ፈቃዳቸው የማይገዛ አንዳችም ነገር የሌለ ይመስላል።

አሊስ፣ ስለ አቢሲኒያ አብዝታ ታልማለች። ጆን ባኘቲስትም የማወቅ ፍላጐትዋን ይበልጥ በመቀስቀስ፣ ለሰዓታት ስለአቢሲኒያ ያወራላታል። አጭር ጊዜም ቢሆን ወደዚያው ለመሄድ አቅደው ነበር። ይሁን እንጂ ለአንዳንድ ከአልቱር ለመጡ ባህረኞች ምስጋና



ይግባቸውና፣ ገዳሙ ውስጥ በሰነበቱበት ጊዜ ከሙራድ የተላከ ደብዳቤ ደርሷቸዋል። ሙራድ፣ ምጽዋ ደርሶ ተልዕኮውን ከዚያ ላይ አጠናቅቋል። በደብዳቤው ላይ ስለኢትዮጵያ አንዳንድ ዜና ገልፆላቸዋል። ንጉሡ ነገስቱ እያሱ፣ ከጥቂት ወራት በፊት አርፈዋል። ምናልባትም ጆን ባኘቲስት እንደሚታመሙበት አውቆ በነገራቸው ሕመም ሳቢያ ሳይሆን አይቀርም። በካህናቱ ተጽዕኖ ሥር ያደገው ልጃቸው ለውጭ አገር ሰዎች መጥፎ አመለካከት አለው። ሌላው ቀርቶ ሙራድም እንኳ ወደዚያው ተመልሶ በመሄድ ስለተልዕኮው ሪፖርት የማቅረቡን ሀሣብ ፈጽሞ ትቶታል። ከዚህ ይልቅ ወደ አሌፖ ወይም ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ እንደውጭ ቤት እየሠራ ካይሮ ውስጥ በሚኖሩ ፈረንሳውያን አጠገብ የመኖር ዕድሉን ለመሞከር መርጧል።

ከሙራድ ዘንድ የመጣው ዜና፣ ከአደጋ ሊጠብቃቸው ለሚችሉትና በከፊል ጆን ባኘቲስት፣ ለንጉሡ ነገስቱ በነበረው ወዳጅነት ተነሳስቶ ሊያደርገው አስቦት የነበረውን ጉዞ እንዳይሞክረው የሚመክር ነበር። የውጭ አገር ሰዎች በዚያች አገር ጉዳይ ጨርሶ ጣልቃ እንዳይገቡ አጥብቆ ያስብ የነበረው ጆን ባኘቲስት፣ አሁን አሁን ምዕራቡና ምዕራባዊያኑ ያልተሳተፉበትን፣ አቢሲኒያ የራሷን ታሪካዊ ፈለግ መከተሏ የሚያሳዝነው ሊሆን አልቻለም።

በዚህ የተነሳ ፍራንቾይዝና ሜትር ዠረሚን በማጀብ ወደ ሰሜን እስከ ኤክሬ ድረስ ለመጓዝ ወሰኑ። ከዚያ በኋላ የየራሣቸውን ምርጫ ያደርጋሉ።

የገዳሙ አስተዳዳሪ ህመም እየጠናባቸው ሄዶ ከአንድ ሣምንት በኋላ አረፉ። ቀብራቸውም በብርታትና በፍቅር ስሜት ተከናወነ። መነኩሳቱም የሚተኳቸውን ሰው መረጡ። አሊስና ጆን ባኘቲስትም ወደ ተራራው የሚያደርጉትን ረዥም ጉዞ ልምድ እያደረጉት መጡ። ነገር ግን በገዳሙ ውስጥ በሚገኙት ስርጓጉጥ የጨለማ መንገዶችም ውስጥ መሽሎክሎክ ሲልና ቀኑን እንቆ የያዘው ሙቀት ቀዝቀዝ ሲል፣ ከቤተክርስቲያኑ በስተምስራቅ በኩል የሚገኘውንና የሚወዱትን አንድ አነስተኛ የዕረፍት ቦታ ለመጎብኘት። ይህ ቦታ በሚያስገርም መልኩ ሁል ጊዜም ባዶ ሆኖ ቢታይም ማንም የማያስተውላትና ከማንም ምንም አይነት እንክብካቤ የማታገኝ ቁጥቋጦ በቅላበታለች። ከዚህም በላይ ይህ ቦታ የገዳሙ የህልውና መሠረት ነው። የሕንፃው የተቀደሰና ዓብይ ነገር ሁሉ የሚሽከረከርበትም ነው። ይሁን እንጂ ይህቺ ተክል በመጀመሪያ በተገኘችበት ቦታ ላይ ከነበረችው ወይም ደግሞ ጆን ባኘቲስት አል ዋህ አጠገብ ካገኛት ተክል ጋር ተመሣሣይ ዝርያ ያላት አይደለችም። በመጠኑም ቢሆን ሁለቱንም ቅር ቢያሰኛቸውም፣ እንደተነገራቸው ግን ይህች እየነደደች ያለች የምትመስለው ቁጥቋጦ እውነተኛዋ ዕፀ ሙሴ ነበረች።

# ተጨማሪ መረጃ

ጆን ባፕቲስት፣ ከፕሮቴስታንት አማኢያን ጋር በፈረንሣይ ፕሮቬንስ ውስጥ መገናኘቱን ከሰማበት ዕለት አንስቶ ሜትር ዠረሚ የሚያልመው ሌላ ምንም ነገር ሳይሆን እነዚሁት አማኢያን መቀላቀል ነበር:: ሁለቱም ፈረንሣይ እንደገቡ በተቀማጭ ገንዘባቸው አንዲት አነስተኛ ሆቴል ወዲያውኑ ተከራዩ:: እርስዋ የካቶሊክ እምነት ተከታይ ስለነበረች ማንም የተቃወመ አልነበረም:: ቀን ቀን ይህችው አነስተኛ ሆቴል ለመንገደኞች፣ ከአገር ቤት ለሚመጡ ባላገሮችና ለወታደሮች የመጠጥ ሽያጭ አገልግሎት ትሰጣለች:: ሲመሽ ደግሞ ሜትር ዠረሚ ከተቀላቀላቸው አድመኞች ጋር ከተራራው ወርዶ ይመጣል:: ስድስት ወር ባልሞላው ጊዜ ውስጥ አማኢያኑ ግልፅና አደገኛ የርስ በርስ ጦርነት በክልሉ ቀሰቀሱ:: እነዚህን በታሪክ «ቁምጣ ለባሽ» ሆነው ብቅ ያሉትን ሽፍታዎች ለማሸነፍ፣ በማርሻል ዱ ቬላርስ የሚመራ ሠራዊት በሙሉ አስፈልጎ ነበር:: ሜትር ዠረሚ በጓደኞቹ ዘንድ ራቬኔል ተብሎ ሲታወቅ ከመሪዎቻቸው አንዱ ነበር:: ሕዝባዊው አመፅ ከተደመሰሰ በኋላ ዠረሚ ለማምለጥ ሲችል ፍራንቸይዝም ተከተለችው:: የሁለቱ ሰዎች ዱካ እዚህ ላይ ጠፋብን:: ይሁን እንጂ ኢንግላንድ ውስጥ ጥገኝነት የማግኘታቸው ምልክት ነገር ነበር::

ጆን ባፕቲስት፣ እከሬ ውስጥ የአገሪቱን ታዋቂ ሃብታሞች በማከም በቂ ገንዘብ አግኝቶ ወደ ሲሪያ ተሻገረ:: ከአሊስ ጋር ወደ ፓልሚራ ሄደው፣ ከዚያም ምድረ በዳውን ሁሉ አቋርጠው፣ በኢፍራጠስ አካባቢ ባለ ረግረጋማ አገር ደረሱ:: ከዚያም ወደ ፋርስ በመሄድ በዚያ ያስስጋት ኖሩ:: ይሀን ሁሉ አገር ሲጓዙ መንፈሣቸው እንደመራቸውና እነርሱም ደስ እንዳላቸው ነበር:: ኢስፋሃን ውስጥ ጆን ባፕቲስት የተለመደውን ጥበቡን በመቀጠል ዝነኛ ስኬት አግኝቶ ነበር:: ፋርሳውያንና የውጭ አገር ነጋዴዎች በሙሉ፣ ዲፕሎማቶች፣ የሕዝብ መሪዎችና ሌላው ቀርቶ የከተማዎቹ ቁጡዎቹ ኢማሞች ሳይቀሩ የጤንነትን ጉዳይ በተመለከተ ያማክሩት ነበር:: በአጭር ጊዜ ውስጥ በሰማያዊው መስጊድ አጠገብ አንድ ትልቅ ቤት ለመግዛት በቂ ወርቅ አገኘ:: በዚህ ቦታ የአየር ጠባዩም ሁሉንም አይነት ተክል ለማብቀልና ለማሣደግ ተስማሚ ነበር:: በሕክምና የአትክልት ሥፍራው ውስጥ በጉዞዎቹ ዘመናት ሲሰበስባቸው የነበሩትን የተክሎች ፍሬዎች አበቀላቸው:: አሊስ፣ ጽጌረዳዎችን ማሳደግ ጀመረች:: ከዚህ ቦታ ወደ ሌላ መሄድ ፈፅሞ አልፈለጉም::



ሉዊስ 14ኛ ሲሞቱ፣ የአርሊያንሱን መስፍን እንደራሴ መሆን ቆይተው ሰሙ:: እኒህ መስፍን የቻርትሬስ ገዥ ሣሉ ጆን ባፕቲስት አግኝቷቸው ነበር:: ጆን ባፕቲስት ለዓፈላቸው ደብዳቤ፣ እንደራሴው፣ ፖንሴ፣ ፖሬስን ቢጎበኙ እጅግ የሚደሰቱ መሆናቸውን የሚገልፅ በራሣቸው እጅ ጽፈው መልስ ላኩለት:: ጆን ባፕቲስት ይህን መልዕክት ከአሊስ ጋር ተመካከረበት:: በመጨረሻም የሚወዷቸውን ተራሮችና ፅጌሬዳዎቻቸውን ላለመተው ወሰኑ::

አቢሲኒያን በተመለከ፣ ከዱ ሮውሌ ሞት በኋላ እጅግ ለረዥም ጊዜ ባለማቋረጥ በስፋት ሲነገርና፣ ከጄስዊቶች አሣዛኝ ውድቀትና ከካፑቺኖች ከአገር መባረር በኋላ፣ ለአንድ ተኩል ምዕተ ዓመት ያህል አገሪቱ ከማንኛውም ዓይነት የውጭ አገር ወረራ ተጠብቃ ቆይታለች:: ይህም ሲባል ጥቂት በእንግሊዛውያን የጂኦግራፊ ሊቃውንት የተደረጉት ሰላማዊ ጉዞዎች ሳይዘነጉ ነው:: ከአሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ያውም የስዊዝ ካናል ከተጠናቀቀ በኋላ፣ የቅኝ ገዥዎች መስገብገብ እንደገና ወደ ቀይ ባህር አቅጣጫ ዞረ:: አቢሲኒያም አንድ ጊዜ ፖንሴ ያስጠነቀቃትን የእነዚህን ሃይሎች እንደገና መመለስ ተመለከተች:: ይህ ሊሆን የቻለው ምናልባትም አገሪቱ፣ ነባሩ እምነትዋ፣ ራስዋን በራስዋ የመምራትዋና ባህልዋ እነዚህን ሃይሎች ለመቋቋም የሚችል ስለሆኑ ይሆናል::

በሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ፣ በኢጣሊያ ኤርትራ ዜና ታሪክ ውስጥ፣ ፖንሴ የሚለው ስም እንደገና ብቅ ይላል:: ይህኛውም ፖንሴ፣ አስመራ ውስጥ መድሃኒት ቀማሚ ነበር:: ምናልባትም ከአሊስና ከጆን ባፕቲስት አራት ልጆች ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ሊሆን ይችላል:: ልክ በደስታ ስለኖሩ ሰዎች ብዙም ሳይታወቅ እንደሚቀር ሁሉ፣ይህን የሚያፈርስ ታሪክ የለም:: በርግጥም የሚያረጋግጠውም መረጃ የለም:: ደስተኞች ኖረዋል:: ደስታቸውም ታሪክ ይሆናል::